# የዘመናችን
# ቤተ ክርስቲያንና
# የመሪዎቿ መሠረታዊ
# የአመራር ሥልት

---

**ክፍል ሁለት**

ከዶክተር መለሰ ወጉ

## ሌሎች በዶክተር መለሰ ወን ተጽፈው የቀረቡ መጻሕፍት

- ስሜት ያለቦታው
- ስንካከስ እንዳንጠፋፋ
- በጸሎት፥ የማይቻለው ይቻላል
- እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?
- የአዕምሮ ጭንቀት
- መንፈሳዊ ውጊያ
- ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅና ማድረግ
- ጋብቻ፥ እስከ ሞት ወይስ እስከ መፋታት?
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማወቅና በአግባቡ መጠቀም
- እስቲ ምላስህ!
- የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ-ክፍል አንድ
- ከአስቸጋሪ ሰዎች ጋር አብሮ መኖር፣ መሥራት፣ መጎራበት፣ ማምለክ...ይቻላል?

የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና የመሪዎቿ መሠረታዊ የአመራር ሥልት - መጽሐፍ ሁለት
*"Ye'zemenwa beteChrisitan Inna Ye'mereewochwa Meseretawee Ye'amerar Silt"—Part Two*
"Today's Church and the Leadership Skills of Its Leaders"

የመጀመሪያ እትም፣ ሰኔ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.
First Edition, June 2007

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው እትም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች፥ እንዲሁም በኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ከታተመው 'አዲሱ መደበኛ' መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ይህን መጽሐፍ በከፊልም ይሁን በሙሉ፥ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ለማባዛት፥ በቅድሚያ ከኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ዋና ጽሕፈት ቤት የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

Copyright © 2007 by Ethiopian Outreach Ministry
All rights reserved. No part of this book may be reproduced in any manner without written permission from Ethiopian Outreach Ministry except in the case of brief quotations in critical articles and reviews.

Produced by:

Ethiopian Outreach Ministry
P.O. Box 2241
York, PA 17408
United States of America

http://www.eomusa.org

Ethiopia Office Address:
P.O.Box 7888, Addis Ababa, Ethiopia.
Phone: 011-281-1-864-268

Printed in Ethiopia

# ማውጫ

ገጽ

መግቢያ ........................................ 5

ምዕራፍ

**ክፍል አንድ ~ ቤተ ክርስቲያንና የአማኞች አንድነት**

1 ▶ ለቤተ ክርስቲያን ሀልውናና ዕድገት የአማኞች አንድነት ወሳኝ ነው ........................ 9

**ክፍል ሁለት ~ መሪዎችና አገልግሎታቸው**

2 ▶ መሪነት፥ በጸጋ ላይ የተመሠረተ ጥሪ ........................ 38

3 ▶ ጥሪን መጠበቅና የማሳደግ ኃላፊነት ........................ 73

4 ▶ መንፈሳዊ ጤንነት ........................ 103

**ክፍል ሦስት ~ መሪዎችና ዕሠይት ሥርዓታቸው (Value System)**

5 ▶ ሎላዊነት ........................ 126

6 ▶ የፍቅር አገልግሎት ........................ 151

7 ▶ ባለራዕይነት ........................ 176

6 ▶ አድማጭነትና አዎንታዊ ነቀፋን የመቀበል ልብ ........................ 203

**ክፍል አራት ~ መሪዎችና አገልግሎት አፈጻጸማቸው**

9 ▶ አገልግሎት አሳታፊነትና አነሳሺነት ........................ 225

10 ▶ ግጭት አርጋቢነት ........................ 249

11 ▶ ተግባራዊ ዕቅድ ........................ 273

12 ▶ ሚዛናዊ ውሳኔ1 ........................ 297

13 ▶ ሥልጣንና ኃላፊነት ........................ 321

ዋቢ ጽሑፎች ........................ 341

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ፣ ቀደም ሲል ታትሞ የወጣው *"የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ"* የሚለው መጽሐፍ ተከታይ ወይም ሁለተኛው ክፍል ነው። መጽሐፉ አራት ክፍሎች የያዘ ሲሆን፣ ይኸውም 1ኛ፣ ቤተ ክርስቲያንና የምዕመናን አንድነትን፣ 2ኛ፣ መሪዎችና አገልግሎታቸውን 3ኛ፣ መሪዎችና ዕውይት ሥርዓታቸውን 4ኛ፣ መሪዎችና አገልግሎት አፈጻጸማቸውን ይተነትናል። ይህን መጽሐፍ አዘጋጅተን ለማውጣት የተነሳንበት ዋና ዓላማ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን የመሪነት ኃላፊነት እንደ ሚገባው መፈጸም እንዲችሉ፣ በእግዚአብሔር ቃል የተደገፈ ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን ለማካፈል ነው። ቤተ ክርስቲያን የተጠራችውና የተመሠረተችው፣ ከውጪ ያሉትን ነፍሳት በወንጌል ለመድረስ፣ ጥሪውን ተቀብለው ወደ አማኞች ሕብረት የተቀላቀሉትን ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለማሳደግ፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ለመስጠት ነው። ቤተ ክርስቲያን ሕይወታቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚመሩ፣ በእውነት ላይ የቆሙ መንፈሳዊ መሪዎች ያስፈልጓታል። ከሌሏት ግን፣ የተጠራችበትን ዓላማ እንደ ሚገባው መፈጸም፣ እንዲሁም የሚገባውን ክብር ለእግዚአብሔር መስጠት አትችልም። ቤተ ክርስቲያን በምታደርጋቸው እንቅስቃሴዎች፣ መንፈሳዊ መሪዎች ትልቅ ድርሻ አላቸው። ቤተ ክርስቲያን ከውጪ ያሉትን በወንጌል መድረስ ካልቻለች፣ ውስጥ ያሉትን ልጆቿን እንደሚገባው ማሳደግ ካቃጣት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተደጋጋሚ የሆነ ጠብና ግጭት የሚስዛ ከሆነ፣ ምዕመናን ሁሉ የአገልግሎት ተሳትፎ ሲኖራቸው ሲገባ ጥቂቶቹ ብቻ የሚያገለግሉ ከሆነ፣ *"ቤተ ክርስቲያኒቱ የመሪዎች ድካም ወይም ችግር ይኖርባት ይሆን?"* ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለናል።

*"መሪነት" (Leadership)* መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ይህም ማለት በዓለም ውስጥ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊነት ባለው ሕብረት ውስጥም *"መሪና ተመሪ"* እንዲኖር መጽሐፍ ቅዱስ ይደግፋል። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን እንዲመሩ መርጦ ያስቀመጣቸው ሰዎች፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተቀመጡ መሆናቸውን አምኖ ምዕመኑ በሙሉ ልቡ እንዲቀበላቸው ወይም እንዲከተላቸው ቢጠይቁ፣ ራሳቸውን ማተለቃቸው እንዳልሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። "መሪነት" መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ያልተረዱ አንዳንድ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ *"ሁላችንም እኩል ስለሆንን ማንም ሌላውን ይህን አድርግ፣ ወይም አታድርግ በማለት ትዕዛዝ መስጠት አይችልም"* የሚል አስተያየት ሲሰጡ ይሰማሉ። ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ መንፈሳዊ መሪዎችን መርጦ የሚሾመው፣ እንደ ዓለማውያን መሪዎች ሥልጣን የተጠሙትን፣ በሕዝቡ ላይ "አለቃ" መሆን የሚፈልጉትን ሳይሆን፣ እንደ አሽከር ወይም እንደ ባሪያ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማገልገል የሚፈልጉትን ብቻ ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመናንም፣ ወደ እግዚአብሔር ዓላማና ፈቃድ የበለጠ ሊያስጠጓቸው ጥረት ስሚያደርጉ እውነተኛ መሪዎች ራሳቸውን ማስገዛት ከባድ አይሆንባቸውም።

በአሁኑ ዘመን በተለይ በኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከምንጊዜውም የበለጠ እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች የታጡበት ዘመን ነው። ምክንያቱ ምን ይሆን? በብሉይ ኪዳን ዘመን የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ላይ በሚያምጽበት ወቅት አልፎ አልፎ ይቀጣቸው የነበረው፣ መሪ በማሳጣት ወይም ብቃት በሌላቸው መሪዎች እንዲመሩ በማድረግ ነበር። ይሄም በኢሳያስ ትንቢት ውስጥ ተገልጿል። *"ገና ታዳጊ የሆኑና ለአምሮ ቸው ያልበሰለ ልጆችንም መሪዎች አድርጎ በሕዝቡ ላይ ያስነሳል"* ይላል (ኢ.ሳ. 3፥4)። በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ብቃት ያላቸው መሪዎች የታጡበት ከላይ በገለጽ ነው ምክንያት ይሆን? በአዕምሮም ሆነ በመንፈሳዊ ዕውቀት የተሞሉ፣ ከእግዚአብሔር ጥበ ብን የተቀበሉ፣ ቤተ ክርስቲያንን በጥሩ ሁኔታ የመምራት ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ጨርሶ የሉም ማለት ይሆን? ወይስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ ለመሆን ያለ ውን ከፍተኛ ትግልና ሽኩቻ ጠልተው ገለል ብለው የተቀመጡ አማኞች በመብዛታቸው ይሆን? ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት ራሱን የቻለ መጽሐፍ ማዘጋጀት ቢያ ስፈልግም፣ እዚሁ መጽሐፍ ላይ በመጠኑም ቢሆን አንዳንድ ምክንያቶችን ለማሳየት ሞክረ ናል። የእግዚአብሔር ሕዝብ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚጎዳው መሪ በማጣት ብቻ ሳይሆን፣ ጥሪም" ሆነ የጸጋ ሥጦታ የሌላቸው መሪዎች ሲመሩትም ጭምር ነው። እውነተኛ የሆኑ መሪዎች ሲጠፉ፣ የመሪነቱን ሥፍራ የሚይዙት የአመራር ዕውቀትም ሆነ ልምምድ የሌላ ቸው፣ በአዕምሮም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወት ያልበሰሉ፣ እንዲሁም ጥሪ የሌላቸው መሪዎች እንደሚሆኑ የታወቀ ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ከራሱ ሕዝብ ጋር የነበረውን ዓላማና ፈቃድ ይፈ ጽም የነበረው፣ መሪ አድርጎ በሚመርጣቸው ወይም በሚሾማቸው አንዳንድ ሰዎች አማካ ኝነት እንደሆነ እናውቃለን። የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ እንዲያወጣ ሙሴን እንዲሁም ሕዝቡን እንዲያስተዳድሩና እንዲመሩ በተለያዩ ዘመናት መሳፍንትንና ነገሥታ ትን፣ ቀጥሎም ነብያትን መርጦ የሕዝቡ መሪ እንዲሆኑ አስነስቷቸዋል። በአዲስ ኪዳን ዘመንም ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሠርቱና እንዲመሩ ሐዋርያትን ሲያስነሳ እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም በሚመርጣቸው መሪዎች እንደሚጠቀም መረዳት ያስችለናል። በአ ሁኑ ዘመንም እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም መርጦ ባስቀመጣቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይጠቀማል። ቤተ ክርስቲያን እንድታድግና ፍሬያማ እንድትሆን፣ መሪዎቿ የመ ሪነት ኃላፊነታቸውን እንደሚገባ መወጣት አለባቸው። መሆን የምትችለው፣ እግዚአብሔር መርጦ ያስቀመጣቸው ጥሩ መንፈሳዊ መሪዎች ሲኖሩት ነው። መንፈሳዊ መሪዎች ከዓለማ ውያን መሪዎች የተለዩ የሚያደርጋቸው፣ መንፈሳዊነት ያላቸው በመሆናቸው ነው። ስለ ዚህ፤ ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት የሌላቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአመራር ብቃት ወይም ችሎታ ያላቸው ቢሆኑ እንኳን የእግዚአብሔርን ሕዝብ፣ ወደ እግዚአብሔር ዓላማና ፈቃድ ሊያደርሱ አይችሉም። ለመሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች ከዓለማውያን መሪዎች የሚለዩት በምን ይሆን? መንፈሳዊ መሪዎች፤

- እግዞችን የእግዚአብሔርን ዓላማ በሕይወታቸው እንዲፈጽሙ ይረዳሉ፣



- በራሳቸው ጥበብና ችሎታ ከመደገፍ ይልቅ፣ በአመራራቸው የመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታን ይፈልጋሉ፣
- በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ስለሚያውቁ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ተጠንቅቀው ይመራሉ፣
- የራሳቸውን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ዓላማና ፈቃድ ይከተላሉ።

የጊዜው ሁኔታ በጣም ያሳሰባቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች፣ *"በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ተመሳሳይ የሆኑ ችግሮች (ግጭቶች) የሚፈጠሩበት ምክ ንያት ምን ይሆን?"* ብለው ይጠይቃሉ። አንዳንዶቻችን እንደተረዳነው፣ በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነው የተቀመጡ፣ እብዛኛዎቹ ቤተ ክርስቲያን በጥሩ መንፈሳዊ መሪዎች ሥር ሆና ስትመራ እያዩ ያደጉ አይደሉም። ትክክል መሆኑና አለመሆኑን ሳይመረምሩ፣ የሌሎችን የአመራር (የአስተዳደር) ስልት ኮፒ አድርገው ወይም ተከትለው ቤተ ክርስቲያ ንን ለመምራት የሚሞክሩ ናቸው። ሰየቦታው ያሉት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት አብዛኛ ዎቹ የሚመሩበት የአስተዳደር ሥልት ተመሳሳይነት ስላለው አንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረው ችግር፣ ሌላውም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲከሰት ይታያል። ሁኔታው አሳሰቧ ቸው በአመራራቸው ላይ ምን እንዳበላሹ አውቀው ራሳቸውን ለማስተካከል ቢፈልጉ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር (አመራር) ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን የያዙ በአማርኛ ቋንቋ ተዘጋጅተው የወጡ መጽሐፍትን አያገኙም። በእንግሊዝኛ የተጻፉት በአማርኛ ተተርጉ መው ቢወጡ እንኳን፣ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ያለባቸውን ወቅታዊ የአመራር ችግር ላይ ያተኮረ ሰላልሆነ፣ አስፈላጊውን ዕርዳታ ማግኘት አይችሉም። ብቃት ያላቸው ኢትዮጵያውያን አስተማሪዎች ቢኖሩ እንኳን፣ አንዳንዶቹ "መሪዎች ነን...፣ ሁሉን እናው ቃለን" ብለው ስለሚያስቡ፣ ተምረው የአመራር ሥልታቸውን ለማስተካከል ፈቃደኞች አይሆኑም። ለውጥ ስለሚፈሩ፣ በልማድ ካገኙት አንድ ዓይነት የአመራር ሥልት ውጪ ሌላ ዓይነት የአመራር ሥልት መቀበል አይፈልጉም። ይህን መጽሐፍ አዘጋጅተን ለአንባ ብያን ማቅረብ የፈለግንበት ምክንያት፣ በስማችን ተዘጋጅተው የሚወጡትን መጽሐፍት ቁጥር ለማብዛት ሳይሆን፣ የመንፈሳዊ መሪዎች ዕጥረት ጎልቶ በሚታይበት፣ በቤተ ክርስቲ ያን ውስጥ ብዙ ግጭትና መለያየት ጎልቶ በሚታይበት በአሁኑ ዘመን፣ መጠነኛም ቢሆን አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን ይሰጣል ብለን ስላመንበት ነው። በዚህ ዘመን ያሉት መሪዎች በመጽሐፉ ለመጠቀም ፈቃደኞች ባይሆኑ እንኳን፣ መጪው ትውልድ ይጠቀም በታል ብለን እናምናለን።

ይህ መጽሐፍ የአመራር ሥልቶችን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ ነው ብለን ባንልም፣ ወደ ፊት በስፋው ተዘጋጅተው ለሚወጡት መጽሐፍት መንደርደሪያ ሀሳብ ይሰጣል ብለን እና ምናለን። በሰለጠነው ዓለም፣ ዓለማውያን ጸሀፊዎች ስለ አመራር ወይም አስተዳደር አዘጋ ጅተው ያወጧቸው ብዙ መጽሐፍት አሏቸው። "መሪነት" ምን እንደሆነ የራሳቸው የሆነ ገለ ጻና መረዳት፣ እንዲሁም "የመሪነት ንድፈ ሀሳብን" (ቲዮሪን) ይዘዋል። የሚከተሉት ንድፈ

ሀሳብ (ቲዮሪ)፣ ከመንፈሳዊ መሪነት በብዙ አቅጣጫዎች የተለየ በመሆኑ፣ በመጽሐፎቻቸው የሚያቀርቡትን አሳብ ሙሉ በሙሉ ተቀብለን ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት እንደ መመሪያ አድርገን እንዳንወስድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ይህን ስንል፣ ዓለማውያን የሚጽፏቸውን የአስተዳደር መጽሐፍት ዋጋ ለሌላቸው ፈጽሞ ማንበብ የለብንም ማለት እንዳልሆነ በቅድሚያ መግለጽ እንወዳለን። ይህን መጽሐፍ ሰፊ ጊዜ ወስደን አዘጋጅተን ያቀረብንላችሁ፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ እንድትሆኑለት የሚፈልገውን ዓይነት መሪዎች መሆን እንድትችሉ የሚረዳችሁን ጠቃሚ ትምህርትም ሆነ ሀሳብ የምታገኙበት፥ እንዲሁም የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ ለማስፋፋት፣ ዓለምን በወንጌል ለመድረስ ለምታደርጉት ጥረት፣ አስፈላጊውን ጥበብና ዕውቀት የምታገኙበት እንዲሆንላችሁ በማሰብ ነው። ይህ ወቅታዊ የሆነው መጽሐፍ በአማረ መልክ ተዘጋጅቶ እንዲወጣ በሀሳባቸው፣ በገንዘባቸው፣ በጸሎታቸውና በምክራቸው ከጎናችን ለብዙ ዓመት አብረውን የቆሙትን፣ የአገልግሎት ተባባሪዎቻችንን ሁሉ ከልብ እናመሰግናለን።

## ምዕራፍ ፩

# ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የአማኞች አንድነት ወሳኝ ነው

*"አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት፥ ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው።"*
(1 ቆሮ. 12፥12)

ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያቀደው ዓላማ ምን እንደሆነ ለብዙ ዘመን ምስጢር (ድብቅ) ሆኖ የቆየ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ኤፌ. 3፥4-5)። ይሄ ለረጅም ጊዜ ምስጢር ሆኖ የቆየው እውነት፣ እግዚአብሔር የወሰነው ጊዜ ሲደርስ ተገለጠ። ሐዋርያው ጳውሎስ ምስጢር ሆኖ የቆየው ነገር ምን እንደሆነ ሲገልጽ፣ *"ይህም ምስጢር አሕዛብ በወንጌል አማካይነት ከእስራኤል ጋር አብረው ወራሾች፣ አብረው የአንዱ አካል ብልቶች እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው ተስፋ አብረው ተካፋይ መሆናቸው ነው"* ይላል (ኤፌ. 3፥6)። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ሊኖረው የሚፈልገው የተቀራረበ ግንኙነት ምን ዓይነት እንደሆነ ለማሳየት፣ እንዲሁም ታላቅ የሆነውን ክብሩን ዓለም እንዲያውቀው ለማድረግ የተጠቀመው፣ በልጁ ደም የዋጃትን ቤተ ክርስቲያኑን ነው። እግዚአብሔር ምስጢሩን ለመግለጥ የተጠቀመባትን ቤተ ክርስቲያን በዘመናት የተለያዩ የዓለም ጠቢባን ምንነቷን ለመግለጽ ሞክረው እንዳልተሳካላቸው እናውቃለን። መንፈሳዊ ባህሪ ያላትን፣ *"የክርስቶስ አካል"* ተብላ የምትጠራዋን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊነት የሌላቸው *"ሰብዓዊ የማኅበረሰብ ጥናት ምሁራን" (Sociologists)* በትክክል ሊገልጿት ባይችሉ፥ ይህን ያህል ሊደንቀን አይገባም። ምክንያቱም መንፈሳዊነት

የሌላቸው ሰዎች የእግዚአብሔር የሆነውን፣ ወይም መንፈሳዊነት ያለውን ነገር የመረዳት አቅምም ሆነ ችሎታ የሌላቸው በመሆናቸው ነው (የማር. 4፥11)። የቤተ ክርስቲያንን ትክክለኛ ምንነት፣ *"የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ"*[1] በሚለው መጽሐፍ ላይ በሰፊው የገለጽን ስለሆነ፣ አንባቢዎች መጽሐፉን ፈልገው እንዲያነቡ እናሳስባለን። ይሁን እንጂ፣ መንደርደሪያ አሳብ እንዲሆነን፣ በእግዚአብሔር ዕቅድ የተመሠረተችው፣ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ምን እንደሆነች ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ለመግለጽ ሞክረናል፥

- *ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አይደለችም። በሥርዓት የተደራጀች፥ ወይም ያልተደራጀች፣ መዋቅር ያላት፣ ወይም ምንም ዓይነት መዋቅር የሌላት መሆን ትችላለች። እንዲሁም የራሷ ሕንጻ ያላት፣ ወይም በግለሰብ ቤት ውስጥ የምትገኝ፥ ወይም አንድ የተወሰነ ሥፍራ ሳይኖራት የምትኖር፣ በጫካ ወይም በበረሃ፣ በድብቅ ወይም በግልጽ የምትንቀሳቀስ ልትሆን ትችላለች።*
- *መጽሐፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን፣ – ቤተሰብ፥ ሙሽራ፥ የወይን አትክልት፥ ቤተ መቅደስ፥ ሕንጻ፥ መንግሥት፥ መንጋና ብዙ ብልቶች ያሏት አንድ አካል ወዘተ. በማለት ይጠራታል።*
- *የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ "ተቋም" (Institution) ሳትሆን፣ "ሕይወት ያላት አካል" (Organism) ናት።*
- *ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ እምነት (denomination)፥ የሃይማኖት ወገን (sect)፥ ወይም ሰዎች የመሠረቷት ማኅበር ሳትሆን፥ "መንፈሳዊነት" ያላት "የክርስቶስ አካል" ናት።*
- *ቤተ ክርስቲያን ምድራዊ ድርጅት ሳትሆን፥ "ኮይኖኒያ" (Koinonia)–የአማኞች መተሳሰር ወይም ሕብረት ናት።*

## 1. ለቤተ ክርስቲያን ህልውናና ዕድገት፥ የአማኞች አንድነት ወሳኝ ነው

በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ዓይነት አንድነት፣ በዓለም ውስጥ በየትኛውም ዓይነት ድርጅት ወይም ማሕበረሰብ ውስጥ የሚታይ አይደለም። እግዚአብሔር አብ በወልድ ውስጥ እንዳለ፣ ወልድም አማኞችን እንደሚወድና እንዲሁም በልባቸው ውስጥ እንደሚኖር ለዓለም ሁሉ ምስክር ሊሆን የሚችለው፣ በአማኞች *"አንድነት"* ውስጥ

[1] መለሰ ወጉ፣ "የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ (ክፍል አንድ)" 2005.



ነው። ይኸም "እውነት" ውስን በሆነው በሰው አዕምሮ ሊገለጽ የማይቻል ነው። ለቤተ ክርስቲያን ህልውናዋም ሆነ ለመንፈሳዊ ዕድገቷ የአማኞች አንድነት በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚያውቀው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አባቱ ሲጸልይ እንዲህ አለ፥

> *"...አባት ሆይ! አንተ በእኔ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ እነርሱም በእኛ እንዲሆኑ ነው። እኛ አንድ እንደ ሆንን እነርሱም አንድ እንዲሆኑ፣ የሰጠኸኝን ክብር ሰጥቻቸዋለሁ። ይህም እኔ በእነርሱ፣ አንተም በእኔ መሆንህ ነው። አንተ እንደ ላከኸኝና እኔን በወደድኸኝ መጠን እነርሱንም እንደ ወደድሃቸው ዓለም ያውቅ ዘንድ አንድነታቸው ፍጹም ይሁን"* (የዮሐ. 17፥21-23)።

ኢየሱስ ክርስቶስ አልፎ በሚሰጥባት በዚያች አስጨናቂ በሆነችው ምሽት፣ ስለ ራሱ መከራና ሞት በማሰብና በመጸለይ ፈንታ፣ ስለተከታዮቹ አንድነት በማሰብ ክላይ ያየነውን ዓይነት ጸሎት ጸለየ። በዚህ ጸሎት ውስጥ የራሱ አካል ስለ ሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት ልመናዎችን በእግዚአብሔር አብ ፊት እንዳቀረበ እናያለን። ይህን ዓይነቱን ጸሎት የጸለየው ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ይኸውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መራራ የሆነውን የሞት ጽዋ ከቀመሰ፣ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ፣ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ ከወረደ በኋላ ለምትመሠረተው ለትንሿ እጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን፣ በዘመናት በዓለም ዙሪያ ለሚፈጠሩት አብያተ ክርስቲያናት ጭምር ነው። በአብ ፊት ያቀረበው ጸሎት አንደኛው፣ *"ሁሉም አንድ እንዲሆኑ"* የሚል ሲሆን፣ *ሁለተኛው፣ "...እንደ ወደድኳቸው ዓለም ያውቅ ዘንድ አንድነታቸው ፍጹም ይሁን"* የሚል ነው። ለዓለም ምስክር፣ እንዲሁም በመከራና በችግር ጊዜ ለአማኞች ድጋፍ ሊሆን የሚችለው ሌላ ነገር ሳይሆን፣ ኢየሱስ አጥብቆ የጸለየበት *"አንድነታቸው"* ነው። ቤተ ክርስቲያን ለማደግ ወይም ለመታነጽ እንድትችል፣ ምዕመናኖቿ እርስ በርሳቸው የተያያዙ መሆን አለባቸው። አንድ የሚሆኑበትም ምክንያት አንድ አምላክ፣ አንድ አባት ያላቸው በመሆናቸው ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን እውነት ሲገልጽ፥ *"...አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ፤ ከሁሉም በላይ የሆነ በሁሉም የሚኖር የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ"* ይላል (ኤፌ. 4፥4-6)። የቤተ ክርስቲያን አንድነት በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ኃይልና ጥረት የሚገኝ ባይሆንም፥ አማኞች አንድነታቸውን እንደያዙ ለመቆየት የራሳቸውን ድርሻ መፈጸም አለባቸው። የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፣ ሁለት ዓይነት "አንድነት" የሚያስፈልጋት ናት። ይኸውም፥ አንደኛው "የመንፈስ አንድነት" ሲሆን፥ ሁለተኛው "የእምነት አንድነት" ነው።

## 1.1. የመንፈስ አንድነት

የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሊኖራት ከሚያስፈልጋት ሁለት ዓይነት *"አንድነት"* የመጀመሪያው፣ መሠረታዊ የሆነው *"የመንፈስ አንድነት"* ነው። እነዚህ ሁለቱ፣ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ካልሄዱ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምዕመናኑ መካከል መከፋፈል ሊያመጣ ይችላል። *"የመንፈስ አንድነት"* ሳይኖራቸው *"የእምነት አንድነት"* ሊኖራቸው አይችልም። ሐዋርያው ጳውሎስ ***"በሰላም ተሳስራችሁ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኘውን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ"*** (ኤፌ. 4፥3) ሲል፣ ስለ *"መንፈስ አንድነታቸው"* መናገሩ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህን ዓይነት አንድነት የሚፈጠረው አንድ አማኝ ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበልና በክርስቶስ አካል ውስጥ እንደገና ሲወለድ ነው። ይሄም የአማኞች አንድነት ጤናማ ሆኖ እንዲያድግና እንዲጠነክር በቂ የሆነ እንክብካቤ ያስፈልገዋል። ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አባል በመንፈሳዊ ሕይወቱና እንዲሁም በአገልግሎቱ ማደግ የሚችለው ከሌሎች አማኞች ጋር በሚኖረው የተቀራረበ ግንኙነትና አንድነት ነው። ይህንን እውነት የተረዳው ሐዋርያው ጳውሎስ፣ *"ይህን ሕብረት ለመጠበቅ ትጉ"* በማለት አማኞችን አጥብቆ ያሳስባል። እግዚአብሔር ክቡር የሆነ ዓላማው እንዲፈጸም፣ የክርስቶስ የአካሉ ክፍሎች የመንፈስ አንድነት እንዲኖራቸው ያሳስባል። ቤተ ክርስቲያን በዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ክብር በሙላት ለማንጸባረቅ የምትችለው፣ የመንፈስ አንድነት ሲኖራት ብቻ ነው። በዘመናችን ያሉ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት መድረስ ከሚገባቸው መንፈሳዊ ደረጃ መድረስ ያልቻሉበት፣ ለዕድገታቸው ትልቅ መሰናክል የሆነባቸው ዋነኛ ምክንያት፣ በምዕመናኑ መካከል እውነተኛ *"የመንፈስ አንድነት"* የማይታይ በመሆኑ ነው። በየሳምንቱ ለአምልኮት መሰብሰብ፣ መዘመርና መጸለይ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ *"የመንፈስ አንድነት"* አለ ማለት እንዳልሆነ ልብ ማለት አለብን።

ከቀድሞ መንፈሳዊ አባቶች መካከል "ተርቱልያን" የተባለው ሰው፣ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ አንድነታቸውን እንዲጠብቁ ለማደፋፈር፣

- *"ደካማ ለሆኑት የምናደርገው እንክብካቤ፣ ፍቅራችንና ርህራሄያችንን በሥራ ስንገልጽ፣ በሚጠሉን ሰዎች ዘንድ እንኳን ያ መታወቂያችን ይሆናል"* አለ።

  አማኝ ያልሆነው ሉሲያን የተባለው ግሪካዊ ጸሐፊ ደግሞ፣ ክርስቲያኖች ያላቸውን አንድነትና ፍቅር ከተመለከተ በኋላ በማድነቅ እንዲህ አለ፡-

- *"የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች እርስ በርሳቸው ያላቸው ፍቅር፣ በችግር ጊዜ አንዱ ለሌላው የሚሰጠው ዕርዳታ እጅግ በጣም ያስደንቃል። ሕግ አውጪአቸው የሆነው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እየተባለ የሚጠራው ሰው፥ 'ወንድማማቾች ናችሁ... ብሎ አንዴ አዕምሯቸው ውስጥ እንዲቀረጽ ስላደረገ፣ እርስ በርሳቸው በጣም ይዋደዳሉ። አንዱ ለሌላው የማይሰጠው ምንም ነገር የለም። ሌላው ቀርቶ አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት አንዱ ለሌላው ለመሞት እንኳ ፈቃደኞች ናቸው።"*



በዘመናት በዚህ ዓይነት ዓለምን ያስደነቀው የአማኞች አንድነትና ፍቅር፣ በአሁኑ ዘመን ባለነው አማኞች ሕይወት ወይም ኅብረት ውስጥ ይታይ ይሆን?

## 1.2. የእምነት አንድነት

በአማኞች ሕብረት ውስጥ መታየት ያለበት ሁለተኛው፣ *"የእምነት አንድነት"* ነው። ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የተለያየ የአገልግሎትን ስጦታ የሚሰጠው አማኞች አገልግሎታቸውን እንዲፈጽሙበት ብቻ ሳይሆን፣ የእምነት አንድነታቸውን እንዲጠብቁ መሆኑን ጳውሎስ ሲገልጽ፣ ***"ይህም የሚሆነው፣ ሁላችንም የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣትና ሙሉ ሰው በመሆን፣ በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስክንደርስ ነው"*** ይላል (ኤፌ. 4፥13)። *በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አማኞች፥ አንድ መሆን እንዲችሉ አንድ ዓይነት የሆነ "ዶክትሪን" እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።* ጳውሎስም በማስተማር የተጋው ይህን ዓይነቱን *"የእምነት አንድነት"* ለመጠበቅ ነበር (ገላት. 2፥6-12)። ለዚሁ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ የተጠቀሰው የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ነው። በአንድ ወቅት አንዳንድ አማኞች የተለያየ የእምነት አቋም በመያዛቸው፣ በመካከላቸው የነበረውን አንድነት ሊያበላሽ ይችላል የሚል ፍርሃት ተፈጥሮ ነበር። ከአማኞች መካከል አንዳንዶቹ በወቅቱ ጠንካራ የሆነ የራሳቸው የሆነ የእምነት አቋም ቢኖራቸውም፣ ከራሳ ቸው አቋም የበለጠ ለእግዚአብሔር ቃል ሕይወታቸውን ያስገዙ በመሆናቸው የነበራቸው የእምነት ልዩነት አንድነታቸውን ለማፍረስ ጉልበት አልነበረውም። "የእምነት አንድነት የለንም" በማለት ተለያይተውና ተከፋፍለው በመሄድ ፈንታ፣ የነበራቸውን የእምነት ልዩነት ለማስታረቅ፣ ከመንፈሳዊ መሪዎቻቸው ጋር ለመወያየት አስፈላጊውን እርምጃ ወሰዱ። አንዳንዶቹ በወቅቱ በአንዳንድ ነጥብ ላይ የራሳቸው የሆነ ጠንካራ የእምነት አቋም የያዙ ቢሆኑም፣ ቀና መንፈስ (ልብ)፣ እንዲሁም "የመንፈስ አንድነታቸውን" ለመጠበቅ ጽኑ ፍላጎት ስለነበራቸው፥ መጨረሻ ላይ ውይይታቸው መልካም ፍሬ አፍርቶ ሁሉም ወደተስማማበት "የእምነት አንድነት" መምጣት ቻሉ (የሐዋ. 15)። በእኛም ዘመን ያለነው አማኞች በዚህ ዓይነት እርስ በርሳችን በቅንነት ከተወያየን፣ በመካከላችን የሚፈጠሩትን የእምነት ልዩነቶቻችንን አጥፍተን፣ ወደ አንድ "የእምነት አንድነት" ልንደርስ (ልንመጣ) እንደምንችል ግልጽ ነው።

*"የእምነት አንድነት"* ስንል፣ *"የእምነት መመሪያንም"* (Doctrine) ያጠቃልላል። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ እውነተኛ የሆኑ አማኞች የእምነት መመሪያቸው የሁሉም ምንም ያህል የተለያየ ቢሆን፣ *"የመንፈስን አንድነት"* ለመጠበቅ አማኞች ሁሉ ከተጉ፣ ወደ

*"እምነት አንድነት ሊደርሱ ይችላሉ"* ብሎ ያምናል። እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚኖራቸው "የመንፈስም ሆነ የእምነት አንድነት" ለመጠበቅ፣ አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው የተቀራረበ ግንኙነት ወሳኝነት አለው። በዘመናችን በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በምዕመናኑ መካከል ብዙ መከፋፈልና መለያየት ጎልቶ የሚታይበት ትልቁ ምክንያት አማኞች የእምነት አንድነት በማጣታቸው ምክንያት ብቻ ሳይሆን፣ የሚያምኑትን በትክክል የማያውቁ፣ እንዲሁም የራሳቸው የሆነ የእምነት አቋም የሌላቸው በመሆኑ ነው። ብዙዎቹ በቀላሉ ወደ እንግዳ ትምህርት የሚሳቡ፣ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑንና አለመሆኑን በጥንቃቄ ሳይመረምሩ የሰሙትን ሁሉ "አሜን!" ብለው የሚቀበሉ ናቸው። የዚህም ትልቁና ዋናው ምክንያት፣ በቂ የሆነ የቃሉ ዕውቀት ስለሌላቸው ነው። የቃሉ ዕውቀትም የማይኖራቸው፣ በግላቸው ቃሉን ለማጥናት ጥረት ስለማያደርጉ፣ እንዲሁም ብቃት ያላቸው አስተማሪዎች የሌላቸው በመሆኑ ነው።

ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት ኃያሉ አምላክ፣ እግዚአብሔር ራሱ ስለሆነ፣ የሰው ኃይልም ሆነ፣ የፖለቲካ ቅንጅት ሊያፈርሳት ወይም ሊያጠፉት አይችልም። ስለዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ *"...በዚህች ዓለት ቤተ ክርስቲያኔን አሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆች አይችሏትም..."* (ማቴ. 16፥16-19) ያለው። ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱ የሆኑትን ለመውሰድ አንድ ቀን እንደ ገና ወደ ዓለም ሲመጣ፣ ተዘጋጅተው እንዲጠብቁት፣ እግዚአብሔር የዓለምን ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በዓለም ዙሪያ ብዙዎችን ወደ ራሱ እየጠራ ነው። በቅርብ ጊዜ ለሚፈጸመው ጋብቻ፣ እግዚአብሔር የክርስቶስ ሙሽራ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያኑን እያዘጋጃት ነው። በዚህ በመጨረሻው ዘመን፣ ቤተ ክርስቲያን እንደሚገባው ተዘጋጅታ ክርስቶስን እንድትጠብቀው ለመርዳት፣ መንፈስ ቅዱስ ከምንጊዜውም የበለጠ በኃይል እየተንቀሳቀሰና እየሠራ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ መጥቶ የሚወስዳት ሙሽራ የተዘጋጀች፣ በክብር የተሞላች፣ ሰማያዊ የሆነውን የባሏን መልክና ውበት የምታንጸባርቅ መሆን አለባት። ሙሽራው ከመምጣቱ በፊት፣ ትልቅ ዝግጅት በሚደረግበት በአሁኑ ዘመን፣ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ እግዚአብሔር መንግሥቱን ለማስፋት እንደ መሣሪያው አድርጎ እንዲጠቀምባት፣ ኃይልና ጥንካሬ ያላት፣ እንዲሁም መሆን የምትችለውን እንድትሆን ይጠብቅባታል። ቤተ ክርስቲያን ይህንን የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም ኃይልና ጉልበት ማግኘት የምትችለው፣ የአካሉ ክፍሎች የሆኑ በአንድነት መያያዝ የቻሉ እንደ ሆነ ብቻ ነው። የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለማሳየት ጳውሎስ "የሰውን አካል" እንደ ምሳሌ አድርጎ ያቀርባል። *"አካልም አንድ እንደ ሆነ፥ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት፥ ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው"* (1 ቆሮ. 12፥12) ይላል።

አንድ ሰው በሥጋ የአንድ ቤተሰብ አባል መሆን የሚችለው፣ ከዚያ ቤተሰብ "በመወለድ" ወይም "በማደጎ" (adoption) ነው። "የክርስቶስ አካል በሆነው ቤተ ክርስቲያን ውስጥስ፥ የዚያ አካል ክፍል መሆን የሚቻለው እንዴት ነው?" በየሳምንቱ ቤተ ክርስቲያን በመሄድና በቤተ ክርስቲያን መዝገብ ውስጥ ስሙ በመጻፉ እንዳልሆነ እናውቃለን። የዚህ ቤተሰብ የአካል ክፍል (ብልት) መሆን የሚቻለው፣ በክርስቶስ በኩል "ደኅንነትን" በማግኘትና እንዲሁም በአንድ መንፈስ በመጠመቅ ብቻ ነው። ሰው የቤተ ክርስቲያን አካል ክፍል (አባል) እንዴት መሆን እንደሚችል ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ፥ *"...እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል"* ይላል (1 ቆሮ. 12፥13)። "ሁላችን" ሲል፣ በክርስቶስ አምነው የዳኑትን መጥቀሱ እንደሆነ ግልጽ ነው። ክርስቶስ ሁላችንንም የጠራን በጅምላ ሳይሆን፣ በግል ወይም በነፍስ ወከፍ ነው። ይሁን እንጂ፥ ብቻችንን እየኖርን በእምነታችን እንድናድግ አይደለም። "እጅ" ከሌሎች የሰውነት ክፍሎች (ብልቶች) ተገንጥሎ ለብቻው ማደግ እንደማይችለው ሁሉ፣ አማኞችም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው መቆምም ሆነ ማደግ የሚችሉት፣ ራስ ከሆነው ክርስቶስ ጋር፣ እንዲሁም የአካሉ ክፍሎች (ብልቶች) ከሆኑት ሌሎች አማኞች ጋር የተያያዙ ከሆኑ ብቻ ነው። አንድ የሰውነት ክፍል ከአካሉ ተቆርጦ ከወደቀ፣ የማያድግ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሕይወት እንደማይኖረው የታወቀ ነው። ልክ እንደዚሁ አማኞችም እርስ በርሳቸው ካልተያያዙ፣ በሕይወት መኖርም ሆነ ማደግ አይችሉም። መንፈስ ቅዱስ አማኞች እንደ ገና እንዲወለዱ ካደረገ በኋላ፥ ሙሉው አካል እንዲታነጽ ለእያንዳንዱ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና እንዲሁም ስጦታውን የሚጠቀምበት የአገልግሎት ሥፍራ (መስክ) ይሰጠዋል።



ቤተ ክርስቲያን በሰው ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተመሠረተች ናት። በውስጧ ያሉት ክፍሎችም (ብልቶች) የተለያዩ ቢሆኑም ለየብቻቸው ራሳቸውን ችለው የቆሙ አይደሉም። ነገር ግን በአንድ አካል ውስጥ እርስ በርሳቸው የተያያዙ ናቸው። *አንድ አካል የሆኑትም ምድራዊ በሆነው ድርጅታዊ መዋቅር ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ነው።* አንድነታቸውም የሚገለጸው ቤተ ክርስቲያን በመሄዳቸው፥ በአምልኮት ወቅት ጎን ለጎን በመቀመጣቸው፥ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ አብሮ በመብላትና አብሮ በመጠጣት አይደለም። የአማኞች አንድነት የተመሠረተው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ነው። ክርስቲያኖች አንድ አካል ቢሆኑም፥ ራሳቸውን ከሌላው አካል ገንጥለው ለብቻቸው የመሆን ዝንባሌ ሊኖራቸው እንደሚችል የታወቀ ነው። አማኞች አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ፥ ጎን ለጎን እየተቀመጡ፥ ሰላምታ እየተለዋወጡ፥ ልባቸው ግን የተራራቀ ሊሆን ይችላል። ወይም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ልባቸውን ከፍተው፣ ለብዙዎች ግን ልባቸው የተዘጋ ሊሆን ይችላል። ይህ ሲሆን፥ አካሉ እንደሚገባው መሥራትና ማደግ እንደማይችል ግልጽ ነው። ለአካሉ ዕድገትም ሆነ ጤንነት፣ የአካሉ ክፍሎች እርስ በርሳቸው መፈላለግና መያያዝ አለባቸው። ለሁለተኛው አዳም (ክርስቶስ) ጥላ እንዲሆን፣ የመጀመሪያውን ሰው (አዳምን) እግዚአብሔር በራሱ እጅ፣ ከምድር አፈር ወስዶ ረቂቅ የሆነና ብዙ ብልቶች ያሉት አድርጎ በጥንቃቄ ሠራው (ዘፍ. 2፥7)። ልዩ ልዩ ብልቶች፣ ጡንቻዎች፣ ጅማቶችና አጥንቶች፣ ከሌሎች የሰውነት ክፍሎች ጋር በመያያዝ እያንዳንዳቸው ለአካሉ ዕድገትና ጤንነት፣ እንዲሁም ጥቅም እንዲሰጡ አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብ

ሔር የመጀመሪያውን ሰው የፈጠረው፣ ኃጢአት የማያበላሸው፣ በሽታም ሆነ ሞት የማይነካው አድርጎ ነው። ሁለተኛው አዳም (ክርስቶስ) ሥጋ ለብሶ በመካከላችን ያደረውም፣ የለበሰው አካል ፍጹምና ኃጢአት የሌለበት፣ የማይታየውን የእግዚአብሔርን አምሳል (መልክ) ይዞ ነው። ጳውሎስ *"...እርሱ የማይታየው አምላክ አምሳል ነው፤ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው"* (ቆላ. 1፥15) ይለዋል።

ቤተ ክርስቲያን ምድራዊ ድርጅት ሳትሆን፥ "ኮይኖኒያ" (Koinonia)--የአማኞች ሕብረት ወይም አንድነትን የምታሳይ ናት። በውስጧ ያሉት የአካሉ ክፍሎች (ብልቶች)፣ ሕብረታቸው ምን ዓይነት መልክና አቋም መያዝ እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ሥፍራ ተጠቅሶ እናነባለን፣

*እርስ በርሳቸው ተስማምተው በሰላም እንዲኖሩ (የማር. 9፥50)፤*

*በክርስቶስ አንድ አካል እንዲሆኑ (ሮሜ 12፥5)፤*

*እርስ በርሳቸው እንዲከባበሩ (ሮሜ 12፥10)፤*

*እርስ በርሳቸው በአንድ አሳብ ተስማምተው እንዲኖሩ (ሮሜ 12፥16)፤*

*አንዱ በሌላው ላይ ሳይፈርድ እንዲኖር (ሮሜ 14፥13)፤*

*እርስ በርሳቸው እንዲተናነጹ (ሮሜ 14፥19)፤*

*አንድ ልብ እንዲሆኑ (ሮሜ 15፥5)፤*

*አንዱ ሌላውን እንዲያስብ (ዕብ. 10፥25)፤*

*እርስ በርሳቸው እንዳይተማሙ (ያዕ. 4፥11)፤*

*እርስ በርሳቸው በኃጢአታቸው እንዲናዘዙ (ያዕ. 5፥16)፤*

*እርስ በርሳቸው እንግድነት እንዲቀባበሉ (1 ጴጥ. 4፥9)፤*

*አንዱ ሌላውን እንዲያገለግል (1 ጴጥ. 5፥5)፤*

*እርስ በርሳቸው እውነት እንዲናገሩ (ኤፌ. 4፥25)*

*እርስ በርሳቸው ደጎችና አዛኞች እንዲሆኑ (ኤፌ 4፥32) ይመክራል።*

እማኞች ምን ዓይነት አንድነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ከላይ እንዳየነው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ቢናገርም፣ ጥንትም ሆነ በዘመናችን የምናያቸው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ግን ያንን መስለው አይታዩም። እርስ በርስ በመከባበር ፈንታ አንዱ ሌላውን ዝቅ ሲያደርግ፣ አንዱ ለሌላው ደግና እዛኝ በመሆን ፈንታ አንዱ በሌላው ሲጨክን፣ እርስ በርሳቸው እውነት መነጋገር ሲገባቸው አንዱ ሌላውን ሲዋሽ ወዘተ.



እናያለን። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ምን እንደሆነች ለመግለጽ የተጠቀሱት ምሳሌዎች ሁሉ "አንድነቷን" የሚያመለክቱ ናቸው። ቤተ ክርስቲያን፥

*አንድ "ሙሽራ" እንዳላት "ሙሽሪት" ናት።*

*አንድ እረኛ እንዳላት "መንጋ" ናት።*

*አንድ ንጉሥ እንዳላት አንድ መንግሥት ናት።*

*አንድ አባት እንዳላት አንድ ቤተሰብ ናት።*

*አንድ መሠረት አንዳላት "ሕንጻ" ናት።*

*አንድ ራስ አንዳላት "አንድ አካል" ናት።*[2]

ቤተ ክርስቲያን እንደ ዓለማዊ ድርጅት፣ እንዲሁም በደረጃና በማዕረግ የተከፋፈለ መዋቅር ያላት እንዳልሆነች የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ይናገራል። አማኞች በክርስቶስ ፊት ሁሉም እኩል ናቸው። እግዚአብሔር ሁሉንም በነፍስ ወከፍ፣ ለማንም ሳያደላና ሳያበላልጥ ሁሉንም እኩል ይወዳቸዋል። በተለያየ መንገድና ሁኔታ ሁሉንም ለክብሩ ይጠቀምባቸዋል። ለጥቂቶች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም አማኞች እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ዓላማ አለው። ስለዚህ፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ "አያስፈልግም" ወይም "አይጠቅምም" በማለት እግዚአብሔር ገለል የሚያደርገው የአካል ክፍል (አማኝ) የለም። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ገና ሕጻን የሆነውም፣ በእምነቱ ገና ያላደገውም፥ ደካማውም ሆነ ብርቱ የሆነውም፥ በሕይወት ለመቆየትም ሆነ ለማደግ እርስ በርሱ የግድ መያዝ አለበት (1 ቆሮ. 3፥16፥ 1 ዮሐ. 2፥12-14) "አሁን በመንፈሳዊ ሕይወቴ አድጌአለሁና ሌሎች አማኞች አያስፈልጉኝም" ማለት የሚችል ማንም የለም።

## 2. የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ "የአንድነቷ" መሠረት ነው

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን ለመግለጽ ከተጠቀሱት ምሳሌዎች መካከል አንደኛው *"አካል"፥ በግሪክ ቋንቋ "ሶማ" (Soma)* የሚለው ቃል ነው። ይሄ *"አካል" ወይም ""ሶማ" (Soma)* የሚለውን ቃል ሐዋርያው ጳውሎስ አዲስ ኪዳን ውስጥ ከ30 ጊዜ በላይ ሲጠቀምበት፥ ከዚህ ውስጥ ግማሹን *"የሰውን አካል"* ለመግለጽ ሲሆን፥ የተቀረውን ግን ቤተ ክርስቲያንን ለመግለጽ የተጠቀመበት ቃል ነው።[3] ጳውሎስ ቤተ

---

[2] Scheidler, Bill. The New Testament Church and Its Ministries. Bible Press, Portland, Oregon, 1980, p. 28.

[3] Getz, A. Gene. Sharpening The Focus of the Church. Scripture Publications, Inc. 1984, p. 183.

ክርስቲያንን ልዩ ልዩ ክፍሎች ያሏት *"አንድ አካል"*ነች ሲል፥ የክርስቲያኖችን አንድነት ለማሳየት ነው። ቤተ ክርስቲያን አንድ ራስ፥ እንዲሁም ብዙ ክፍሎች (ብልቶች) ያሏት የክርስቶስ አካል ነች። የዚህ አካል ራስም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጳውሎስ *"ሁሉንም ነገር ከሥልጣኑ ሥር አድርጎ አስገዛለት፤ በቤተ ክርስቲያንም ከሁሉ በላይ እንዲሆን ራስ አደረገው። ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካልና የእርሱ ሙላት ናት፤ እርሱም ሁሉን በሙሉ የሚሞላ ነው"*(ኤፌ. 1፥22-23) ይለዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ "ራስ" ከሆነ፣ ሥልጣን ሁሉ የእርሱ ነው ማለት ነው። ሥልጣን ሁሉ የእርሱ ከሆነ፥ አካልን የሚመራ፥ ወይም የሚቆጣጠር ሰው ሳይሆን ክርስቶስ ራሱ ነው። ከሰው የአካል ክፍሎች ውስጥ "ከራስ" (ከአንጎል) ትዕዛዝን ሳይቀበል በራሱ ፈቃድና ሥልጣን የሚንቀሳቀስ አንድም የሰውነት ክፍል (ብልት) የለም። በክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አንዳንድ አማኞች ግን፥ በሕይወታቸውም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርስቶሳዊ አመራር ሳይኖር፣ እንዲሁም ከእርሱ ትእዛዝ ሳይቀበሉ አገልግሎት ለመስጠት በራሳቸው ፈቃድና ፍላጎት የሚንቀሳቀሱ እንዳሉ የታወቀ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ከሆነ፣ አማኞች በሕይወታቸውም ሆነ በቤተ ክርስቲያናቸው ሙሉ የሆነ ሥልጣን ሊሰጡት ይገባል። ሙሉ ሥልጣን ከሰጡት ያዘዛቸውን ሁሉ ያለማመንታት ያደርጋሉ፤ እንዲሁም "አድርጉ" ያላላቸውን እያደርጉም። የሰው አካል የሚንቀሳቀሰው ከአንጎል የሚተላለፍለትን ትእዛዝ እየሰማ እንደሆነ ከላይ ገልጸናል። ለምሳሌ የወደቀውን ዕቃ እጅ እንዲያነሳ ከአንጎል ትዕዛዝ ሲደርሰው፣ "እጅ" የተሰጠውን ትዕዛዝ ይፈጽማል። በበሽታ ምክንያት እጅ ሽባ (የማይሠራ) ከሆነ ግን፣ ትዕዛዙን ቢሰማም፣ በሽባነቱ ምክንያት የታዘዘውን ትእዛዝ መፈጸም አይሆንለትም። ልክ እንደዚሁ፣ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ (አንጎል) ስለሆነ፣ ራሥ ከሆነው ክርስቶስ የሚሰጠውን ማንኛውንም ዓይነት ትዕዛዝ የአካሉ ክፍሎች የማያደርጉ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያንቲቱ አካለ ስንኩል (ሽባ) የሆነች ቤተ ክርስቲያን ናት ማለት ነው። የሰርዴስን ቤተ ክርስቲያን *"...በስም ሕያው ነህ፤ ነገር ግን ሞተሃል"* ያላት ለዚህ ነው (ራዕ. 3፥1)። ዛሬ የክርስቶስን ስም ቢይዙም፣ መንፈሳዊ ሞት የሞቱ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በዓለም ዙሪያ እንዳሉ የታወቀ ነው። የሃይማኖት ሥርዓትና ደንብ በመፈጸማቸው ብቻ፣ በውስጣቸው ሕይወት አለ ማለት አይደለም። በቁጥር ቢበዙ አድገዋል ማለት አይደለም። ሙት የሆነ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ሊዘራ የሚችልበት ያለው አንድ መንገድ ብቻ ነው። ይኸውም ሕይወትና ትንሳኤ ወደሚሰጠው ህያው ጌታ እንደ ገና በመመለስ ብቻ ነው።

የአካሉ ክፍሎች (ብልቶች) በሕይወት ለመቆየት እርስ በርሳቸው መያያዝ እንዳለባቸው ሁሉ፥ ቤተ ክርስቲያንም ሕይወት እንዲኖራት ምዕመናኖቿ እርስ በርሳቸው የተያያዙ መሆን አለባቸው። ከአካል ክፍሎች መካከል አንዱን "ትልቅ ነው፤ ችሎታ ያለው ነው፤ ለብቻው መቆም ይችላል" ብለን ከተያያዘበት አካል ቆርጠን በማውጣት የተመደበ



ለትን አገልግሎት በተናጠል ለብቻው እንዲሰጥ ማድረግ አይቻልም። ለምሳሌ፥ እጅ ከሌላው ሰውነት ተለይቶ ከተቆረጠ፥ ምንም ያህል ብርቱና ጠንካራ ቢሆን፥ ይሞታል እንጂ በሕይወት መቆየት አይችልም። የሰው እካል በሕይወት መኖር የሚችለው፣ የአካሉ ክፍሎች (ብልቶች) ሁሉ በአንድ ላይ መያያዝ ሲችሉ ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያንም ሕይወት ዋጋት ማደግ የምትችለው፣ አባሎቿ እርስ በርስ ከተያያዙ ብቻ ነው። የሚያያይዛቸውም ሌላ ነገር ሳይሆን "ራስ" ከሆነው ከክርስቶስ የሚፈልቀው ሕይወት ብቻ ነው። እጅ ቢቆረጥ "ራሥ" እስካለ ድረስ፥ የተቀረው የሰው አካል አይሞትም። ራስ ከተቆረጥ ግን እጅም ሆነ ሌሎች የሰውነት ክፍሎች እርስ በርሳቸው የተያያዙ ቢሆኑም አንኳ ሕይወት አይኖራቸውም። ልክ እንደዚሁ ቤተ ክርስቲያንም ያለ ክርስቶስ ሕይወት አይኖራትም።

ከሰውነት ክፍሎች (ብልቶች) መካከል አንደኛው በአደጋ፣ ወይም በተለያየ ምክንያት ሊቆስል፣ ሊጎዳ ይችላል። የተጎዳው አንዱ የሰውነት ክፍል ቢሆንም፣ ሌሎች ክፍሎች ጉዳቱ አይሰማቸውም ማለት አይደለም። ሌሎች የሰውነት ክፍሎች የተጎዳውን ክፍል ለመርዳት ሲሞክሩ ይታያሉ። ለምሳሌ "እጅ" በእሳት ቢቃጠል፣ አንጎል ለሌሎች የሰውነት ክፍሎች እጅ መቃጠሉን አስታውቆ አስፈላጊውን እርዳታ እንዲያደርጉለት ትእዛዝ ይሰጣል። የተቃጠለው እጅ ላይ በረዶ መያዝ ሕመሙን ስለሚቀንስው፣ "እግር" በረዶ ወዳለበት ሌሎችን ክፍሎች ተሸክሞ መሄድ ይጀመራል። ሌላው "እጅ" በረዶውን ከማቀዝቀዣ ያወጣል፣ "ዐይን" በረዶው ያለበትን ቦታ ያያል... በዚህ ዓይነት የሚመለከታቸው የሰውነት ክፍሎች ሁሉም ተባብረው "የተቃጠለውን እጅ" ህመሙ እንዲቀንስለት ያደርጋሉ። በቤተ ክርስቲያንም ከምዕመናን መካከል አንዱ ቢጎዳ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ሁሉም ተባብረው ያንን የተጎዳውን ምዕመን ሊረዱት ይገባል። በዘመኗ ቤተ ክርስቲያን የሚታየው ግን ይህን ዓይነት ሳይሆን፣ ሌላው ቀርቶ በአንዳንድ ነገር ሳይስማሙ ቢቀሩ እንኳን ልዩነታቸውን ለማስታረቅ በመሞከር ፈንታ፣ ያንን ሕብረት ትተው ሌላ ሕብረት ይጀምራሉ። ችግሩ ሌላ ሕብረት (ቤተ ክርስቲያን) መጀመራቸው ብቻ ሳይሆን፣ እንዱ የሌላው ጠላት ሆኖ የሚጟቀሱና የጎሪጥ የሚተያዩ መሆናቸው ነው። በዚህ ዓይነት *"...አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ፤ አንድ እምነትና አንድ ጥምቀት አለ፤ ከሁሉም በላይ የሆነ በሁሉም የሚኖር የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ"* (ኤፌ. 4፥4-6) የሚለውን ቃል አምነው የተቀበሉ አይመስሉም። ለሁለት የተለያየ ጌታ የሚሠሩ፣ ሁለት የተለያየ አምላክ የሚያመልኩ ይመስላሉ። የሚያሳዝነው፣ ያሉበት መጥፎ ሁኔታ ትንሽም ሳይቆረቁራቸው ሁለቱም "በቁጥር ለማደግ" ሲታገሉ የሚታዩ መሆናቸው ነው። ቁጥራቸው ካደገ፣ ብዙ ሰዎች መሰብሰብ ከቻሉ፣ ቀደም ሲል ያበሳጮት (ያጠፉት) ተሰርዞ፣ እግዚአብሔር "ጎሽ የእኔ ልጆች፣ ቀልጣፋ ሆናችሁ ብዙ ነፍሳት አመጣችሁልኝ" የሚላቸው መስሎ ይሰማቸው ይሆን?

የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በጤናማ መንገድ እንዳታድግ እንቅፋት ሊፈጥሩባት የሚችሉ ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከብዙዎቹ መካከል፣ በጣም አሳሳቢ የሆኑትን ሁለት ሁኔታዎችን ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ በጻፈው በመጀመሪያ መልዕ

ክቱ ገልጿቸዋል። *"አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች ብንሆን፤ ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብን ሆን፤ እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አንዱን መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል"* (1 ቆሮ. 12፥14) ይላል። ይህን ሲል የበላይ ነትና የዝቅተኛነት ስሜት በምዕመናኑ መካከል በመግባት ለአካሉ ዕድገትና ጤንነት እን ቅፋት እንዳይሆን ስማሳሰብ ነው።

## 2.1. የዝቅተኛነት ስሜት

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "ጠቃሚ አይደለሁም... አላስፈልግም..." በማለት ራሳቸ ውን ከአካሉ ገለል ስማድረግ የሚፈልጉ አንዳንድ አማኞች አሉ። *"እግር እኔ እጅ ስላል ሆንሁ የአካል ክፍል አይደለሁም" ቢል ይህን በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን? ጆሮም 'እኔ ዐይን ስላልሆንሁ የአካል ክፍል አይደለሁም" ቢል ይህን በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን?"* (1 ቆሮ. 12፥15-16) በማለት ጳውሎስ ይጠይቃል። አንዳንድ ክርስቲያኖች በጣም ጎልቶ የሚታይ ስጦታ ካላቸው አማኞች ጋር ራሳቸውን በማወዳደር ራሳቸውን ዋጋ እንደሌላቸው አድርገው የሚቆጥሩ አሉ። ራሳችንን ከሌሎች ጋር የምና ወዳድር ሲሆን፣ ከሌላው ተሽለን ራሳችንን ካላገኘን፣ ጥቅም እንዳለን ሰዎች አድርገን ራሳችንን መቀበል ያቅተናል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ራስን ከሌላው አማኝ ጋር ማወዳ ደር፣ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን ለመገንባት የሚሰጠውን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ስራሳችን ጥቅምና ስስማችን መጠሪያ ስማድረግ እንድንመኝ እንፈተናስን። ከበላይነትም ሆነ ከበታችነት ስሜት ለመዳን፣ ለእያንዳንዱ የአካሉ ክፍሎች የተሰጠውን ልዩ ልዩ ስጦታ ስይቶ ማወቅ ይጠቅማል። ስጦታው የሚሰጠው አማኙ ራሱን የሚጠቅምበት ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያንን ስማነጽ እንደሆነ በአሁኑ ዘመን ብዙዎች የተረዱት አይመስልም። የዝቅተኛነትን ስሜት ስመግለጽ *"ግሬግን ኦገዴን፣ ጎርደን ኮስቢ"* የተባለው ጸሀፊ ከጻፈው መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ሲል ይጠቅሳል፥

> *"እግዚአብሔር እያንዳንዳችንን ሲፈጥረን የተለያየን እንጂ አንድ ዓይነት አድርጎ አልፈ ጠረንም--ፍጹም ድንቅ፤ እርሱን ደስ ማሰኘት እንድንችል አድርጎ ፈጠረን። አንዳችን ከሌ ላው የተለየን፤ በአካሉ ውስጥ ሁላችንም የተለያየ ስፍራ (አገልግሎት) እንዲኖረን፤ እን ዲሁም ለተመደብንበት አገልግሎት ጠቃሚዎች እንድንሆን አድርጎ ፈጥሮናል። ስመግ ለጽ አስቸጋሪና ልዩ የሆነውን እኛነታችንን፣ እንዲሁም አገልግሎታችንን እንደሚገባው መፈጸም እንድንችል ብቃትን የሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው። በክርስቶስ አካል ውስጥ ሥፍራ እንዲኖረን ሲጠራን፤ አገልግሎታችንን መፈጸም የሚያስችለንን ልዩ የሆነ ስጦታ ሰጥቶን ነው፤ ያለዚያ ስጦታ ለአካሉ ዕድገት ጠቃሚዎች መሆን አንችልም።"*[4]

## 2.2. የበላይነት ስሜት

[4] Ogden, Greg. The New Reformation, Zondervan Publishing House, Grand Rapids, Michigan, c1990.



አካሉን የሚጎዳ ወይም ጤና የሚነባ ሌላው ጳውሎስ የገለጸው፣ "የበላይነት ስሜት" ነው። በራሳቸው ብቁ የሆኑ፣ ሌሎች የአካሉ ክፍሎች በሕይወታቸው የሚያስፈልጋቸው መስሎ የማይሰማቸው፣ ወይም ለብቻቸው ማደግ የሚችሉ የሚመስላቸው እንዳንድ አማኞች አሉ። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ *"ዐይን እጅን 'አታስፈልገኝም" ሊለው አይችልም፤ ራስም እግርን 'አታስፈልገኝም' ሊለው አይችልም። እንዲያውም ደካማ የሚመስሉት የአካል ብልቶች እጅግ አስፈላጊ ናቸው"* ያለው (1 ቆሮ. 12፥21)። 'እታስፈልገኝም' የሚለው አባባል፣ "ለብቻዬ ብቁ ነኝ" የሚል፣ የበላይነት ስሜትን የሚያንጸባርቅ ነው። ይሁን እንጂ፣ ምንም ያህል ጠንካራ የሆነ ቢመስለው፣ ለብቻው መኖርም ሆነ ማደግ የሚችል የለም። ሌሎች አማኞች ያስፈልጉታል። በመንፈሳዊ ሕይወታችን ማደግ የምንችለው ከሌሎች የአካል ክፍሎች ጋር ስንያያዝ ብቻ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል።

## 3. የአማኞች አንድነት ምንድነው?

አማኞች እርስ በርሳቸው እንደሚገባው ተዋውቀውና የበሰጠ ተቀራርበው፥ እርስ በርሳቸው ተቀባብለው መኖር እንዲችሉ፥ እንዲሁም በመካከላቸው የመተማመን መንፈስ እንዲፈጠር፥ አንዱ ስስ ሌላው ዕድገትና በጎነት ማሰብ አለበት። የክርስቲያን ሕብረት ሊፈጠር የሚችለው፥ አማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት በመፈለግ ሁሉም ድርሻውን መፈጸም ሲችል ነው። *አብሮ መሰብሰብና በክርስትና ሕብረት ውስጥ መሆን አንድ ዓይ ነት አይደለም።* በክርስትና ሕብረት ውስጥ መሆን፥ ጥሩ የሆኑ ጓደኞችን ከማፍራት በላይ ነው።

- *የክርስቲያን ሕብረት ማለት፣ የአንዱ አካል ክፍል መሆን፥ በክርስቶስ ውስጥ አንድ ዓይነት ዓላማ ካላቸውና ስዚህ አንድነት ከተሰጡ አማኞች ጋር መተሣሰር ማለት ነው።*

የክርስቲያን ሕብረት ማስት በተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ መገኘት ማለት እይደለም። ቤተ ክርስቲያን በምታካሂደው ስብሰባ ሁሉ እየተገኙ፥ በምታካሂዳቸው ፕሮግራሞች ሁሉ ተካፋይ እየሆኑ፥ ነገር ግን ከክርስቲያኖች ሕብረት ጋር የማይያያዙ፥ ወይም ከሌሎች አማኞች ጋር አንድ ልብ መሆን የሚያቅታቸው አንዳንድ አማኞች ሊኖሩ እንደሚችሉ የታወቀ ነው።

- *የክርስቲያን ሕብረት ማለት፣ በውስጡ ያሉት ሰዎች፥ አንድ ዓይነት ዓላማ፥ ተመሳሳይ የሆነ ግብ ወይም መድረሻ ያላቸውና እንዲሁም አንድ ለመሆን እርስ በርሳቸው የተያያዙ ወይም የታነጹ ማለት ነው።*

እውነተኛ የሆኑ ክርስቲያኖች፣ ከአማኞች ሕብረት ወይም አንድነት ውጪ ወይም ለብቻቸው ሆነው መኖር አይችሉም። በሕብረት መኖር ያለባቸውም ደስ ሲላቸው፣ ወይም አንዳንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ ሁልጊዜ መሆን አለበት። አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጸንተው ለመቆምም ሆነ ለማደግ፣ በአንድ ላይ ከመያያዝ በስተቀር ሌላ አማራጭ የሆነ መንገድ እንደሌላቸው ማወቅ አለባቸው። እግዚአብሔር ሁላችንንም የጠራን በግል ይሁን እንጂ፥ ተገልለን ለብቻችን እንድንኖር አይደለም። የቤተ ክርስቲያን አካል ወይም የክርስቶስ ቤተሰብ አባል መሆን የምንችለው፥ በክርስቶስ በማመናችን፣ ቀደም ሲል አንደገለጽነው ስማችን ከአባላት መዝገብ ውስጥ በመጻፉ፥ በየሳምንቱ በሚደረገው የቤተ ክርስቲያን የአምልኮት ሥርዓት ላይ ተካፋዮች በመሆናችን፥ አሥራታችንን በመክፈላችን አይደለም። የቤተ ክርስቲያን የአካሉ ክፍል ለመሆን፣ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ እንደ ገና መወለድ አለብን። በክርስቶስ አማካኝነት እንደ ገና ከተወለድን፣ ከሌሎች አማኞች ጋር የልብ አንድነት ሊኖረን፥ የተመረጠ ትውልድ፥ ቅዱስ ሕዝብ መሆን እንችላለን (1 ጴጥ. 2፥9)። በሌሎች ዘንድ የምንታወቀው፥ በተናጥል ሳይሆን፥ ከክርስቶስ ጋርና እንዲሁም እርስ በርሳችን በሚኖረን መያያዝ ወይም አንድነት ነው።

"ቤተ ክርስቲያን" መጽሐፍ ቅዱስ የሚገልጻትን ዓይነት መሆን እንድትችል፥ የአካሉ ክፍል የሆኑት ምዕመናን፥ እርስ በርሳቸው የጠበቀ (የተቀራረበ) ግንኙነት ወይም አንድነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ኢየሱስ ስለ አማኞች አንድነት በጸለየው ጸሎት፥ *"...አንተ እንደላከኸኝም ዓለም እንዲያምን..."* ሲል፣ የክርስቲያኖች የተቀራረበ ግንኙነት ወይም አንድነት ለወንጌል ሥርጭት ትልቅ ኃይል እንደሆነ መረዳት ያስችለናል። አማኞች እርስ በርሳቸው ካልተቀራረቡ፥ አንዱ ለሌላው ካልተጠነቀቀ፥ አንዱ ሌላውን ካልደገፈ፥ካላበረታታ በአማኞች የግል ሕይወትም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ ዕድገት ሊኖር አይችልም። የክርስቶስ ክብር በዓለም ውስጥ በደንብ እንዲገለጽ፥ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል መንፈስ ቅዱስ በሰጠው ስጦታ ማገልገል ይገባዋል። አማኞች እውነተኛ ሕብረት ወይም አንድነት በመካከላቸው ከሌለ ደግሞ፥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲሠራ አይታይም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ አንድነት እንዲኖር ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያለባቸው ምዕመኑ ብቻ ሳይሆን፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምዕመናን አንድነት ሳይኖር፣ ግጭትና መከፋፈል እያለ "የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ሥራ በመካከላችን አለ" ብሎ ማሰብም ሆነ ማውራት፣ እያወቁ ራስን እንደመዋሸት ይቆጠራል።

"ቤተ ክርስቲያን" የሚለው ቃል *"ኤክሌሺያ"* ከሚለው የግሪክ ቃል የወጣ ነው። ትርጉሙም "ጉባኤ" *(Assembly)* ማለት ሲሆን፥ መሠረታዊ ቃሉ የወጣው "ተጠርቶ የወጣ" ከሚለው ቃል ነው።[5] ክርስቲያኖች አዲስ ሕይወት ለመኖር ከዓለም ተጠርተው

[5] [illegible] A. Gene. Elders and Leaders. Moody Publishers. Chicago, IL, 2003, p. 49.



የወጡ ናቸው። ጳውሎስ ተጠርተው የወጡ በመሆናቸው ምን ዓይነት ሕይወት መኖር እንዳለባቸው ሲገልጽ፥ *"...የተጠራችሁበትን ጥሪ የሚያስመሰግን ሕይወት ይኑራችሁ ብዬ እለምናችኋለሁ"* ይላል (ኤፌ. 4፥1)። ቤተ ክርስቲያን "ተጠርተው የወጡ" የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሕብረት ነው። ጳውሎስ *"የእስራኤልን ዜግነት አጥታችሁ ለተስፋው ቃል እንግዶች ሆናችሁ በዚህ ዓለምም ተስፋ አጥታችሁና ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ። አሁን ግን እናንተ ከዚህ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁት በኢየሱስ ክርስቶስ ሆናችሁ በእርሱ ደም ቀርባችኋል። ሊያይቶን የነበረውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰና አይሁዳውያንንና አሕዛብን አንድ ያደረገ ሰላማችን ክርስቶስ ነው። ሰላምንም በማድረግ ከሁለቱ ሕዝቦች ከእርሱ ጋር የሚተባበር አንድ አዲስ ሕዝብ ለመፍጠር የሕግን ትእዛዞችና ደንቦች በሥጋው ሻረ"* ይላል (ኤፌ. 2፥12-15)። ጳውሎስ ይህን ሲል በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም ዓይነት ልዩነት መኖር እንደማይገባው መግለጹ ነው።

ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያኑን ሲመሠርት ዓላማው አማኞችን በጾታ፥ በዘር ከፋፍሏቸው የነበረውን ልዩነት አጥፍቶ አንድ ለማድረግ፣ አዲስ ሕብረተሰብ ለመፍጠር ነው። ይህን አዲስ ሕብረተሰብ ጳውሎስ ሲገልጽ፥ *"ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ስለሆናችሁ በአይሁዳዊና በግሪካዊ፥ በአገልጋይና በጌታ፥ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም"* (ገላት. 3፥28) አለ። ክርስቶስ "ራስ" በሆነበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአማኞች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት ሊኖር እንደማይገባው ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች ግልጥ አድርጎ ነግሯቸዋል። *"እንግዲህ አንዱ እግዚአብሔር የሁሉም ጌታ ስለ ሆነ፥ በአይሁዳዊና በአረማዊ መካከል ምንም ልዩነት የለም..."* (ሮሜ 10፥12) ይላል። ይሁን እንጂ፥ በቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ አማኞች፥ በተለይ ከአይሁድ እምነት ወደ ክርስትና የመጡ፥ ከአሕዛብ ጋር ተቀላቅለው ማምለክ ከባድ ይሆንባቸው ነበር። ክርስቶስ በሰዎች መካከል የነበረውን ልዩነት አጥፍቶ ሁሉንም አንድ ያደረገ በመሆኑ፥ በክርስቲያኖች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት ሊኖር እንደማይገባ መረዳት ተሳናቸው ነበር።

## 4. አማኞችን አንድ ላይ ሊያያይዛቸው የሚችለው ምንድነው?

ጳውሎስ የፊልጵስዮስ አማኞች አንድነታቸውን በምን እንዳገኙ ሲገልጽላቸው፥ *"በመንፈስ ቅዱስ አንድነትን አግኝታችኋል.."* ይላቸዋል (ፊልጵ. 2፥2)። እንዲሁም አንድነታቸው በምን ዓይነት ሁኔታ መገለጽ እንዳለበት ሲመክራቸው ደግሞ፥ *"...እርስ በርሳችሁ ደግነትንና ርኅራኄን አሳይታችኋል። ስለዚህ በአሳብ፥ በፍቅር፥ በመንፈስ፥ በዓላም እየተስማማችሁ ደስታዬ ሙሉ እንዲሆን አድርጉ"* ይላቸዋል (ፊልጵ. 2፥2)። ጳውሎስ "አንድ አሳብ" ሲል፥ የትኛውን አሳብ ነው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ያ አዲስ

አሳብ የክርስቶስ አሳብ እንጂ የዓለም አይደለም። አማኞችን አንድ ላይ እንዲያያዙና በሕብረት እንዲኖሩ የሚያስችላቸው አንደኛው "ትህትና" ሲሆን፥ ሁለተኛው "ፍቅር" ነው።[6]

## 4.1. የትሕትና መንፈስ

ሐዋርያው ጳውሎስ የፊልጵስዩስን አማኞች ሲመክር፥ *"ከትሕትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቁጠሩ እንጂ ወገን በመለየትና በራስ ወዳድነት ወይም ያለ እኔ ማን አለ በሚል ትምክህት ምንም ነገር አታድርጉ"* ይላቸዋል (ፊልጵ. 2፥3)። በዚህ ነጥብ ላይ ምሳሌ ሊሆናቸው የሚችለውን ሰው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽላቸው፥ *"...በዚህ ዐይነት ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው የትሕትና ጠባይ በእናንተም ሕይወት ሊኖር ይገባል"* ይላቸዋል (ፊልጵ. 2፥5)። ከሌላው ጋር ለመያያዝ፥ በቅድሚያ በራስ ካተኮረ ሕይወት መላቀቅን ይጠይቃል። ሰው ከራሱ ፍቅር ሲላቀቅ፥ ያተርፋል እንጂ፥ አያጎድልም። ከራስ ጋር የተላቀቀ ሕይወት ለመኖር እንዲችሉ ጳውሎስ አሁንም ለፊልጵስዩስ አማኞች ምክር ሲሰጥ፥ *"...እያንዳንዱ የራሱን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሰው ጥቅም ያስብ"* ይላል (ፊልጵ. 2፥4)። ክርስቲያኖች የክርስቶስ ልብ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። የክርስቶስ ልብ በትህትና የተሞላ ስለሆነ ምሳሌያችን እርሱ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ኢየሱስ ያለውን ትሕትና ሲገልጽ፥ *"...ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው የትሕትና ጠባይ በእናንተም ሕይወት ሊኖር ይገባል። እርሱ የመለኮት ባሕርይ አለው፤ ይሁን እንጂ፥ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደርገውን የመለኮት ባሕርይ እንደያዘ መቅረት አልፈለገም። ይልቁንም ያለውን ክብር በገዛ ፈቃዱ ትቶ፥ አገልጋይ መሆንን መረጠ፤ በሰው ምሳሌም ተገለጠ፤ እንደ ሰው ሆኖም በትሕትና ራሱን ዝቅ አደረገ..."* (ፊልጵ. 2፥5-8)። እንዲሁም *"በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ ሃሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን"* ይላል (ፊልጵ. 2፥5)።

እውነተኛ ትሕትና የሚገኘው ከክርስቶስ ጋር በሚኖረን ግንኙነት ውስጥ ብቻ ነው። ሰው በግሉ የሃይማኖት ትምህርቶችን ማወቅ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በቃሉ ማጥናት ይችላል። ከክርስቶስ ጋር ሕብረት ሳይኖረው በትሕትና መመላለስ ግን አይችልም። በክርስትና ልምምድ ውስጥ "ትዕቢት" ወይም "ኩራት" አደገኛ ነው። ክርስቲያን በትሕትናው አርአያ ወይም ምሳሌ የሚሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። *"ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው የትሕትና ጠባይ በእናንተም ሕይወት ሊኖር ይገባል"* (ፊልጵ. 2፥5) ይላል። እውነተኛ ደቀ መዝሙርነት የሚጀምረው ከዚህ ነው። ጳውሎስ ተገቢ ስለሆነው የክርስትና ጉዞ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን አባሎችና መሪዎች ሲናገር እንደ ምሳሌ አድርጎ ያቀረበው የራሱን ሕይወት ነው። *"...በአይሁዳውያን ሴራ ምክንያት መከራ ቢደርስብኝም እንኳ በፍጹም ትሕትናና በእንባ ጌታን አገለግላለሁ"* አለ (የሐዋ. 20፥19)። ጳውሎስ በሌላ ጊዜ ለኤፌሶን አማኞች ደብዳቤ ሲጽፍላቸው፥ ይህንኑ አሳብ ይጠቅስላቸዋል። ክርስቶስ ስለ ራሱና እንዲሁም ስለ መብቱ አልተከራከረም። አንዳንዶች ቀለዱበት፤ ምራቃቸውንም ተፉበት። እጆቹን በምስማር ወጉ፤ በመስቀልም ላይ አንጠለጠሉት። እርሱ ግን ስለ መብቱ አልተከራከረም። "ይህን በእኔ ላይ ማድረግ አትችሉም፤ ከዚህ በላይ መታገስ አልችልም" አላለም። በትሕትና ልብ የተሞላው "በእኔ ላይ የምታደርጉት ነገር ወደ ደህንነት ካመጣችሁ፥ እውነትን እንድታውቁ ከረዳችሁ፥ በረከት ከሆናችሁ፥ ስቃዩ አይሰማኝም። ምክንያቱም ስለ እናንተ ግድ ይለኛልና" ማለቱ ነው። የክርስቶስ ልብ ያለው ጳውሎስም *"...የእኔም ሕይወት ተጨማሪ መሥዋዕት ሆኖ ቢቀርብ እንኳ ደስ ይለኛል..."* ይላል (ፊልጵ. 2፥17)። እኛንም ሲመክረን፥ *"እያንዳንዳችሁ እግዚአብሔር በሰጣችሁ እምነት መጠን በትሕትና አስቡ እንጂ፥ ከሚገባችሁ በላይ ስለራሳችሁ በትዕቢት አታስቡ ብዬ እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ እመክራችኋለሁ"* ይለናል (ሮሜ 12፥3)።

ክርስቲያኖች ሁሉ የክርስቶስ የአካሉ ክፍሎች ናቸው። ያላቸውንም አንድነት የሚረዱት ራሳቸውን በማስቀደም ፈንታ ለሌሎች ቅድሚያ ሲሰጡ ነው። ክርስቲያኖችን *"እኔነት" (Ego)* ሊያጠቃቸው፣ ስለ ራሳቸው ፍላጎትና መብት ማሰብና መጨነቅ አይገባቸውም። *"በእኔነት"* መንፈስ የተሞላ ሰው የራሱን እንጂ ስለሌላው ሰው ፍላጎት ግድ የለውም። የራሱን የማያስነካ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ ቢችል የሌሎችን ከመንጠቅ ወደ ኋላ አይልም። ይሄን ዓይነቱ ከዓለማውያን እንጂ ከክርስቲያኖች የሚጠበቅ ባሕሪ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። የቆሮንቶስ አማኞች ከሚታዩባቸው ድካሞች መካከል አንደኛው፣ *"የራሴ የሆነውን አላስነካም"* በማለት አብረዋቸው የሚያመልኩትን ክርስቲያኖችን ከሰው ፍርድ ቤት ያቀረቧቸው መሆናቸው ነው። ይሄ ሁኔታቸው ጳውሎስን ስላሳዘነው፥ *"እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን? ነገር ግን እናንተ ትበድላላችሁ፤ ታታልሉማላችሁ፤ ያውም ወንድሞቻችሁን"* (1 ቆሮ. 6፥7-8) ሲል ጻፈላቸው።

ክርስቲያኖች አንድ አካል እንዲሆኑ እርስ በርስ ከሚያያዟቸውም ነገሮች መካከል አንደኛው፣ *"ትሕትና"* ነው። የትሕትና መጨረሻ ለመሆኑ እስከ ምን ድረስ ይሆን? ትህትናን በሕይወቱ የሚለማመድ ክርስቲያን፣ በሌሎች መረገጫ እስከ መሆን ደረጃ ድረስ ሊደርስ ይችላል። ያም ቢሆን፥ እግዚአብሔር ከወደቀበት ያነሳዋል። ትሕትና የሚፈልቀው "ራስን በማወቅ"፥ ራስን መለኮታዊ በሆነ መመዘኛ በመመዘን ነው። *"አይነ ሥውራን ብቻ ባሉበት አካባቢ (አገር)፥ አንድ ዓይን ያለው ሰው ንጉሥ ነው"* የሚል አባባል አለ። ክርስቲያን ራሱን የሚለካው በዓለም ውስጥ ከሚጠጡትና ከሚሰክሩት ጋር በማወዳደር ከሆነ፣ እውነተኛ ማንነቱን መረዳት አይችልም። ከዓለማውያን ጋር ራሱን የሚያወዳድር ከሆነ፥ ከእነርሱ ትንሽ በመሻሉ፣ *"እስከዚህ ድረስ መጥፎ አይደለሁም"* በማለት ራሱን ሊያጽናና ይችላል። ፈሪሃ እግዚአብሔር ከሌላቸው ሰዎች ጋር ራሳችንን

[6] MacArthur, John, Jr. Body Dynamics. SP Publications, Inc. Wheateon, ILL, 1982, pp. 18-21.

በማነጻጸር ከፍጹምነት ደረጃ የደረስን መስሎን እንዳንታበይ መጠንቀቅ አለብን። የክርስቲያን መለኪያው ሌላ ሰው ሳይሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ምንም ያህል ጥሩ ክርስቲያኖች የሆንን ቢመስለን፥ ከክርስቶስ ሕይወት ጋር ራሳችንን ስናነጻጽር ወይም ስናስተያይ፥ ምን ያህል ሩቅ እንደሆንን፥ እንዲሁም ገና ብዙ እንደሚቀረን እንገነዘባለን። ትሕትና ምን ዓይነት እንደሆነ ሲያስተምረን ኢየሱስ ጎንበስ ብሎ የደቀ መዛሙርቱን እግር አጠበ። ጌታችን አምላክ ሆኖ ራሱን ዝቅ አድርጎ የሰውን እግር ካጠበ፥ ምንም ያልሆነው እኔና እናንተማ ምን ያህል ራሳችንን ዝቅ ማድረግ ይገባን ይሆን?

ትህትና በሌለበት፥ ሁሉም "እኔ እበልጣለሁ፥ እኔ እሻላለሁ" በሚልበት ሕብረት ውስጥ፥ ጦርነትና ግጭት እንጂ እውነተኛ "አንድነት" ሊኖር አይችልም። ደቀ መዛሙርቱ በትሕትናው ጥሩ ምሳሌ ሊሆናቸው የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ አጠገባቸው እያለላቸው "ከእኛ መካከል ትልቁ ማን ነው?" በማለት እርስ በርሳቸው ይከራከሩ እንደ ነበር እናውቃለን። ይሄም በመካከላቸው ከባድ ቅሬታና ግጭት እንደፈጠረባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ እናያለን። ዛሬም በክርስቲያኖች መካከል ትልቅ ግጭት ወይም ጠብ የሚፈጠረው፥ አንዳንዶች ከሌላው ቀድሞ ለመገኘት፥ ሌላውን ለመብለጥ በሚያደርጉት ትግል ወይም ሩጫ ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው። ሁሉም "እኔ እበልጣለሁ፤ እኔ ከሌሎች እሻላለሁ" ካለ፥ በሕብረት መጓዝ አይቻልም። የወንጌል ጠላት የሆነው ሰይጣን፥ ቤተ ክርስቲያንን ከውጪ ሆኖ ከማፍረስ ይልቅ፥ ከውስጥ ሆኖ ማፍረስ ቀላል ሆኖ ስላገኘው፥ በራሳቸው በክርስቲያኖች ከምንጊዜውም የበለጠ እየተጠቀመ ነው። ሰይጣን ክርስቲያኑን "ደካማ ነህ፤ አትረባም" ቢለው፥ ብርቱ ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ነበር። ይሆንን በማለት ፈንታ ተንኮለኛው ሰይጣን ክርስቲያኑን "ጎበዝ ነህ! ከሁሉም ትበልጣለህ" በማለት ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ እንዲታየው ያደርጋል። የሰይጣንን ተንኮል ያልተረዳው ክርስቲያንም፥ እውነት ትልቅ የሆነ፥ ከሌሎች ሁሉ የተሻለ ይመስለውና፥ "ማን እንደ እኔ አለ? ከሁሉም እበልጣለሁ" በማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሥልጣን ትግል ማካሄድ ይጀምራል። ይሄን ዓይነቱ መንፈስ ክርስቲያኖችን አንድ በማድረግ ፈንታ ሲበታትናቸው፥ ሲከፋፍላቸው፤ እርስ በርሳቸው እንደ ጠላት እንዲተያዩ ሲያደርጋቸው ማየት በአሁን ጊዜ አዲስ ነገር አይደለም። በዘመናት የእግዚአብሔርን ልብ የነኩት፥ ደስ ያሰኙት፤ እግዚአብሔርን ያከበሩ አስመስለው በአገልግሎት ላይና ታች በመሯሯጥ የደከሙት ሳይሆኑ፥ ራሳቸውን "አገልጋይ" ወይም "አሽከር" አድርገው ያቀረቡት ናቸው።

## 4.2. እውነተኛ የእርስ በርስ ፍቅር

አማኞችን አንድ ላይ እንዲያያዙና በሕብረት እንዲኖሩ የሚያስችላቸው ሌላው ነገር፥ ፍቅር ነው። እውነተኛውን ፍቅር ለማወቅ፥ ኢየሱስ ለእኛ የገለጸውን ፍቅር ማየቱ ይጠቅማል። ኢየሱስ ለሰው ያሳየውን ፍቅር ዮሐንስ ሲገልጽ፤ *"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን*



*አሳልፎ ስለሰጠ፥ በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል"* ይላል (1 ዮሐ. 3፥16)። ራሱ ፍቅር የሆነው ኢየሱስ፤ *"እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። እርስ በርሳችሁ ብትዋደዱ የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ ሰው ሁሉ ያውቃል"* በማለት ይመክረናል (ዮሐ. 13፥34-35)። እዚህ ላይ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ *"ከቻላችሁ፥ ከፈቀዳችሁ፥ የሚወደድ ነገር ካለው፥ ከተስማማችሁ ውደዱ"* በማለት ምርጫ በመስጠት ፈንታ፥ የማያዛንፍ ትዕዛዝ ሲሰጥ እናየዋለን። ትክክለኛው "ፍቅር" ሁኔታዎች አይወስኑትም። እንዲሁም ሌላው በሚያደርገው ሁኔታ ላይ ያረፈ አይደለም። በዘመናችን ዓለማውያን በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ጎልቶ የሚታያቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነው "ፍቅር" ሳይሆን፤ የሥጋ ሥራዎች የሆኑት "ጥል፥ ክርክር፥ ቅንአት፥ ቁጣ፥ አድመኝነት..." ናቸው። በአሁኑ ዘመን ዓለማውያን፤ ክርስቲያን መሆናችንን ለይተው የሚያውቁን እርስ በርሳችን ባለን ፍቅር ሳይሆን፤ በመጣላታችንና እርስ በርስ በመከፋፈላችን ይሆናል ብለን እንገምታለን። ያለ ፍቅር ክርስቲያን መሆን እንደማይቻል ብናውቅም፤ አንዳንዶቻችን ከፍተኛ ጦርነት እያካሄድን ራሳችንን "ክርስቲያን" ብለን መጥራት አያሳፍረንም። የፍቅርን ወንጌል እንደሚገባው ስለማንሰብክ፥ የሰበክነውንም የማንኖርበት በመሆናችን ነው ዛሬ መከፋፈልና መለያየት በክርስቲያኖች መካከል ከምንጊዜውም የበለጠ ጎልቶ የሚታየው። "ከፍተኛው የወንጌል ስርጭት፤ ወይም ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በዓለም ላይ እየተካሄደ ነው" ማለት የምንችለው ታላላቅ ስብሰባዎችን በማድረጋችን ሳይሆን፥ በክርስቲያኖች መካከል በፍቅር የተያያዘ አንድነት ሲኖር ነው። የክርስቲያን አንድነት ዋና ምልክት በአማኞች መካከል የሚታየው ፍቅር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ሲጸልይ፥ *"እኛ የምናፈቅራችሁን ያህል እርስ በርስ ያላችሁን ፍቅርና ለሌሎችም ያላችሁን ፍቅር ጌታ ይጨምርላችሁ፤ ያብዛላችሁም"* (1 ተሰሎ. 3፥12) ሲል፤ ሐዋርያው ዮሐንስ ደግሞ *"ከመጀመሪያው የሰማችሁት መልእክት እርስ በርሳችን እንድንዋደድ የሚል ነው"* ይላል (1 ዮሐ. 3፥11)። አንድነታችን የማይበጠስ እንዲሆን የሚያያይዘው "ፍቅር" እንደሆነ በግልጽ እናያለን።

አማኞች ለእግዚአብሔር ያለን አምልኮት፥ እንዲሁም ሙሉ መሰጠታችን በግልጽ የሚታየው፤ እርስ በርሳችን በሚኖረን ፍቅር ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ *"ማንም እግዚአብሔርን እወደዋለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችኝ"* ይላል (1 ዮሐ.4፥20-21)። የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የሚታይባት፥ ምዕመናኗ የተለያየ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያላቸው ነበሩ። ይሁን እንጂ፥ እርስ በርሳቸው የሚያያይዛቸው ፍቅር አልነበራቸውም። ለዚህ ነው አንዳንዶች *"...እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ እኔ የአጵሎስ ነኝ፤ እኔ የኬፋ ነኝ፤ እኔ የክርስቶስ ነኝ"* (1 ቆሮ. 1፥12) በማለት በቡድን

ተከፋፍለው የነበሩት። ያለፍቅርና ያለአንድነት ቤተ ክርስቲያን ማደግ፥ እንዲሁም እግዚአብሔርን ማገልገል፣ እርሱን ደስ ማሰኘት አይቻልም። ፍቅር ሁልጊዜ በውስጣችን መኖር ያለበት እንጂ፣ ስንፈልግ የምናበራው፥ ሳንፈልግ ደግሞ የምናጠፋው መሆን የለበትም። እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ ስለሆነ፥ ፍቅር የሚኖረን መጀመሪያ በእግዚአብሔር ፍቅር ስንሞላ ብቻ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በሰው ሕይወት ውስጥ ሲፈስ፥ የሰው ሕይወት በፍቅር የተሞላ ይሆናል። በእግዚአብሔር ፍቅር ልቡ የተሞላ ሰው፥ የማይወደድ እንኳን ቢሆን፣ "ሌላውን መውደድ አልችልም" አይልም።

የክርስቲያኖችን አንድነት የሚያመለክተው "ፍቅር" በሕይወቱ የሞላው አማኝ፣ ሌላውን ወንድሙን *"ወንድሜ በአንተ ላይ ቅር ተሰኝቼብህና አዝኜብህ ነበር፥ ይቅር እንድትለኝ እፈልጋለሁ፥ በአንተ ላይ ያለኝን ቅሬታ ትቼ በፍቅር መመላለስ እፈልጋለሁ"* ለማለት የሚያቅተው አይደለም። ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ግድ የሚለው ሌላው ወንድም ደግሞ ይህንን ሲሰማ፣ "ወንድሜ ይቅር ብዬሃለሁ" ማለት አያቅተውም። "የክርስቲያኖች አንድነት" ማለት፣ አማኞች ሁሉ አንድ ዓይነት ይሆናሉ ማለት አይደለም። ጳውሎስ *"አካል የተሠራው ከብዙ የአካል ክፍሎች እንጂ ከአንድ የአካል ክፍል ብቻ አይደለም"* (1 ቆሮ 12፥12) ይላል። የሰው አካል አንድ ነው፥ ይሁን እንጂ፥ ልዩ ልዩ አገልግሎት ያላቸው የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች አሉት። የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ይኑሩ እንጂ፥ የሰው አካል አንድ ነው። የሰው የአካል ክፍል የሆነው አንዱ፣ ከሌሎች ተቆርጦ ቢወድቅ በሕይወት መኖር አይችልም። ልክ እንደዚሁ የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያንም፥ የአንዱ አካል ክፍል ከሌሎች የአካል ክፍሎች ምንም ያህል የተለየ ቢሆንም፣ በሕይወት ለመቆየት፣ እንዲሁም ለማደግ፣ ከሌሎች የአካል ክፍሎች ጋር አንድ ላይ መያያዝ አለበት። "ቲሹዎች"፥ ጡንቻዎችና አጥንቶች" የሰውነት ክፍሎችን (ብልቶችን) እርስ በርሳቸው እንደሚያይዟቸው ሁሉ፣ ክርስቲያኖችንም እርስ በርስ የሚያይዛቸው ፍቅር ነው። ፍቅር ከሌለ መያያዝ የለም። መያያዝ ከሌለ ደግሞ በተናጥል ለመኖር ስለማይቻል፥ እውነተኛ የሆነ ዕድገት አይኖርም።

የአካሉ አንድነት የሚታየው ወይም የሚገለጸው በአገልግሎትና በሚኖረው ሕብረት ነው። በዘመናችን ብዙ እውነትነት የሌላቸው ብዙ ሕብረቶች አሉ። ሰዎች የልብ ግንኙነት ሳይኖራቸው አስመስለው አንድ ላይ ይሰበሰባሉ። እንዲህ ዓይነቱ እውነተኛ የክርስቲያን ሕብረት አይደለም። የአካሉ ሕብረት የተመሠረተው በምን እንደሆነ ሐዋርያው ዮሐንስ ሲገልጽ፥ *"...እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን..."* (1 ዮሐ. 1፥3) ይላል። ዮሐንስ እዚህ ላይ ለማለት የፈለገው፥ ከክርስቶስ ጋር ሕብረት ስለ ነበረው፥ የሚሰብከው ወንጌል በግሉ ያየውና የተለማመደው መሆኑን ነው። ወንጌሉን የሚሰብከው፥ ወንጌል የክርስቲያኖች ሕብረት መሠረት በመሆኑ ነው። የወንጌሉ ዓላማ ሌላ ነገር ሳይሆን፥ የክርስቲያኖችን



ሕብረት ለመፍጠር ነው። ክርስቶስ በዓለም በነበረበት ዘመን የነበረው ግሩም የሆነ አንድነት በዚያን ዘመን ብቻ ተወስኖ እንዲቀር ሳይሆን፥ አሁንም በክርስቶስ ከምናምነው ጋር እንዲቀጥል ነው። ሕብረታችንም እርስ በርሳችን ብቻ ሳይሆን ከአብ፥ ከወልድና እንዲሁም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ነው። በክርስቶስ አማካኝነት ደህንነትን ሳናገኝ ግን ከአብ ጋር ሕብረት ሊኖረን አይችልም። እንዲሁም አማኞች ሳንሆን፥ ከአማኞች ጋር ኅብረት ሊኖረን አይችልም። ከእግዚአብሔርም ሆነ ከአማኞች ጋር ሕብረት እንዲኖረን የፈቀደው እግዚአብሔር ራሱ ነው። ጳውሎስ *"ከልጁ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው"* (1 ቆሮ. 1፥9) ይላል። እግዚአብሔር ሩቅ የሆነ፥ ፈጽሞ ልንቀርበው የማንችለው ሳይሆን፥ በጸጋው በክርስቶስ በማመን ከእርሱ ጋር ሕብረት እንዲኖረን የፈቀደ ነው። እያንዳንዱ አማኝ "የጋራ የሆነ እምነት" ተካፋይ ነው (ቲቶ 1፥4)።

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች፣ የነበራቸው ሕብረት ምን ዓይነት እንደነበረ ሉቃስ ሲገልጽ፥ *"አማኞች ሁሉ አንድ ልብና አንድ ሐሳብ ነበራቸው፤ ማንም ሰው 'ይህ የእኔ ነው' የሚለው ነገር አልነበረውም፤ በመካከላቸውም ሁሉ ነገር የጋራ ነበር"* ይላል (የሐዋ. 4፥32)። ይኼን ዓይነቱ የክርስቲያኖች ሕብረት ለብዙዎች ወደ ክርስቶስ መምጣት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። *"አማኞች ሁሉ በአንድነት አብረው ይኖሩ ነበር፤ ያላቸውም ነገር ሁሉ የጋራ ነበር። መሬታቸውንና ንብረታቸውን እየሸጡ ገንዘቡን ለእያንዳንዱ እንደሚያስፈልገው ያከፋፍሉ ነበር። በየቀኑ በቤተ መቅደስ በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር፤ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በቅን ልብ ይመገቡ ነበር። እግዚአብሔርንም ያመሰግኑ ነበር። ሰውም ሁሉ ያከብራቸው ነበር፤ እግዚአብሔርም የሚድኑትን ሰዎች በየቀኑ ወደ ማኅበራቸው ይጨምር ነበር"* (የሐዋ. 3፥44-47)። እየሱስ የጸለየው እንዲህ ዓይነቱ አንድነት እንዲኖራቸው ነበር።

የዘመኑ ክርስቲያኖች አንድነት ምን ይመስላል? የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ሲያልቅ ሻይና ቡና ለመጠጣት ወደተወሰነው አዳራሽ መሄድ ይሆን? ወይስ በዓመት አንድ ጊዜ ሽርሽር መሄድ ይሆን? ብዙ ጊዜ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቲያኖች በአንድነት ሲሰበሰቡ፥ በእግዚአብሔር ቃል እርስ በርስ በመተናነጽና በመደጋገፍ ፈንታ፥ ሆሜትና አሉባልታ በማውራት ጊዜ ስለሚያልፍ፥ ፕሮግራሙ አልቆ ሁሉም ወደ ቤቱ ሲሄድ፥ በነበረው የአንድነት ጊዜ በመደሰት ፈንታ፥ ባወሩት አሉባልታ ምክንያት በአዕምሮ ጸጸት የሚሞሉ አሉ። እውነተኛ ሕብረት ሲኖር፥

- ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው አይተማሙም፤
- አንዱ በሌላው ላይ አይፈርድም፤
- አንዱ በሌላው አይቀናናም፤

- አንዱ ሌላውን አይዋሽም፣
- አንዱ ስለ ሌላው ክፉ አይናገርም።
- አንዱ ሌላውን ያንጻል፣
- አንዱ ሌላውን ይቅር ይላል፣
- አንዱ ሌላውን ያጽናናል፣
- አንዱ ሌላውን ይመክራል፣
- አንዱ ሌላውን ይደግፋል።

ሕብረቱን በሚመለከት፤ እያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት እንዳለበት ያውቃል። ሕብረቱ ጸንቶ መቆም የሚችለው እያንዳንዱ አማኝ፣ ለሌላው አማኝ አንድ ነገር ማድረግ የቻለ እንደሆነ ነው። ይኸውም፤ አንዱ ሌላውን ማሰብ ሲችል (ዕብ. 10፥25)፣ እርስ በርሳቸው የማይተማሙ ሲሆኑ (ያዕ. 4፥11)፤ እርስ በርሳቸው በኃጢአታቸው ሲናዘዙ (ያዕ. 5፥16)፤ እርስ በርሳቸው ሲቀባበሉ (1 ጴጥ. 4፥9)፣ እንዲሁም አንዱ ሌላውን ሲያገለግል (1 ጴጥ. 5፥5) ነው።

## 5. ኃጢአት የአማኞችን አንድነት የማበላሸት ኃይል አለው

አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ጊዜያዊ ሳይሆን ዘላለማዊ ስለሆነ፤ ምን ጊዜም አንድነቱ የተጠበቀ መሆን አለበት (ዮሐ. 10፥28-29)። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለ ሆነ፤ አማኝ ሁልጊዜ በኃጢአት ውስጥ መኖርን ከመረጠ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን አንድነትና ግንኙነት ሆን ብሎ ማፍረሱ እንደሆነ ግልጽ ነው። ኃጢአት ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ይቀንስበታል እንጂ፣ ኃጢአት የሚሠራው አማኝ ለእግዚአብሔር ምንም ዓይነት ፍቅር የለውም ማለት አይደለም። ፍቅር ቢኖረውም እግዚአብሔር ከኃጢአት ጋር ስለማይተባበር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ሊቋረጥበት ይችላል። ይኸውም የጸሎት ሕይወቱ ሊቀዘቅዝ፣ ለቃሉ ያለው ፍቅርና መጠማት ሊቀንስ፣ ከሌሎች አማኞች ጋር ያለው ግንኙነት የተራራቀ ሊሆን ይችላል። የዚህ ሁሉ ምክንያት ከኃጢአቱ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ድፍረት ስለማይኖረው ነው። የክርስቲያኖች ሕብረት መሠረት የክርስቶስ የመስቀል ሞት ነው። የቅዱስ ቁርባን ፕሮግራማችን በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለንን ሕብረት (አንድነት) ያሳያል። ክርስቲያኖች በቅዱስ ቁርባን ወቅት ህብስቱን ሲቆርሱ፤ ወይኑን ሲጠጡ፤ በክርስቶስ ሞት ያላቸውን አንድነት መግለጻቸው ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "እግዚአብሔርን አመስግነን የምንካፈለው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? አብረን የምንቆርሰው ኅብስት ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? ኅብስቱ አንድ በመሆኑ እኛም ከዚህ ከአንዱ ኅብስት የምንካፈል ስለሆንን፤ ምንም እንኳ ብዙዎች ብንሆን አንድ አካል ነን"



ያለው (1 ቆሮ. 10፥16-17)። ከክርስቶስ ጋር ሕብረት ያለው አማኝ፤ የጌታን ጽዋ ተካፋይ የሆነ፤ እንዴት ከኃጢአትና ከዲያብሎስ ጋር ሕብረት ሊኖረው ይችላል? ይህን ቢያደርግ በክርስቶስ መስቀል መቀለዱ ይሆናል። ኃጢአት ስንሠራ ከሰይጣንና ከግብረ አበሮቹ ጋር መተባበራችን ይሆናል። ከሰይጣን ጋር እየተባበርን ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ሊኖረን አይችልም። ለዚህ ነው ጳውሎስ "...ማንም ሰው ይህን ኅብስት ከመብላቱና ይህንንም ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት ራሱን መመርመር አለበት። ማንም ሰው የጌታ ሥጋ ምን መሆኑን ለይቶ ሳያውቅ የጌታን ኅብስት ቢበላና የጌታን ጽዋ ቢጠጣ በራሱ ላይ ፍርድን ያመጣል" ያለው (1 ቆሮ. 11፥28-29)።

ማንኛውም አማኝ ራሱን ሳይመረምር ከህብስቱ እንዳይበላ፤ ከጽዋውም እንዳይ ጠጣ ያለበትን ምክንያት ጳውሎስ ሲገልጽ፤ "ከእናንተ መካከል ብዙዎች የደከሙትና የታመሙት፤ አንዳንዶችም የሞቱት በዚሁ ምክንያት ነው። ራሳችንን ብንመረምር እንዲሁ ባልተፈረደብንም ነበር" ይላል (1 ቆሮ. 11፥30-31)። አማኝ በኃጢአት ውስጥ እየኖረ ቅዱስ ቁርባን እንዲወስድ የማይፈቀድለት፤ የመስቀሉ ኃይል የቆመበትን ዓላማ ስለሚቃረን ነው። በኃጢአት እየኖረ ቅዱስ ቁርባን ቢካፈል በመስቀሉ የሚቀልድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በራሱ ላይም ፍርድን ያመጣል። ለዚህ ነው ኅብስቱን ከመብላታችንና ጽዋውን ከመጠጣታችን በፊት ራሳችንን መመርመር እንዳለብን ጳውሎስ የሚመክረን። አማኝ ከሌሎች አማኞች ጋር ጥሩ ኅብረት እንዳይኖረው ኃጢአት መሰናክል ይሆንበታል። "የፈለግሁትን ዓይነት ኃጢአት ብሠራ፤ ራሴን አንጂ ሌላውን አማኝ አልጎዳም" ማለት አይችልም። የአንዱ የአካሉ ክፍል፣ በአካሉ ውስጥ የተመደበለትን ኃላፊነት ባይ ፈጽም፤ ወይም ባይሠራ አካሉ እንደሚገባ ማደግ እንደማይችለው ሁሉ፤ የአንዱ አማኝ በኃጢአት ውስጥ መኖርም ሌላውን አማኝ ሊጎዳ ወይም እንዳያድግ ሊያደርገው ይችላል። "ትዕቢት፤ የሥጋ አምሮት፤ ዓለማዊነት፤ እንዲሁም በተሰጠን ስጦታ አለማገልገል፤ አለመጸለይ፤ መንፈሳዊ ስንፍና እንዲሁም ለመንፈስ ቅዱስ አለመሰጠት"–እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ኃጢአቶች ወይም ድክመቶች በአካሉ ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ኅብረት ወይም አንድነትን ያጠፋሉ።

## 6. እያንዳንዱ አማኝ ለኅብረቱ ኃላፊነት አለበት

የአማኞች ኅብረት ተካፋዮች ከሆንን ግዴታችን ምን ይሆን? ኅብረታችንን መጠበቅ የምንችለው፤ ለሌሎች አማኞች መታነጽ ድርሻችንን መፈጸም የቻልን እንደሆነ ነው። ይህንንም ያዕቆብ ሲገልጽ፤ "ስለዚህ እንድትፈወሱ ኃጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፣ እያንዳንዱም ለሌላው ይጸልይ፣ የጻድቅ ሰው ጸሎት ብዙ ውጤት የሚያስገኝ ታላቅ ኃይል አለው" አለ (ያዕ. 5፥16)። አንዱ አማኝ ሌላውን አማኝ ቢበድል፤ ወደ በደለው ወንድም መሄድና በመካከላቸው የተፈጠረውን ችግር ማስተካከል እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ያዘዋል። "መባህን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር በምታቀርብበት ጊዜ ያበ፦ብህ

*ሰው መኖሩን ብታስታውስ፥ መባህን በመሠዊያው ፊት አስቀምጥና ሂደህ በመጀመሪያ ከዚያ ሰው ጋር ታረቅ፥ ከዚህም በኋላ ተመልሰህ መባህን አቅርብ"* ይላል (የማቴ. 5፥23-24)። አማኞች በሕብረቱ ውስጥ ኃላፊነታቸውን የሚፈጽሙት በተለያየ ሁኔታ ነው። ይኸውም፥

## 6.1. እርስ በርስ ኃጢአትን መናዘዝ

በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለውን ኅብረት መጠበቅ የምንችለው ኃጢአት ስንሠራ ኃጢአታችንን ለሌላው ክርስቲያን መናዘዝ የቻልን እንደሆን ነው። ክርስቲያኖች ሁሉ ምንም ሳይደብቁ ኃጢአታቸውን ቢናዘዙ ኖሮ፥ በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚኖረውን እውነተኛነት ምን ያህል ከፍተኛ ይሆን ነበር? ሁሉም እርስ በርሱ ኃጢአቱን መናዘዝ ቢችል፥ ኃጢአቱን የሚሸሽግ አማኝ አይኖርም ነበር። የሌላውን ኃጢአት ለምቶ በመታዘብ ፈንታ፥ "እኔም ተመሳሳይ ችግር አለብኝ" ይል ነበር። አማኞች ሁሉ የራሳቸው የሆነ ድካም እንዳለባቸው ቢገነዘቡ፥ አንዱ ለሌላው በምን ዓይነት ሁኔታ መጸለይ እንዳለበት ጥሩ መረዳት ይኖረው ነበር። አንዳንድ አማኞች እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት እርስ በርሳቸው ኃጢአታቸውን በመናዘዝ ፈንታ፥ ራሳቸውን ቅዱስና እንከን የሌለባቸው አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው የታወቀ ነው። ድካማቸውን ለማንም ገልጸው ለመናገር አይፈልጉም። ድካማቸውን ገልጸው የማይናገሩት፥ ሌላው አማኝ ምን ይለኝ ይሆናል ብለው በመፍራት ነው። ያዕቆብ "እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ" ሲል በዚህ ውስጥ ያለውን ጥቅም ስለሚያውቅ ነው። ኃጢአትን ለሌላው መናዘዝ የሥነ ልቦና ዕረፍት መስጠቱ ብቻ ሳይሆን፥ ተደጋጋሚ ኃጢአት እንዳንሠራ የሚጠብቀን መሆኑ ነው። ስለሆነም፥ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ሸፍነው ከመኖር ነጻ መውጣት አለባቸው። ኃጢአታችንን እርስ በርሳችን መናዘዝ፥ ኅብረታችንን ያጠነክራል።

## 6.2. እርስ በርስ ይቅር መባባል

አማኞች እርስ በርሳቸው ኃጢአታቸውን መናዘዝ ብቻ ሳይሆን፥ እርስ በርሳቸው ይቅር መባባልም እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይመክራቸዋል። አንዳንድ ክርስቲያኖች የበደላቸውን ይቅር ማለት በጣም ይከብዳቸዋል። ይሄም ብርታት ሳይሆን፥ ከክርስቲያኖች የማይጠበቅ ትልቅ ድካም ነው። ለበደለኛ ይቅርታ ስለማድረግ ጳውሎስ ሲጽፍ፥ *"ነውን ያሳዘነ ማንም ቢኖር ያሳዘነው እኔን ሳይሆን በደሉን ማጋነን አይሁንብኝ እንጂ በሌላ በኩል ከእናንተ ብዙዎቹን አሳዝኖአል። ለእንዲህ ዐይነቱ ሰው ከእናንተ አብዛኞዎቹ የፈረዱበት ቅጣት ይበቃዋል። ስለዚህ ይህ ሰው በጣም ከማዘኑ የተነሣ ተስፋ እንዳይቆርጥ ይልቅስ ይቅርታ እንድታደርጉለትና እንድታጽናኑት ይገባል"* ይላል (2 ቆሮ. 2፥5-7)። አማኝ በኃጢአት ቢወድቅ፥ በኃጢአቱ ምክንያት የሚደርስበት ጉዳት እንደሚኖር በመገንዘብ፥ ሌሎች አማኞች በእርሱ ላይ ከመፍረድ ይልቅ፥ ኃጢአቱን ይቅር ሊሉት ይገባል። ጳውሎስ *"እርስ በርሳችሁ ታገሡ፤ ከእናንተ አንዱ በሌላው ላይ ቅር የተሰኘበት ነገር ቢኖር ይቅር ተባባሉ፤ ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተም ይቅር በሉ"* (ቆላ. 3፥13) ብሎ ይመክረናል። ይቅርታ የሚገባን ባንሆንም፥ ክርስቶስ ኃጢአታችንን ይቅር ካለን፥ እኛ ደግሞ ሌላውን ይቅር አለማለታችን ትክክል አይደለም። *"ይልቅስ እርስ በርሳችሁ ደጎችና ለዛኞች ሁኑ፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ፥ እናንተም እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ"* ይላል (ኤፌ. 4፥32)።



## 6.3. እርስ በርስ መተጋገዝ

ጳውሎስ *"እርስ በርሳችሁ በመተጋገዝ ከእናንተ እያንዳንዱ የሌላውን ከባድ ሸክም ይሸከም፥ በዚህ ዐይነት የክርስቶስን ሕግ ትፈጽማላችሁ"* ይላል (ገላት. 2፥6)። ሸክሙ የከበደው አንድ አማኝ በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳለ ገልጦ ካልተናገረ፥ ሌላው አማኝ ሸክሙን ሊረዳው አይችልም። ስለዚህ አማኝ የሚኖርበትን የኃጢአት ሕይወት በመናዘዝ ሲጀምር፥ ለሚው ይቅርታ መስጠት፥ ከዚያም ሸክሙን መሸከም ይችላል። ይህም በምህረትና በርህራሄ በተሞላ ፍቅር ማፍቀርን ይጠይቃል። አንድ አማኝ፥ ሌላው አማኝ ኃጢአት ሲሠራ ቢያይ ምን ማድረግ አለበት? ኃጢአት ሠሪውን ላለማሳፈር ሲል ዝም ማለት አለበት? ለዚህ ጥያቄ ጳውሎስ መልስ አለው። *"ወደ ብርሃን አውጥታችሁ ኢጋልጡት እንጂ ፍሬቢስ ከሆነ ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ"* ይላል (ኤፌ. 5፥11)። ክርስቲያን ሆኖ ኃጢአት ሲሠራ የሚያይ አማኝ፥ ኃጢአት የሚሠራውን አማኝ በፍቅር የመገሰጽ መንፈሳዊ ግዴታ ወይም ኃላፊነት አለበት። *"ወንድምህ ቢበድልህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ በደሉን ንገረው፤ ቢሰማህ እንደገና ወንድምህ እንዲሆን ታደርገዋለህ"* ይላል (የማቴ. 18፥15)። በተለይ በመሪዎች ላይ ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ሲገልጽ፥ *"ሌሎች እንዲፈሩ ኃጢአት የሚሠሩትን በሰዎች ሁሉ ፊት ገሥጻቸው"* (1 ጢሞ. 5፥20) ብሎ ጢሞቴዎስን ያዘዋል። እዚህ ላይ አያቆምም። ተነግሮትም ኃጢአቱን ለማስወገድ ወይም ለመተው ፈቃደኛ ባይሆን ምን ዓይነት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ጳውሎስ ቀጥሎ ሲገልጽ፥ *"በኃጢአት የተሞላው የዚህ ሰው ሥጋ ይፈርስ ዘንድ ለሰይጣን አሳልፋችሁ ልትሰጡት ይገባል። ይህንንም የምታደርጉት ጌታ ለፍርድ በሚመጣበት ቀን የዚህ ሰው ነፍስ እንድትኖር ነው"* ይላል (1 ቆሮ. 5፥5)። እንደ እግዚአብሔር ቃል ኃጢአት የሚሠራውን በሰዎች ሁሉ ፊት መገሰጽ ብዙዎችን ከኃጢአት ያነጻ ነበር። ይሁን እንጂ፥ ብዙዎቻችን ኃጢአት የሚሠራውን ፊት ለፊት መገሰጽ ድፍረት የለንም። ድፍረት ስለሌለን፥ አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ ፈንታ፣ ውስጥ ውስጡን እሱባልታ ስናስፋፋ እንታያለን።

አንድ አማኝ ኃጢአት ሲሠራ ሌላው አማኝ ቢያይ፥ በፍቅር መገሰጽ እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። የዚህም ዋና ዓላማ ኃጢአትን ለመግታት ብቻ ሳይሆን፥ አማኞች ልባቸውን ለሌላው አማኝ ከፍተው ማሳየት እንዲችሉ ነው። ቤተ ክርስቲያን፥

የክርስቶስ አካል የሆኑት አገልግሎታቸውን የሚሰጡበት ኅብረት ነው። ስለዚህ አንዱ አማኝ ኃጢአት ሲሠራ ሌላው አማኝ መገሰጽ መቻል አለበት። ጳውሎስ ለቲቶ ሲጽፍለት፥ *"... ስለዚህ በእምነት ጤናማዎች እንዲሆኑ፥ የአይሁዳውያንን ተረት እንዳይከተሉና እውነትን የሚቃወሙትን ሰዎች ምክር እንዳይሰሙ በብርቱ ገሥጻቸው"* ይለዋል (ቲቶ 1፥13-14)። ትክክል ያልሆነ ትምህርት የሚያስተምሩትም ፊት ለፊት መገሰጽ እንዳለበት ጳውሎስ ለቲቶ በጻፈው መልዕክቱ ገልጾታል። *"...በሙሉ ሥልጣን ተናገርና ምክር፤ ገሥጽም፤ ማንም አይናቅህ"* ይላል (ቲቶ 2፥15)። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክርስቲያን ወንድሙ ኃጢአት ሲሠራ ቢያይ፥ ፊት ለፊት ሊገሰጸው ይገባል። በዚህም ኅብረቱ ንጹህ ይሆናል። ኃጢአቱን አምኖ ንስሀ ከገባ፥ ወደ ኅብረቱ ሊመለስ ይገባል። *"ወንድሞች ሆይ! ሰው ማናቸውንም ስሕተት አድርጎ ቢገኝ፥ መንፈሳውያን የሆናችሁት እናንተ እንዲህ ያለውን ሰው በገርነት አቅኑት፤ ነገር ግን አንተም በዚህ ዐይነት ፈተና እንዳትወድቅ ተጠንቀቅ"* ይላል (ገላት. 6፥1)።

ከመጀመሪያው ጀምሮ የእግዚአብሔር ፍላጎት "እውነትን" ለሰው መግለጽ ነው። እውነትንም ለመግለጽ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ዓለም ላከው። በመስቀል ላይ ከሞተና፥ ትንሳኤን ካገኘ በኋላ በምድር ያለውን አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ አብ ሄደ። በዓለም ውስጥ በአካል እንደ ገና አይታይም። ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስን ልኮ በክርስቶስ አካል ውስጥ፥ ይኸውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ራሱን ገለጸ። በዚህኛው ወቅት በአንድ ሥጋዊ አካል ሳይሆን፥ ልዩ ልዩ ክፍል ባሉት በአንድ መንፈሳዊ አካል ውስጥ ራሱን ገለጸ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት፥ ክርስቶስ በሥጋ በዚህ ዓለም ውስጥ በነበረበት ጊዜ እንደሚያደርገው ክብሩን፥ ጥበቡን፥ ኃይሉንና የእግዚአብሔርን ሙሉ ክብር እየገለጠ ይኖራል። የዚህ አካል ክፍሎች ለሆኑት የእግዚአብሔር ፈቃድና ፍላጎት ምን እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ፥ *"...የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ በእምነት ወደሚገኘው አንድነት ደርሰን፥ ክርስቶስ ፍጹምና ሙሉ ሰው እንደሆነው እኛም ሙሉ ሰው እንድንሆን ነው"* (ኤፌ. 4፥13) ይላል።

የዚህ አካል ክፍል የሆኑት ክርስቶስን ለዓለም ገልጸው ማሳየት አለባቸው። የእግዚአብሔርም ፍላጎትና ዓላማ ይኸው ነው። እያንዳንዳቸው በተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እርስ በርሳቸው ሲተናነጹ፥ የበለጠ አንድ ይሆናሉ። በመንፈስም አንድ ሲሆኑ፥ ዓለም በግልጽ ያያቸዋል፤ በዚህም ምክንያት ምስክርነታቸው ተቀባይነት ያገኛል። ዓለምም የክርስቲያኖችን አንድነት ሲያይ፥ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ የመጣ መሆኑን ያምናል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቲያኖች የመንፈስ አንድነት እንዲህ ይላል፥

እርስ በርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ (1 ጴጥ. 1፥22)።

አንዱ ሌላውን በፍቅር ያገልግል (ገላት. 5፥13)።

እርስ በርሳችሁ ተረዳዱ (ኤፌ. 4፥2)።



እርስ በርሳችሁ ደጎችና አዛኞች ሁኑ (ኤፌ. 4፥32)።

እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ (ቆለ. 3፥13)።

እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ (1 ተሰ. 4፥18)።

እርስ በርሳችሁ ተረዳዱ (1 ተሰ. 5፥11)።

እርስ በርሳችሁ የምትታነጹበትን ነገር ተከተሉ (ሮሜ 14፥19)።

እያንዳንዳችሁ ሌላውን ለመምከር የምትችሉ ሁኑ (ሮሜ 15፥14)።

አንዱ ሌላውን በጥበብ ያስተምር፥ ይምከርም (ቆለ. 3፥16)።

ኃጢአታችሁን እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ (ያዕ. 5፥16)።

እያንዳንዱም ስለሌላው ይጸልይ (ያዕ. 5፥16)።

## 7. የአማኞች መለያየትና መከፋፈል እግዚአብሔርን ያሳዝናል

ቤተ ክርስቲያን ሰው በቀላሉ ሊረዳው የማይችለው፥ በውስጡ ልዩ ልዩ የአካል ክፍሎች ያሉት፥ አስደናቂ የሆነ አንድነትን የሚያሳይ ሕያው አካል ነው።[7] "አንድነት" ማለት ሁሉም ተመሳሳይነት አለው ማለት እንዳልሆነ ቀደም ሲል ገልጸናል። ሁሉም አንድ ዓይነት ከሆነ፥ ሰው ማንነቱንና መለያውን ያጣል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛውን ማንነታችንንና የተፈጥሮ ባሕሪያችንን ሳንተው፥ መብታችንና ስጦታችንን ችላ ሳንል ከሌሎች አማኞች ጋር እውነተኛ አንድነት ሲኖረን ይገባል። በዓለም ውስጥ ይህን ዓይነት "አንድነት" የትም የለም። ቤተ ክርስቲያንም ልዩ ኃይል እንዲኖራት የሚያደርገውም ይኸው አንድነቷ ነው። ወንጌሉንም ለዓለም እንዲያሰሙ የሚያስችላቸው "አንድነታቸው" እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። እግዚአብሔር በልጆቹ አማካኝነት መሥራት ለሚያስበው ነገር ዋና መሠረት የሚሆነው የአማኞች አንድነት ነው።

በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አማኞች በመካከላቸው መለያየትና መከፋፈል ሲኖር፥ እግዚአብሔርን ያሳዝነዋል። አንድነታቸውና ፍቅራቸው ግን ደስ ያሰኘዋል። ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በመሞት ርቀው የነበሩትን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ፤ በመካከላቸው የነበረውንም ልዩነት አጥፍቶ የአንድ ቤተሰብ አባል፥ የአንዱ አካል ክፍሎች በማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ። ቤተ ክርስቲያን አንድነታችንን በተ ብሎ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በውስጣችን ለማኖር የመጣው መንፈስ ቅዱስ፥ የእኛ መለያየት በጣም ያሳዝነዋል። የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንዲከፋፈልና እንዲለያይ ዕድል የምንሰጠው ምን ዓይነት የሥጋ መስኮት መመሪያ ይዘን ነው?

---

[7] Ogden, Greg. The New Reformation. Zondervan Publishing House. Grand Rapids, Michigan, 1990, p. 29.

በክርስቶስ ውስጥ ያገኘነው እርስ በርሳችን ያለን ፍቅርና አንድነት፣ የክርስቶስ ተከታዮች ለመሆናችን መልካም ምስክርነት ይሆናል። ግጭታችንና መለያየታችን ግን ቤተ ክርስቲያንና ክርስትናን መቀለጃ ያደርጋል። ሰው በተፈጥሮ ኃጢአተኛ በመሆኑ በሰዎች መካከል ግጭትና አለመስማማት ብናይ ይህን ያህል አይደንቀንም። ጳውሎስ የሥጋ ሥራዎችን ሲዘረዝር፥ *"...ጠላትነት፥ ንትርክ፥ ቅንአት፥ ቁጣ፥ ራስ ወዳድነት፥ መለያየት አድመኛነት"* ይላል (ገላት. 5፥20)። አንድነትን የሚያጠፉ እነዚህን የመሳሰሉ የሥጋ ሥራዎች ናቸው። ይሁን እንጂ፥ ፈቃደኞች ከሆንን፣ እንደገና አንድ የሚያደርገንን አዲስ ልብ፥ አዲስ መንፈስ እንደሚሰጠን ተስፋ ገብቶልናል። መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን የሚሠራ ከሆነ፥ *"ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግስት፥ ደግነት፥ በጎነት፥ ታማኝነት፥ ቸርነት፥ ራስን መግዛት"* (ገላት. 5፥22-23) በሕይወታችን በግልጽ ይታያል።

የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን የነበራት ጉልበት፥ በአንድነቷ ላይ የተመሠረተ ነበር። በአንድ ልብ፥ በአንድ መንፈስ ለወንጌሉ ጽኑ ሆነው የቆሙ ነበሩ። በአንድነት ውስጥ ያለውን ኃይል የተረዳው ጳውሎስ፣ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን አንድ እንዲሆኑ አጥብቆ ይመክራቸው ነበር። *"ወንድሞቼ ሆይ! መለያየት በመካከላችሁ አይኑር፤ ሁላችሁም ተስማምታችሁ ኑሩ ብዬ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ"* ይላቸዋል (1 ቆሮ. 1፥10)። ለገላትያ ክርስቲያኖች ደግሞ *"ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ስለሆናችሁ በአይሁዳዊና በግሪካዊ በአገልጋይና በጌታ፥ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም"* ይላቸዋል (ገላት. 3፥28)። እግዚአብሔር ቤተሰብን ሲመሠርት፥ በውስጡ የቤተሰብ አባል ሳይኖር አይደለም። አንድ ሕጻን ተወልዶ ወደዚያ ቤተሰብ ውስጥ ሲጨመር፥ አስፈላጊውን እንክብካቤ እየሰጡ እንዲያሳድጉት ያንን ሕጻን ለወላጆቹ ኃላፊነትን ይሰጣል። ሕጻናት ተወልደው የሚያሳድጋቸው ሰው ባይኖር በሕይወት ለረጅም ጊዜ መቆየት አይችሉም ነበር። እግዚአብሔር፥ ሰው ብቻውን እንዲኖር አድርጎ እንዳልፈጠረው ሁሉ፥ በክርስቶስ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የሚጨመሩትም፥ ያለአሳዳጊ ብቻቸውን እንዲኖሩና እንዲያድጉ አላደረገም። ይህን እውነት ያልተረዱ አንዳንድ አማኞች፥ "የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን የለብንም፥ ለብቻችን እምነታችንን ጠብቀን መኖር እንችላለን" ሲሉ እንሰማለን። ይሁን እንጂ፥ አባባላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ያለው አይደለም። አማኞች በአንድ የክርስቲያን ኅብረት ውስጥ ካልታቀፉ፥ ጤናማ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል እየመገበ የሚያሳድጋቸው፥ ከመንገድ ሲወጡ የሚመልሳቸው፥ ሲያጠፉ የሚቀጣቸው ሰው ስለማይኖራቸው፥ ትክክለኛ የሆነ መንፈሳዊ ዕድገት ላይኖራቸው ይችላል።

የክርስቶስ ፍላጎትና ጸሎት በደሙ የዋጃቸው አማኞች "አንድ" እንዲሆኑለት ነው። "የወንጌሉ" የምሥራች ቃል፣ ከእግዚአብሔር ለይቶን የነበረው የኃጢአት ግድግዳ የፈረሰ መሆኑን፣ ከእርሱ ጋር ለመታረቅና አንድ ለመሆን መንገዱ ክፍት እንደሆነ የሚያበስር ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ሳይሆን፥ ከሌሎችም ሰዎች በዘር፣ በጾታ፣ በሕብረተሰቡ ውስጥ ባለን የደረጃ ልዩነት ምክንያት ለይቶን የነበረው ግድግዳም መፍረሱን ያበስራል። *"ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ስለሆናችሁ በአይሁዳዊና በግሪካዊ በአገልጋይና በጌታ፥ በወንድና በሴት መካከል ምንም ልዩነት የለም"* (ገላት. 3፥28) ይላል። "የአንድነት" ምንጩ ከእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው፥ ቤተ ክርስቲያንን *"የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅ በእምነት ወደሚገኘው አንድነት ደርሰን ክርስቶስ ፍጹምና ሙሉ እንደሆነው እኛም ሙሉ ሰው እንድንሆን ነው"* (ኤፌ. 4፥13) ይላል ሐዋርያው ጳውሎስ። በአማኞች አንድነት ውስጥ የሚኖረውን ኃይል የተረዳው ጳውሎስ፥ የሮም ቤተ ክርስቲያን አማኞችን፣ *"እናንተ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች በመሆናችሁ የትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ የአንድነትን መንፈስ ይስጣችሁ። እንዲሁም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነውን አምላክ በአንድ ልብና በአንድ ቃል እንድታከብሩ ያደርጋችሁ"* (ሮሜ 15፥5-6) በማለት ይመክራቸዋል።

## ምዕራፍ ፪

# መሪነት ~ በጸጋ ላይ የተመሠረተ ጥሪ

ከጌታ ጋር በቆየሁባቸው ረጅም ዘመናት ውስጥ፣ የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ሊጠቅሙ የሚችሉ ብዙ ትምህርቶችንና ልምምዶችን አግኝቻለሁ። አብዛኛዎቹ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት ገብቼ የተማርኋቸው አይደሉም። ነገር ግን፣ ገና የማገልገል ብቃት ሳይኖረኝ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቴ በደንብ ሳላድግ ወይም ሳልጎለምስ "እሠራለሁ፤ አገለግላለሁ" ብዬ ከዘላሽኋቸው ነገሮች ውስጥ፣ እንዲሁም እግዚአብሔርን በቅንነት ከሚያገለግሉት ጋር ተሰልፌ ሳገለግል ያገኘኋቸው ትምህርቶች ናቸው። ሳያጠፉ መማር ጥሩ ነበር። ይሁን እንጂ፤ አብዛኛዎቻችን በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ ከስህተት ሁሉ ነጻ ሆነን አላገለገልንም። ብንሳሳትም፣ "ብቃት የለኝም" በማለት ተስፋ ቆርጠን የያዝነውን ጥለን እጆቻችንን አጣምረን ዳር አልቆምንም። እየተሳሳትም ቢሆን ጌታን ለማገልገል ጥሪት የሚያደርጉትን እያየን መታዘዙንና መተቸቱን አልመረጥንም። እየተሳሳትንም ቢሆን እንኳን፣ ከስህተታችን እየተማርን በአገልግሎታችን ገፋንበት። እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ ያበላሸነውንና ያጠፋነውን እያስታወስን ከስህተታችን መማራችን ብቻ ሳይሆን፣ "እኛ እንደተሳሳትነው እንዳትሳሳቱ! ከእኛ ስህተት ተማሩ" በማለት ሌሎችን ማስጠንቀቅና ማስተማር አስቻለን። የሚያሳዝነው ግን አንዳንዶች እኛ ካጠፋነውና ካበላሸነው በመማር ፈንታ፣ "እናንተን አንሰማም፤ እኛው ራሳችን አጥፍተንም ሆነ አልምተን መማር አለብን" በማለት ተመሳሳይ ስህተት የሚፈጽሙ መሆናቸው ነው። ከሌሎች ለመ



ማር ፈቃደኛ አለመሆን፣ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ዕድገቷ መድረስ ካለባት ደረጃ እንዳትደርስ እንቅፋት መሆን፣ ወይም ወደ ኋላ መጎተት እንደሆነ አንዳንዶች የተገነዘቡት አይመስሉም።

## 1. ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የመሪዎች የአመራር ችሎታ ወሳኝ ነው

ከተሰለፍኩበት የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ውጪ፣ አሜሪካን አገር ፔንሴልቬንያ ስቴት ውስጥ፣ ዮርክ እየተባለ ከሚጠራው ከተማ ውስጥ፥ *"ሕያው ቃል" (Living Word)* እየተባለ በሚጠራ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሽምግልና በማገልገል ላይ እገኛለሁ። "ሕያው ቃል" ቤተ ክርስቲያን፥ ከሃያ በማይበልጡ ክርስቲያኖች፥ ከአንድ የግል ሰው ምድር ቤት ውስጥ ከተጀመረች 28 ዓመት ሲሆናት፥ እኔም በዚህች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሃያ አራቱን ዓመት በሽምግልና የማገልገል ዕድል አጋጥሞኝ ዕድገቷንና ፍሬዋን ማየት ችያለሁ። ዛሬ እነዚያ ሃያ ሰዎች ቁጥራቸው እድጎ ከሦስት ሺህ በልጠዋል። ከአንድ የግል ሰው ምድር ቤት ወጥታ፣ ዛሬ ከ8 ሚሊዮን ዶላር በላይ ያወጣ በጣም ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አሠርታ አገልግሎቷን በስፋት በመስጠት ላይ ትገኛለች። የዓመት ባጀቷ ከሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ሲሆን፣ በተጨማሪ በዓለም ዙሪያ ሚስዮናውያንን ለመላክ በዓመት ከግማሽ ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ ታደርጋለች። ስትመሠረት አንድ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ብቻ የነበራት ስትሆን፣ ዛሬ በተለያየ ደረጃና አገልግሎት ተሰልፈው የሚያገለግሉ ሃምሳ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችና ሠራተኞች አሏት። ይህንን ስዘረዝር የቤተ ክርስቲያን ዕድገትና ፍሬያማነት በምታሠራው ሕንጻ፥ በአገልጋዮቿ ቁጥር ወይም ብዛት፣ በሚኖራት የዓመት በጀት ይለካል ማለቴ አይደለም። መንፈሳዊ የሆነውን ነገር በቁጥር መለካት ከባድ ስለሚሆን ነው በዚህች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዳኑትን፥ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የበቁትን፥ ሚስዮናዊ ሆነው በዓለም ዙሪያ የሄዱትን ቁጥር ያልዘረዘርኩላችሁ። ይሁን እንጂ፥ እንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች ካሏት፣ በዓለም ዙሪያ የክርስቶስን ወንጌል እንዴት ማሠራጨት እንደምትችልና እንዲሁም ትልቅ ኃይል መሆን እንደምትችል ተረድቻለሁ። በዚህ ዓይነቱ አገልግሎት ውስጥ ተካፋይ በመሆኔም በጣም ደስ ይለኛል። በዚህች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሽማግሌዎች አንዱ ሆኜ ማገልገል በመቻሌ ብዙ ትምህርቶችንና ልምምዶችን አግኝቻለሁ። በጣም ቅር ሚለኝና የማዝነው ግን፥ ይህን በልምምድ የገኘሁትን ሰፊ የቤተ ክርስቲያን የአመራር ዕውቀት ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ከአሁኑ በበለጠ ሁኔታ፥ ወይም እንደምፈልገው በሰፊው ማካፈል ባለመቻሌ ነው። ይህንን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ዋና ምክንያት የሆነኝ፣ የምጽፋቸውን መጻሕፍት ቁጥር ለማብዛት ሳይሆን፥ ከላይ በገለጽኩላችሁ ሁኔታ ያገኘሁትን ሰፊ ልምምድ ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ ለማካፈል ነው። የዚህችን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴና ዕድገት፥ ዳር ሆኜ የተመለከትኩ ሳልሆን፥ አመራሩ ውስጥ በመሆን ዕድገቷን በቅርብ ያየሁ ነኝ። ውሳኔ ከሚያ

ስተሳልፉት፥ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኒቱን አመራር በቅርብ ከሚከታተሉት ሰዎች አንዱ ሆኜ 24 ዓመት በማገልገሌና አሁንም እያገለገልኩ በመሆኔ፥ ያገኘሁት ልምምድና ትምህርት ለወገኖቼ ይጠቅማል ብዬ ስላመንኩበት፣ ትምህርት እንዲሆነን የዚህችን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንቅሲቃሴ እንደ ምሳሌ አድርጌ አቅርቤላ ችኋለሁ።

በሕይወቴ በሁለት ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ አልፌአለሁ። አንደኛው፣ "በሽማግሌዎች ቦርድ" ብቻ የሚመራ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ በመጋቢና በሽማግሌዎች ቦርድ የሚመራው የአስተዳደር ሥልት ነው። በሁለቱም የአመራር ሥርዓት ውስጥ "ሽማግሌ" ሆኜ አገልግያለሁ። አንደኛው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በነበርኩበት ዘመን ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ከላይ እንደገለጽኩት አሜሪካ ውስጥ በምትገኘው "ሕያው ቃል" ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። የሁለቱንም ዓይነት የአመራር ስልቶች ጥቅምና ጉዳት በቅርብ ሆኜ ተመልክቻለሁ። እዚህ ምዕራፍ ላይ ለመግለጽ የተነሳሁት ሁለቱን ዓይነት አመራሮች ለማወዳደር ሳይሆን፥ የቤተ ክርስቲያን መጋቢና ሽማግሌዎች በሕብረት እንዴት ቤተ ክርስቲያንን በጥሩ ሁኔታ ሊመሩ እንደሚችሉ ለማሳየት ነው። ከላይ የገለጽኩላችሁ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረችው እንዴት ነው? ጀማሪው ማን ነው? ብላችሁ መጠየቃችሁ አይቀርም። ሃያ የሚሆኑ ክርስቲያኖች በአንድ ግለሰብ የምድር ቤት ውስጥ ተሰብስበው የሥነ መለኮት ትምህርቱን የጨረሰውን አንድ የሃያ አምስት ዓመት ወጣት፣ መጋቢ ሆኖ እንዲያገለግላቸው ጠየቁት። ይህም ሰው ከአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተባባሪ መጋቢ ሆኖ አገልግሎቱን ጀምሮ አንዳንድ ያልጠበቃቸው መጥፎ ሁኔታዎች ስላጋጠመው፥ "በመጋቢነት እንዳገለግለው እግዚአብሔር እኔን አይፈልገኝም ይሆናል' የሚል ጥርጣሬ ውስጥ ስለ ነበረ፣ ጥሪውን ለመቀበል ለጥቂት ጊዜ አመነታ። በመጨረሻ ግን በእምነት ጥሪውን ተቀብሎ በመጋቢነት ማገልገል ጀመረ።

ምንም ያህል ትንሽ ብትሆንም ቤተ ክርስቲያኒቱን ለብቻው መምራት እንደማይችል፥ ለመምራትም ቢሞክር ትክክል እንዳልሆነ ስለተረዳ፥ አብረውት የሚያገለግሉ ሦስት ሽማግሌዎችን መርጦ ለምዕመናኑ አቀረበ። ምዕመናኑም ያቀረባቸውን ሦስት ሽማግሌዎች አጸደቁለት። እኔም ትምህርቴን ጨርሼ ቤተ ክርስቲያኒቱ ወደምትገኝበት ስቴትና ከተማ "የኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎትን" ለመጀመር ስመጣ፥ እኔና ቤተሰቤ አብረናቸው ማምለክ ጀመርን። መጋቢው ገና የሥነ መለኮት ትምህርት ተማሪ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ስለምንተዋወቅ፥ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረኝን የረጅም ጊዜ አገልግሎት ስለሚያውቅ በአገልግሎቱ እንድተባበረው ጠየቀኝ። በወቅቱ የነበሩት ሦስት ሽማግሌዎችና መጋቢው እኔ ለሽምግልና ብቃት እንዳለኝና እንደሌለኝ ከመረመሩና ከጸለዩ በኋላ፥ ሁሉም የተስማማበት መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ፥ አራተኛ ሽማግሌ ሆኜ እንዳገለግል እሳቡ ለምዕመን ቀረበ። ምዕመኑም በሙሉ ድምጽ ሽማግሌ ሆኜ እንዳገለግል ፈቅደው አብረዬቸው ማገልገል ጀመርኩ። በነዚህ ሃያ አራት ዓመታት ውስጥ



እውነተኛ መንፈሳዊ ለውጥ ያላቸው፥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ፥ ድብቅ ወይም የተለየ አጀንዳ የሌላቸው መሪዎች ያሏት ቤተ ክርስቲያን ለአለችበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን በዓለም ዙሪያ ለሚካሄደው ታላቅ የወንጌል እንቅስቃሴ ምን ያህል ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ ማድረግ እንደምትችል አይቻለሁ። እንዲሁም ለዚህ ታላቅ ኃላፊነት ጌታ በቦታው ሳያስቀምጣቸው በልዩ ልዩ መንገድ ሥልጣን የያዙ፥ ለግል ጥቅም ሲሉ ቤተ ክርስቲያን ለመምራት በሚሞክሩ ሰዎች ምክንያት የእግዚአብሔር ሥራ ምን ያህል ወደ ኋላ ሊጎተት እንደሚችልም ተገንዝቤአለሁ። "ሕያው ቃል" ቤተ ክርስቲያን አሁን ከደረሰችበት ደረጃ መድረስ የቻለችው፥ በዓለም ዙሪያ ለሚደረገው የወንጌል እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ የረዳት ወይም ያስቻላት ምክንያት ምን ይሆን? ለትምህርታችን እንዲሆን ጥቂቶችን ለመጥቀስ እሞክራለሁ።

## 2. ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት፣ ትክክለኛ መሪዎች አስፈላጊ ናቸው

ለቤተ ክርስቲያን ዕድገትን የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ብዙዎቻችን እናምናለን። ይሁን እንጂ፥ መንፈስ ቅዱስ እንዲሠራ ሰዎችንና አንዳንድ ሁኔታዎችን እግዚአብሔር እንደሚጠቀም አንክድም። ይህንንም በረጅም ዘመን አገልግሎቴ ውስጥ አይቻለሁ። ካየኋቸው መካከል ጥቂቶቹን ለማቅረብ እሞክራለሁ።

እግዚአብሔር ያለሰው ዕርዳታ (ድጋፍ) ብቻውን የፈለገውን ለመሥራት ኃይልና ችሎታ ቢኖረውም፥ ከሰው ጋር ተባብሮ መሥራትን ለምን እንደ መረጠ ግን አናውቅም። የሚተባበረውም ዓላማውን ለመፈጸም ፈቃድና ችሎታ ካለው ሰው ጋር ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ብቻውን ነጻ ማውጣት ቢችልም፥ መሪ ሊኖረው የሚገባ ቀጥተኛ ልብና ቀና መንፈስ ከነበረው ከሙሴ ጋር መተባበርን መረጠ። ሙሴን ለመምረጥ እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሚዛን፥ ሰው ሌላውን ሰው የሚመዝንበት ዓይነት ሚዛን አይደለም። ሚዛኑ ከሰው የተለየ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ስህተት የማይገኝበትና ሀቀኝነት ያልጎደለው ነው። የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማስፈጸም "መሪ" ከፍተኛ ድርሻ ሊኖረው እንደሚችል ስለሚያውቅ ነው እንደ ልቡ የሚሆኑትን አንዳንድ መሪዎች በተለያየ ዘመን ለተለያየ ዓላማ የጠራቸው። በአዲስ ኪዳን ዘመንም ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተመረጡ መሪዎች አስፈልገዋታል። ጥንት ብቻ ሳይሆን በእኛም ዘመን ያለችው ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ መሪዎች ያስፈልጓታል። ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ሆና ማደግ የምትችለው ጤናማ የሆኑ መሪዎች ሲኖሯት እንደ ሆነ ግልጽ ነው።

በዘመናት እግዚአብሔር ለዓላማው የጠራቸውና ለክብሩ የተጠቀመባቸው ሰዎች

*(1) እግዚአብሔርን የሚፈሩትን፣*

*(2) እውነተኛና ንጹህ ልብ ያላቸውን፣*

*(3) የግል ጥቅማቸውን የማይፈልጉትን ነበር።*

በዓለም ውስጥ የደረሱበት ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ፥ ያላቸው የተፈጥሮ ችሎታ፥ ለአገልግሎታቸው ጠቃሚነት ያለው ቢሆንም፣ ለመሪነት ግን የሚያበቃቸው መስኪያ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትም ሥፍራ ተጽፎ አናነብም። ሙሴ ሲሞትና ኢያሱ በቦታው ሲተካ ጥሩ መሪ መሆን የሚያስችለውን ነገር እግዚአብሔር ለኢያሱ የሰጠው ምክር፥

*(1) መንፈሳዊ ብርታትና ድፍረት እንዲኖረው (ኢያሱ 1፥6, 7, 9)፥*

*(2) የሕጉን መጽሐፍ እንዲያነብና እንዲያሰላስል (ኢያሱ 1፥8)፣ እንዲሁም*

*(3) በሙሉ ልቡ ታዛዥ (ኢያሱ 1፥7) እንዲሆን ነው።*

ኢያሱ እነዚህን ነገሮች በሕይወቱ ቢጠብቅ፣ ብልጽግናና እንዲሁም በሕይወቱ መሳካትን እንደሚሰጠው እግዚአብሔር ተስፋ ገብቶለት ነበር። ብዙ ክርስቲያን መሪዎች በአሁኑ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ችላ ብለው በራሳቸው ኃይልና ጥበብ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት ሲሞክሩ ይታያሉ። ያልተረዱት ነገር ቢኖር፥ እግዚአብሔር ለመሪዎች የሚሰጠው ድል የሚገኘው፥ እንደ ቃሉ በመኖር እንጂ፥ ከቃሉ በመውጣት አለመሆኑን ነው።

"ሕያው ቃል ቤተ ክርስቲያን" የዕድገቷ ምክንያት እግዚአብሔርን የሚፈሩ፥ እውነተኞች የሆኑና እንዲሁም የግል ጥቅም የማያሸንፋቸው ሽማግሌዎች (መሪዎች) እንዲሁም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚከተሉ መጋቢዎች ስላሏት ነው። ለመሆኑ ሽማግሌዎችን የሚመርጣቸው ማን ነው? የሚመረጡትስ እንዴት ነው? በሽምግልና የሚያገለግሉት ለምን ያህል ጊዜ ነው? ሽማግሌዎችን ስለ መምረጥና ስለ መሾም መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች በብዙዎቻችን አዕምሮ ውስጥ መመላለሳቸው አይቀርም። ጳውሎስ ለቲቶ ሲጽፍለት፤ *"አንተን በቀርጤስ የተውሁበት ምክንያት የጎደለውን በማሟላት እንድታደራጅና ባዘዝሁህም መሠረት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን በየከተማው እንድትሾም ነው"* ይለዋል (ቲቶ 1፥5)። እዚህ ላይ ቲቶ ሽማግሌዎችን እንዲሾም የታዘዘው ሕዝቡ መርጦ ያቀረበለትን ነው? ወይስ የሚሾመው ራሱ የመረጣቸውን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ አይናገርም። በዚህ ምክንያት ነው የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት በተለያየ መንገድ ሽማግሌዎቻቸውን የሚመርጡት። ስለ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አመራረጥና ብቃታቸውን በመጀመሪያው መጽሐፌ *(የዘመናችን ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ)* ላይ በሰፊው የተጻፈ ስለሆነ፥ መጽሐፉን በጥንቃቄ እንድታነቡት ይሁን።

እዚህ ላይ አሳቡን ያነሳሁት እኔ በማገለግልበት "በሕያው ቃል" ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ምን ዓይነት መንፈሳዊ አቋም እንዳላቸውና በጌታ የተሰጣቸውን ኃላፊነት



እንዴት እንደሚፈጽሙ ለማሳየት ብቻ ነው። "ሕያው ቃል" ሽማግሌዎቿን የምትመርጠው በምን ዓይነት መንገድ ነው? ሽማግሌዎቹ ተመርጠው በአገልግሎት ላይ የሚቆዩትስ ለምን ያህል ጊዜ ነው? ከላይ እንደገለጽኩት፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ገና ስትጀመር፤ መጋቢው ሦስት ሰዎችን ከመረጠ በኋላ ለምዕመኑ እንዳቀረበና ምዕመኑ መጋቢው ያቀረባቸውን እንዳጸደቀ ተመልክተናል። የቤተ ክርስቲያኒቱ አባሎች ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ፥ ሽማግሌዎች እንዲጨመሩ በሚያስፈልግበት ጊዜ፥ ዋናው መጋቢ ከምዕመናኑ መካከል ለሽምግልና ብቃት አላቸው ብሎ የሚያምናቸውን ሰዎች ስም ለሽማግሌዎች ቦርድ ያቀርባል። የሽማግሌዎችም ቦርድ የቀረቡትን ሰዎች መንፈሳዊ አቋም በደንብ ካጠናና ከጸለየ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል። ውሳኔ የሚወሰነውም በድምጽ ብልጫ ሳይሆን፥ መቶ በመቶ ወይም ሁሉም የተስማማበት ከሆነ ብቻ ነው። ከሽማግሌዎች መካከል አንድ ሰው በልቡ ውስጥ ደስ ባይለው፥ ያ ሰው በሽምግልና አይመረጥም። የሁሉም ልብ ከደገፈው ግን፥ የተመረጠው ሰው ለምዕመናን ጉባኤ ቀርቦ "ይሁን" ወይም "አይሁን" የሚል ውሳኔ ይሰጥበታል። ለምዕመናን ጉባኤ ከመቅረቡ በፊት፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢዎችና ሽማግሌዎች ጸልየውና እንደሚገባው አስበውበት እንደሚያቀርቡት ጉባኤው ስለሚያምን፥ ያለምንም ጥያቄ ይቀበለዋል። በአሁኑ ወቅት በዚህ ዓይነት የተመረጡ አሥራ አንድ ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያኒቷን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ከአሥራ አንዱ ውስጥ ዋናው መጋቢና ሁለት ተባባሪ መጋቢዎች ይገኙበታል። ሦስቱም መጋቢዎች ራሳቸው ሽማግሌዎች ናቸው። በሽምግልና የሚመረጡት ለተወሰነ ዓመት ሳይሆን እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ነው። ስለዚህ ነው እኔም ሃያ አራት ዓመት በሽምግልና እያገለገልኩ የቆየሁት። አንድ ሰው ከሽምግልና አገልግሎቱ የሚወርደው፣ 1) በኃጢአት ሲወድቅ፣ 2) አገልግሎቱን በተለያየ ችግር ምክንያት መፈጸም ሲያቅተው፥ እንዲሁም 3) ከተማውን ለቅቆ ሲሄድ ብቻ ነው።

እነዚህ አሥራ አንድ ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያኒቷ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ መሪዎችና ተጠያቂዎች ናቸው። እነዚህ መሪዎች የራሳቸው መሪ አላቸው። እርሱም ዋናው መጋቢ ነው። ዋናው መጋቢ የቤተ ክርስቲያኒቷና እንዲሁም የመሪዎች መሪ ይሁን እንጂ ለማንም ተጠያቂነት የሌለው፣ ለብቻው የቆመ አይደለም። እርሱ ራሱ ለሽማግሌዎች ቦርድ ተጠያቂነት አለው። ሽማግሌዎችም ለዋናው መጋቢ እንደ አለቃ ሆነው የሚቆጣጠሩት ሳይሆኑ፥ በፈቃዱ ራሱን በእነርሱ ሥር ያደርጋል። ዋናው መጋቢ ከሽማግሌዎች አንዱ ቢሆንም፥ ከሌሎች ሽማግሌዎች ጋር ሆኖ የማይወስነው ነገር ቢኖር፥ እርሱን በሚመለከት ጉዳይ ላይ ብቻ ነው። ይኸውም የመጋቢውን ደሞዝ፥ በየዓመቱ የሚደረግለት የደሞዝ ጭማሪና የዕረፍት ጊዜውን እርሱ በማይገኝበት ስብሰባ የሽማግሌዎች ቦርድ ይወስናል። የሽማግሌዎችን ስብሰባ በሊቀ መንበርነት የሚመራው ዋናው መጋቢ ነው። መጋቢው የቤተ ክርስቲያኒቱን ራዕይና ፕሮግራም ለሽማግሌዎች ያቀርባል። ከሽማግሌ

ዎች ጋር በመተባበር ራዕዩዋ ተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል። መንጋውን በማስተማርና በመስበክ የሚያገለግለው ዋናው መጋቢ ብቻ ነው። ሁለቱ ተባባሪ መጋቢዎችና ሽማግሌዎች ተራ ጉብተው አይሰብኩም። ዋናው መጋቢ በማይኖርበት ጊዜ ብቻ ተባባሪ መጋቢዎቹ ይሰብካሉ። እነዚህ ተባባሪ መጋቢዎች ዕሁድ በሚደረገው ስብሰባ ላይ አይሰበኩ እንጂ፤ በቤተ ክርስቲያኒቷ ውስጥ ሰፌ የአገልግሎት መስክ አላቸው። አንደኛው፥ የቤተሰብ አገልግሎት (Family Life Ministry) መጋቢ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ "የመሪዎች ማጎልበት" (Leadership Development) መጋቢ በመሆን ከፍተኛ አገልግሎት ይሰጣሉ። በተጨማሪ የልዩ ልዩ ፕሮግራም ድሬክተሮችና ረዳቶቻቸው በተለያየ መስክ ተሰልፈው በሙሉ ጊዜ ቤተ ክርስቲያኒቱን ያገለግላሉ።

"ሕያው ቃል ቤተ ክርስቲያን" ከሦስት ሺህ በላይ የሆኑ ምዕመናን አሏት። ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው፥ ከሠላሳ እስከ አርባ የሚደርሱ ሐኪሞች (ዶክተሮች)፥ ብዙ የሕግ ባለሞያዎች፥ ዳኞች፥ ከፍተኛ የሂሳብ ባለሞያዎች፥ መሀንዲሶች፥ መምህራኖች፥ የጤና መኮንኖች፥ ከፍተኛ የአስተዳደር ባለሙያዎች ይገኙበታል። ይህንን የገለጽኩበት ዋና ምክንያት፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ትልቅነት አጉልቶ ያሳያል በማለት ሳይሆን፥ ለቤተ ክርስቲያን መሪነት የተመራጭነት ብቃት የሚሰጠው አማኝ ያለው የትምህርት ደረጃና በሕብረተሰቡ መካከል ያሰው ክብርና ተቀባይነት ወሳኝ አለመሆኑን ለማሳየት ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ከሚፈጠርባቸው ምክንያቶች መካከል አንደኛው፥ የአማኙ መንፈሳዊ ሕይወት እንደሚገባ ሳይመዘን፥ በዓለም ውስጥ ባላቸው ደረጃ ብቻ ተለክተው በመሪነት በሚመረጡ ሰዎች ምክንያት ነው። ከፍተኛ ትምህርትና እንዲሁም በዓለም ውስጥ ትልቅ ደረጃ ያላቸው አማኞች ለመሪነት ብቁ አይሆኑም፥ ወይም አያስፈልጉም ማለት ሳይሆን፥ መመዘኛው ያ ሊሆን አይገባም ማለታችን ነው። "ሕያው ቃል" ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሽማግሌዎች በየሁለት ወይም ሦስት ዓመት የሚለዋወጡ ስላልሆኑ፥ ከመመረጣቸው በፊት ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረጋል። ሽማግሌዎች ከፍተኛ መንፈሳዊ አቋም፥ እውነተኛ የሆነ የሕይወት ለውጥ ያላቸው፥ በክርስትና ሕይወታቸው አዲስ ያልሆኑ፥ ጌታን በቅን ልብ ከማገልገል በቀር ሌላ ድብቅ አጀንዳ የሌላቸው፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ መልካም ስም ያላቸው፥ እንዲሁም ከሰው ጋር አብሮ መሥራት የሚችሉ፥ እስቸጋሪ ጠባይ የሌላቸው መሆን አለባቸው። "ባለበት መሥሪያ ቤት ዋና መሪ ወይም ኃላፊ ነው፥ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያለው አዋቂ ሰው ነው፥ ወይም ብዙ ገንዘብ ያለው ሀብታም ስለሆነ ቤተ ክርስቲያኒቱን በገንዘብ ይረዳልና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ አድርገን እንምረጠው" የሚል የለም። ባለው ከፍ ተኛ ደረጃ የሚመረጥ ቢሆን ኖሮ አሁን በሽምግልና ከምናገለግለው ውስጥ አብዛኛዎቻችን ቦታ የለንም ነበር።

ሽማግሌዎቹ የእግዚአብሔር ሰዎች፥ የራሳቸውን ምኞትም ሆነ ፍላጎት ማስፈጸም የማይታገሉ፥ ከሌሎች ተልቀው ለመታየት ጥረት የማያደርጉ በመሆናቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ አመራር ፍጹም ጤናማ ነው። በ24 ዓመት የሽምግልና አገልግሎቱ ውስጥ አንድም ጊዜ ተጣልተንና ተጨቃጭቀን መሠራት ያለበት ነገር ሳይሠራ የቀረበት ጊዜ የለም።



ከላይ እንደ ገለጽኩት ውሳኔ የምንሰጠው በድምጽ ብልጫ አይደለም። ከአሥራ አንዱ ሽማግሌዎች መካከል አንዱ ካልተስማማ ምንም ዓይነት ውሳኔ አናደርግም። ጊዜ ወስደን እንድንጸልይበት ይተዋል። ሁልጊዜ መቶ በመቶ መስማማት እንዴት ይቻላል? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። የምንሰበሰበው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም፥ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት እንጂ፥ የራሳችንን ፍላጎት ለማስፈጸም፥ ራሳችንን ለማሳደግና ለማሳየት እንዳልሆነ ሁላችንም እናውቃለን። እያንዳንዱ ሽማግሌ የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት፥ ፈቃዱን ለማወቅ እንዲያስችለው፥ የግል ሕይወቱን ስለሚጠብቅ፥ እግዚአብሔር የሁላችንንም ልብ የሚያሳርፍ ሀሳብ ይሰጠናል። የሁላችንም ልብ አንድ ዓይነት ሳይሆን የተውናቸው ነገሮች፥ ከጊዜ በኋላ ሁኔታውን ስንመረምር፥ ልናስተላልፍ የነበረው ውሳኔ ልክ እንዳልነበረ የተገነዘብንበት ጊዜ ብዙ ነው። ለአሥራ አንዱ ሽማግሌዎች ውሳኔው ተስማምቷቸው ለአንዱ ብቻ ካልተስማማው፥ ያልተስማማው ሰው የእኔ አሳብ ይሁን ብሎ በመከራከርና በመጨቃጨቅ ፈንታ እንዲህ ይላል፥ "ወንድሞቼ! ይሄ ነገር ለሁላችሁም ሲታያችሁ ለእኔ አልታየኝም። ችግሩ የእናንተ ሳይሆን የእኔ ሊሆን ይችላልና፥ እናንተን ወንድሞቼን አምናችኋለሁና አሳባችሁን እንደ ራሴ አሳብ እቀበለዋለሁ" ይላል። ይህ በሚሆንበት ወቅት ምንም ዓይነት ቅሬታ አንዱ በሌላው ላይ አይኖረውም።

## 3. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመሪነት ብቃታቸው በምን ይለካል?

"ሕያው ቃል ቤተ ክርስቲያን" ሌላው የዕድገቷ ምክንያት እግዚአብሔርን የሚፈራ፥ እውነተኛ የሆነና እንዲሁም የግል ጥቅም የማያሸንፈው መጋቢ (ፓስተር) ስላላት ነው። የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚገባው ለመምራት የሚቻለው፥ በመጋቢዎችና በሽማግሌዎች መካከል የተቀራረበ ግንኙነትና አንድነት ሲኖር ነው። መጋቢው በሽማግሌዎች ላይ፥ እንዲሁም ሽማግሌዎች በመጋቢው ላይ እምነት ሊኖራቸው ይገባል። ይህም መተማመን እንዲሁ የሚመጣ ሳይሆን፥ መጋቢው በችሎታውና በጥሩ ክርስቲያን ባሕሪው የእነርሱን ልብ ወደ እርሱ መሳብ መቻል አለበት። መሪ የሆነ ሰው፥ ከሌሎች መሪዎች "እጅግ በጣም ጥሩ" የሆነ ውጤትን ይጠብቃል። መተማመን የሚጀምረው "በችሎታ" ነው። ችሎታ የሌለውን ማመን ከባድ ነው። የቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና እንዲሁም ሽማግሌዎች፥ መጋቢው ችሎታ ያለው እንዲሆን ይፈልጋሉ። ችሎታውን የሚጠራጠሩትን ሰው እንደ መሪ አድርጎ መቀበል ያስቸግራል። "ችሎታ" ስንል፥ በአንድ ብቻ ሳይሆን በተለያየ አቅጣጫ ነው። ይኸውም፥

## 3.1. በማስተማር ችሎታቸው

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ፣ መጋቢ "ለማስተማር ችሎታ ያለው" (1 ጢሞ. 3፥2) መሆን አለበት። ዛሬ በተለይ በኢትዮጵያውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል መጋቢ ተብለው የተቀመጡትን የማስተማር ችሎታቸውን ስንመዝን፥ እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ እናዝናለን። አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት "መጋቢ እንፈልግም። እኛው ራሳችን ተራ እየገባን እንሰብካለን" የሚሉበት ምክንያት አንደኛው ይሄ ሳይሆን አይቀርም ብለን እንገምታለን። መጋቢ ያላቸውም ስብከቱ በፈረቃ እንዲሆን ከሚፈልጉበት ምክንያት አንደኛው መጋቢ ተብሎ በተቀመጠው ሰው የማስተማር ችሎታ እምነት ስለሌላቸው ነው። በክርስቲያን አምልኮት ውስጥ መካከለኛውን ሥፍራ መያዝ ያለበት የእግዚአብሔር ቃል ቢሆንም፥ የማስተማር ችሎታቸው አነስተኛ ስለሆነ፥ ወይም ለሕዝቡ የሚሰጡት ቃል ስለሌላቸውና ቶሎ ስለሚያልቅባቸው ነው ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ "መዝሙር" ከፍተኛውን ሥፍራ የያዘው። አብዛኛዎቹ የማስተማር ችሎታቸው ተመዝኖ ወይም የማስተማር ስጦታ እንዳላቸው ታውቆ ሳይሆን፥ በተለያየ መንገድና ሁኔታ የመጋቢነቱን ሥልጣን ያገኙ ናቸው። ብዙዎቻችን መሰበክ የጀመርነው ትምህርት ቤት ገብተን የአሰባበክ ሥርአተ ትምህርት (homiletics) ተምረን አይደለም። ይሁን እንጂ ለመማር ዕድሉ ሲያጋጥመን "ትምህርት አያስፈልገንም" አላልንም። አንዳንድ መጋቢ ዎች ተምረው ራሳቸውን የበለጠ ማሻሻል ዕድሉ እያላቸው በስንፍና ምክንያት ከነበሩበት የማይንቀሳቀሱ አሉ። ትምህርት ቤት ገብተው በመማር፥ ልዩ ልዩ መጽሐፍትን በማንበብ ራሳቸውን ማሻሻል ሲችሉ፥ "ትልቅ ነው" ብለው ያሰቡትን ሰባኪ ኮፒ በማድረግ ብቻ ለመስበክና ለማስተማር የሚሞክሩ አሉ። ኮፒ እንዳደረጉት ሰው ይጮኻሉ፥ መድረክ ላይ ይሮጣሉ፥ እጃቸውን ያወራጫሉ። እነዚህ ነገሮች በአሰባበክ ሥርዓት ውስጥ መጠናቸውን ካልጠበቁ ትክክል እንዳልሆኑ አያውቁም።

"ሕያው ቃል ቤተ ክርስቲያን" የዕድገቷ ሌላው ምክንያት መጋቢው ለእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠው ከፍተኛ ሥፍራ ነው። ግሩም የሆነ የአምልኮት ጊዜ አለን። በዝማሬ ሕዝቡ ጌታውን ለግማሽ ሰዓት ያህል በነጻነት ያመልካል። ይሄም ምዕመኑ ልቡን ለእግዚአብሔር ቃል እንዲያዘጋጅ እንጂ፥ ዘምሮ ወደ ቤቱ እንዲሄድ አይደለም። መጋቢው እንደሚገባ ተዘጋጅቶ በየሳምንቱ መንጋውን ከእግዚአብሔር ቃል የሁሉንም ልብ፥ በሁሉም አቅጣጫ እንዲነካ አድርጎ ያቀርባል። የመጋቢዎች ትልቁ ሥራቸው መንጋውን ጠቃሚና እንዲሁም ተመጣጣኝ የሆነ መንፈሳዊ ምግብ መመገብ ነው። ሳይመግቡ "መጋቢ" ብሎ ራስን መጥራትም ሆነ መጠራት ልክ አይደለም። "መጋቢነት" የአገልግሎት ዓይነት እንጂ ሹመት አይደለም። ወታደር የነበረ ሰው፥ በአገልግሎቱ "ኮሬኔል" ደረጃ ደርሶ ከወታደርነት ቢወጣ፥ ማዕረጉን ይዞ "ኮሬኔል እከሌ" እየተባለ ይጠራል። መጋቢ የነበረ ሰው ግን ከመጋቢነት አገልግሎት ከወጣ፥ የሚመግባቸው መንጋዎች ከሌሉት፥ መጋቢነት "ሹመት" ስላልሆነ፥ "መጋቢ እከሌ" ተብሎ መጠራት ትክክልነቱ አይታየኝም። ቃሉን የመመገብ ችሎታ ሳይኖረው፥ መድረኩ በፈረቃ የሚያዝ፥ ወይም ኮንፍራንስ እያዘጋጁ ሌሎችን በመጥራት የሚሞላ ከሆነ፥ መጋቢው ለማስተማር ብቃት እንደሌለው ያሳያል። የሽማግሌዎች ቦርድ በመጋቢው ላይ የሚኖራቸው እምነት በጣም አነስተኛ ይሆናል። ብዙ ዓመት በመጋቢነት ያገለገሉ "ቢል ሎረንስ" (Bill Lawrance) እንዲህ አሉ፥



> *"በተመሳሳይ ሰዓት በየሳምንቱ ሠላሳ ወይም ሠላሳ አምስት ደቂቃ በሚሰብከው ስብከት ምን ያህል የሰው ሕይወት አንደተነካ የሚታይበት፥ እኔ የማውቀው ከመጋቢነት ሥራ ውጪ ሌላ የለም። መጋቢዎች የሆንን ያለብንን ከፍተኛ ኃላፊነት ተገንዝበን፥ በስብከታችንና በትምህርት አቀራረባችን እጅግ በጣም ጥሩ ከሚባልበት ደረጃ ለመድረስ በተቻለን መጠን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባናል። የሽማግሌዎች ቦርድ፤እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት በእኛ ላይ እምነት እንዲኖራቸው ስብከታችንን ጥሩ ለማድረግ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን።"*[8]

## 3.2. ከሰዎች ጋር በሚኖራቸው ጥሩ ግንኙነት

አንዳንድ መጋቢዎች ምንም ያህል ያገልግሎታቸው ሁኔታ ከብዙዎች ሰዎች ጋር የሚያገናኛቸው ቢሆንም፥ ከሚያገለግሉት ሕዝብ ጋር እንዴት መቀራረብ እንደሚችሉ ባለማወቃቸው የተነሳ በተቻላቸው መጠን ከሰው ለመሸሽ፥ በእነርሱና በሚያገለግሏቸው ሰዎች መካከል ገደብ ለማበጀት ይሞክራሉ። ከሕዝቡ ጋር ቅርበት የሌለውን መጋቢ ማመንና መቀበል የሚችል ማን ነው? መጋቢዎች ክርስቶስ በሚሰጣቸው ኃይልና ጸጋ እየተጠቀሙ ከሚያገለግሉት ሕዝብ ሳይሸሹ፣ ከእግዚአብሔር በአደራ የተሰጣቸውን ሕዝብ ቀረብ ብለው ማገልገል መቻል አለባቸው። በአንዳንድ የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ መጋቢያቸውን ለማነጋገር ዕድል በማጣት ከስድስት ወር በላይ የሚጠብቁ እንዳሉ ሰምቻለሁ። ከሰዎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት፣ መጋቢዎች የሚያገለግሏቸው ምዕመናንም ሆኑ የሽማግሌዎች ቦርድ በእነርሱ እምነት እንዲኖራቸው፥ ከሕዝቡ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት መፍጠር መቻል አለባቸው። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሚያገለግሉት ሕዝብ ጋር የተቀራረበ ግንኙነት የማይኖራቸው ለምን ይሆን?

- ምናልባት ሰዎች በትክክል የማይረዱቸው ከሆነ፥ "ለምን ሰዎች አይረዱኝም?" ብለው መልሱን ከሌሎች ለመስማት ከመጠበቅ ይልቅ፥ የሚያገለግሏቸውን ምዕመ

---

[8] *(Lawrence, Bill, Effective Pastoring, 1968, p. 129)*

ናንን የበለጠ ለመረዳት የራሳቸውን ጥረት ማድረግ አለባቸው። ሰው ሁሉ የተለያየ ተፈጥሮና ባህሪ እንዳላው ሲረዱ፥ ሁሉም ሰው እንደ እኛ መሆን አለበት የሚለውን እምነታቸውን ይተዋሉ።

- ከሚያገለግሏቸው ሰዎች ጋር የተቀራረበ ግንኙነት እንዲኖራቸው፥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሚያለቅሱት ጋር ለማልቀስ፥ ከሚስቁት ጋር ለመሳቅ ራሳቸውን ማለማመድ አለባቸው።
- መጋቢዎች (የቤተ ክርስቲያን መሪዎች) ሁሉን ነገር የማያውቁ መሆናቸውን ሲረዱ፥ ለመማር ፈቃደኞች ይሆናሉ። በሚያጋጥማቸው ዕድል ሁሉ ከዚህ በፊት ያላወቁትን ለማወቅ፥ ያልተማሩትን ለመማር በአዕምሯቸው የተዘጋጁ ይሆናሉ። ይሄም የሚያገለግሉትን ሕዝብ የበለጠ ለመረዳት ያስችላቸዋል።
- መጋቢዎች አገልግሎታቸውን ሲሰጡ አንዳንድ የሚደርስባቸውን ጉዳት በትዕግስት ተቀብለው ለማለፍ ራሳቸውን ማለማመድና ማዘጋጀት አለባቸው። ይሄም ከሚያገለግሉት ሕዝብ እንዳይሸሹ ያደርጋቸዋል። የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ከሰው ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት መፍጠር የሚችሉ ከሆነ፥ ምዕመኑ ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው የሚያገለግሉ ሽማግሌዎችም በእነርሱ ላይ እምነት ይኖራቸዋል።

## 3.3. ባላቸው የማገልገል ችሎታ

መጋቢዎች የሚያገለግሉት ሕዝብ ዕርዳታ በሚፈልግበት ሰዓትና ጊዜ በቦታው ተገኝተው ለመደገፍ፥ ለማበረታት ፈቃደኝነታቸውን ማሳየት አለባቸው። በመከራ፥ በችግርና በፈተና ውስጥ የሚያልፉትን በርህራሄና በፍቅር ተሞልተው የሚያገሉ መጋቢዎች፥ እነርሱ ያደረጉትን ቢረሱ እንኳን ከተደረገላቸው ሰዎች ልብ ድርጊታቸው ፈጽሞ አይጠፋም። ለአንዳንድ ሰዎች ከሰው ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ለመፍጠር ከባድ ነው። ጥሩ አድርገው መስበክ፥ ጥሩ አድርገው ማስተማር ይችላሉ። ከሰው ጋር ግን የተቀራረበ ጥሩ ግንኙነት ማድረግ ግን አይሆንላቸውም። በዚህ ተፈጥሯዊ ባሕሪያቸው ምክንያት "እኔ ስመጋቢነት እስማማለሁ ወይ? እግዚአብሔር እንዳገለግለው የሚፈልገው በዚህ መስመር ነው ወይ?" ብለው ራሳቸውን የሚጠይቁ አሉ። ጥሩ ጥያቄ ነው። ይሁን እንጂ፥ በዚህ አቅጣጫ እግዚአብሔር እንዲረዳቸው መጸለይ፥ እንዲሁም ራሳቸውን ለማሻሻል የግል ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል። መጋቢዎች የሚያገለግሉት ሕዝብም ሆነ አብረዋቸው የሚያገለግሉ አገልጋዮች በእነርሱ ላይ እምነት እንዲኖረው፥ ከሰው ሁሉ ጋር ጥሩ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል።



# 4. ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት፥ የመሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት አስፈላጊ ነው

በቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አምልኮ ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል መካከለኛውን ቦታ መያዝ አለበት። የእግዚአብሔር ቃል የሌለበት ቤተ ክርስቲያን ጤናማነቱ ያጠራጥራል። ከሦስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ አማኞች ቅዱስ ቃሉን ያከብሩ እንደ ነበረ ታሪክ ያመለክራል። ቃሉ ሲነበብና ሲሰበክ ቆሞ መስማት ከአምልኮታቸው ክፍል ከፍተኛውን ሥፍር የያዘ ነበር። በመካከሉ ግን ቃሉ በሃይማኖት ሥርዓቶችና ልምምዶች እየተተካ መጣ። በመካከለኛው ክፍለ ዘመን፤ ከተሃድሶ በኋላ በቤተ ክርስቲያን አምልኮት ውስጥ ችላ ተብሎ የነበረው የእግዚአብሔር ቃል እንደ ገና መካከለኛውን ሥፍራ መያዝ ቻለ። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚናገርበት ዋናውና ትልቁ መንገድ በቃሉ ነው። ለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን *"ቃሉን ስበክ፥ ቢመችም ባይመችም በማንኛውም ጊዜ ተግተህ ሥራ፥ እያስረዳህ እየገሠጸህና እየመከርህ በትዕግሥትና በማስተማር ጽና"* ብሎ የመከረው (2 ጢሞ. 4፥2)። ከማንኛውም ነገር የበለጠ፥ ዓለም የአዳኙን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል መስማት አለበት። የመስቀሉ ቃል በምንም ዓይነት ችላ ሊባል አይገባም። ጳውሎስ ይህን ቃል የመስበክ ግዴታ እንዳለበት ሲገልጽ፤ *"የምሥራቹን ቃል ማብሠር ግዴታዬ ስለሆነ የምመካበት ነገር አይደለም፥ እንዲያውም የምሥራቹን ቃል ሳላበሥር ብቀር ወዮልኝ!"* ይላል (1 ቆሮ. 9፥16)። መጋቢው የቃሉ ዕውቀት ከሌለው፣ ለማወቅም የራሱን ጥረት የማያደርግ ከሆነ፣ ምዕመናኑን እንዴት መመገብ ይችላል?

እኛ ባለንበት በዚህ ዘመን፣ የእግዚአብሔር ቃል መካከለኛውን ወይም ዋናውን ሥፍራ እንዳያጣ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ የመሪዎች ኃላፊነት ነው። በእኛ የክርስትና ዘመን እንኳን ለእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠው ጊዜ በጣም እየቀነሰ ሲመጣ እናያለን። በቤተ ክርስቲያን አምልኮት ውስጥ ብዙ ጊዜ ሲሰጠው የምናየው መዝሙር መዘመር ነው። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ለመዝሙር የሚሰጠው ጊዜ ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ሰዓት ነው። አምልኮቱን የሚመራው ሰው ለረጅም ጊዜ እዘምሮ ሲቀመጥ፥ መጋቢው ወይም በወቅቱ የሚሰብከው ሰው ቃሉን ለማቅረብ በቂ ዝግጅት እንዳላደረገ ሲያውቅ፥ ወይም የሚሰጠው አዲስ ነገር የሌለው ከመሰለው፥ ጉባኤውን መውቀስ ይጀምራል። "ለጌታ የምትዘምሩት እንደዚህ ነው ወይ?" በማለት እንደገና ሞቅ ባለ ሁኔታ ማስዘመር ይጀምራል። የሚያሳዝነው ረጅሙን ጊዜ በዝማሬ የሚያሳልፉት ቆመው መሆኑ ነው። ከሁለትና ከሦስት ሰዓት ዝማሬ በኋላ አብዛኛው ሕዝብ ስለሚደክም፥ ቃሉን የመስማት ጉልበት ያጣል። በየሳምንቱ የአምልኮቱ ሁኔታ በዚህ ዓይነት የሚሆን ከሆነ፥ ሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወቱን የሚያሳድግበት መንፈሳዊ ምግብ ስለማያገኝ፥ ፈተናና ትግል በሕይወቱ ሲያጋጥመው በቀላሉ ይወድቃል።

በዚህ ዘመን፥ ሰዎች መስማት የሚፈልጉት ነገር፥ ከጊዜው ጋር አብሮ የሚሄደውን ስለሆነ፥ ፍላጎታቸውን እያየን መስበክና ማስተማር አለብን ብለው የሚያምኑ አንዳንድ አስተማሪዎችና ሰባኪዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። በዘመናችን አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ከአምልኮት ክፍላቸው ውስጥ ስብከት አንደኛው ይሁን እንጂ፥ ከመድረካቸው ላይ የሚያስተላልፉት ቃል መልኩን እየሰወጠ መጥቷል። እንደ ክርስቶስ አምባሳደር፥ መጋቢዎች ወይም ቃሉን የሚሰብኩ፥ ለቃሉ ታማኞች በመሆን የሰውን ሕይወት ለመለወጥ ኃይል ስላለው ስለ ክርስቶስ፥ እንዲሁም ያለ ክርስቶስ ሰው መጨረሻው ምን እንደሚሆን ማሳወቅ አለባቸው። ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል ችላ ብለው፥ ሌላ እነርሱ የሚፈልጉትን ዓይነት መልዕክት ብቻ ለመስማት ስለሚፈልጉ ሰዎች ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት፤ *"...ሰዎች ንጹሑን ቃል ለመስማት የማይፈልጉበት ጊዜ ይመጣል፥ ነገር ግን ለወሬ በመጎምጀት እነርሱ ራሳቸው የሚወድዱትን ነገር የሚነግሩአቸውን አስተማሪዎች ይሰበስባሉ"* (2 ጢሞ. 4፥3) አለው።

## 5. ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት፥ የመሪዎች የማይነቀፍ ጠባይ አስፈላጊ ነው

"ሕያው ቃል ቤተ ክርስቲያን" ለዕድገቷ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገው ሌላ ነገር፥ መጋቢዎቹም ሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የማይነቀፍ ክርስቲያናዊ ጠባይ ያላቸው በመሆኑ ነው። መጋቢዎች ራሳቸውን ከነቀፋ በላይ ማድረግ ያለባቸው በሚሠሩት ሥራ ብቻ ሳይሆን፥ ሆነው በሚገኙት ባሕሪያቸውም ጭምር ነው። ከላይ በገለጽናቸው ነገሮች መጋቢዎች ችሎታ ያላቸው ሲሆኑ፥ በጥሩ ባሕሪም እያደጉ ሲመጡ ይታያሉ። "ድርጊታችን ከመሆናችን" ጋር ግንኙነት የሌለው ወይም የተራራቀ አይደለም። ብዙ ጊዜ ደጋግመን የምናደርገውን የመሆን ዝንባሌ አለን። አንዳንድ ጊዜ በባሕሪ ድክመት የተነሳ የምናደርገው ነገር ደካማ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ለዚህ ነው በባሕሪያችንና በችሎታችን መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው። ሰዓት የማናከብር ከሆነ፥ በባሕሪያችን ግዴለሾች መሆናችን ይታወቃል። መጋቢዎች በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ጥሩ ለመሆን፥ በህልውናቸው ጥሩዎች መሆን አለባቸው።

አንዳንዶች በሕዝብ ዘንድ ቆመው መስበከም ሆነ ማስተማር የሚፈሩበት ምክንያት አላቸው። የፍርሃታቸው አንደኛው ምክንያት ጥሩ ያልሰበኩ እንደሆነ፥ የተበላሸብኝ እንደሆን በማለት ይሆናል። ጥሩ ካልሰበኩ፥ በሌላ ነገር ለመካስ ይሞክራሉ። ምዕመናኑን የበለጠ ይጎበኛሉ፥ የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፥ በማስተዳደር ጥሩ ውጤት ለማምጣት ይሞክራሉ። ይሄ ሁሉ ጥሩ ነው። ይሁን እንጂ ይሄ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ምትክ ወይም መካሻ መሆን አይችልም። ለምን ጥሩ እንዳልሰበኩ ራሳቸውን ቢጠይቁ ምክንያቱ የተሰወረ አይደለም። ትልቁ ምክንያት የዝግጅት ማነስ፣ በቂ ጊዜ ወስደው አለመጸለያ



ቸው ሊሆን ይችላል። እንዲሁም የራሳቸውን መንፈሳዊ ሕይወት ለማሳደግ ጊዜ ወስደው የተለያዩ መንፈሳዊ መጽሐፍትን የማያነቡ በመሆናቸው ይሆናል። የአንዳንዶቹ የዝግጅት ማነስ ዋና ምክንያት ሌላ ነገር ሳይሆን "ስንፍና" ነው። ስንፍና ደግሞ የጥሩ ባሕሪ ምልክት አይደለም (ምሳሌ 26፥15-16)። መጋቢዎች ለሚሰብኩት ወንጌል እውነተኞች መሆን አለባቸው። ችሎታ የሚፈጠረው ከጥሩ ጠባይ ውስጥ ነው። መጋቢዎች በሚሠሩት ሥራም ሆነ በባሕሪያቸው ራሳቸውን ብቁ ለማድረግ የሚያደርጉትን ጥረት ተገልጋዮቹም ሆኑ አብረዋቸው የሚያገለግሉት ሰዎች ስለሚያዩ ጥረታቸውን ማድነቅ ብቻ ሳይሆን በእርሱ ላይ እምነት ይኖራቸዋል።

መጋቢዎች የተሰለፉት ሁልጊዜ በሚታይ አገልግሎት ላይ ስለሆነ፥ የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ በአደባባይ የሚታይ ስለሆነ ለሰዎች ነቀፋ የተጋለጡ ናቸው። የሚወረወርባቸውን ነቀፋ ሁሉ "አሜን!" ብለው መቀበል አለባቸው ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ ተደጋግሞ የሚመጣ ከሆነ፥ በተለይ ከሽማግሌዎች የሚመጣውን አስተያየትና ገንቢ ነቀፋ ችላ ብለው ሊያልፉት አይገባም። በሕይወታቸው አንዳንድ ኃጢአቶች ወይም ድካሞች እንዳሉ ሲነገራቸው፥ የተነገራቸው ድካም እውነት መሆኑን ልባቸው ሲያውቀው፥ በመከራከር ፈንታ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ንስሀ መግባት ይገባቸዋል። ይህንን በማድረጋቸው ምዕመናኑም ሆነ ሽማግሌዎች ለእነርሱ አክብሮትና እምነት ይኖረዋል እንጂ፥ አሳንሰው አያዩዋቸውም።

## 6. ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት፥ የመጋቢዎችና የሽማግሌዎች አንድነት አስፈላጊ ነው

ከላይ እንደ ገለጽኩት በቤተ ክርስቲያናችን ዋና መጋቢና ሌሎች ሁለት ተባባሪ መጋቢዎች አሉን። ሦስቱም ሽማግሌዎች ቢሆኑም፤ ዋናው መጋቢ የቤተ ክርስቲያኒቱና የእኛም የሽማግሌዎች መንፈሳዊ መሪ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቷ በምታደርገው እንቅስቃሴ ላይ ተሰብስበን የተለያዩ ውሳኔዎችን እንሰጣለን። የምንነጋገርበትን አጀንዳ አዘጋጅቶ የሚያቀርበው ዋናው መጋቢ ነው። ውሳኔ ከመስጠታችን በፊት፥ ማወቅ የሚገባንን ነገር ከመጽሐፍም ሆነ፥ ሌሎች ከእኛ ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንደሚሠሩ፥ ምን ዓይነት እርምጃዎች እንደወሰዱ እንመለከታለን። ለምሳሌ፥ አንድ ተባባሪ መጋቢ ብንጠራና ምን ያህል ደሞዝ መከፈል እንዳለብን ለመወሰን ብንሰበሰብ፥ ውይይቱን የምንጀምረው በጨለማ ወይም ባዶ እጃችን ሆነን አይደለም። በእኛ ደረጃ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ምን ያህል እንደሚከፍሉ፥ እንዲሁም አሜሪካን አገር ብዙ ዓይነት ስታቲስቲክስ የሚገኝበት አገር በመሆኑ፥ ባለንበት ከተማ፣ አንድ አገልጋይ በኑሮው ሳይጣበብ መኖር የሚያስችል ገቢ ምን ያህል እንደሆነ፥ እንዲሁም የመጋቢዎች የደሞዝ እርከን (ስኬል) የሚያሳይ ተዘጋጅቶ የወጣ ስታትስቲክስ ስላለ፥ ሁሉንም አዘጋ

ጅቶ ያቀርብልናል። ያንን እያየን ስፊ ውይይት ካደረግን በኋላ እንወስናልን። ዋናው መጋቢ ያቀረበውን ሁሉ ሳናምንበት "ይሁን" ብለን የምንቀበል አይደለንም። ይሁን እንጂ ትክክል ከሆንና ካመንበት፥ ላለመቀበል ስንል ወይም ጉልበታችንን ለማሳየት ስንል ብቻ "አይሆንም" አንልም። መጋቢውና ሽማግሌዎች "እጅና ጓንት" ሆነን እንሠራለን እንጂ፥ አንዱ የሌላው አለቃና ተቆጣጣሪ በመሆን፥ በጥልና በክርክር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም አንሞክርም። ሥራው የእርሱ እንጂ፥ የእኛ ስላልሆነ የምንጣላበት ምክንያት የለም። "የሕያው ቃል ቤተ ክርስቲያን" የዕድገቷ ትልቁ ምክንያት አንደኛው እግዚአብሔርን የሚፈሩና እግዚአብሔርን የሚያከብሩ ሽማግሌዎችና መጋቢዎች ያሏት በመሆኗ ነው።

ከሦስቱ መጋቢዎች በቀር ስምንቶቻችን በተለያየ የግል አገልግሎትም ሆነ ሥራ ላይ የተሰለፍን በመሆናችን፥ ለሽማግሌዎች ስብሰባ ስንመጣ በሥጋችን ደክሞን ነው። ይሁን እንጂ ስብሰባችን አዕምሯችንን የሚያደክም አይደለም። በጌታ ፊት የምናሳልፈው የጸሎት ጊዜ፥ በግል ሕይወታችን ውስጥ ያጋጠመንን ስንወያይ፥ አልፎ አልፎ ታላላቅ ክርስቲያን መሪዎች የጻፉትን መጽሐፍ አንብበን ያገኘነውን አዲስ አሳብ ስንለዋወጥ፥ የተለያየ አሳብና አስተያየት ቢኖረንም መጨረሻ ላይ ወደ አንድ አሳብ ስንደርስ ማየት፥ ቀደም ባሉት ውሳኔዎቻችን ጌታ የሠራውን ስንገመግም፥ በወንድማማችነት ያለን መቀራረብ እየጠነከረ ሲመጣ እያየን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። እግዚአብሔርን የሚወዱና የሚፈሩ ሰዎች ለአንድ ዓላማና ግብ በሕብረት ሲሠሩ፥ በመካከላቸው የእግዚአብሔርን መገኘት አጉልቶ ያሳያል። ወደ ሽማግሌዎች ስብሰባ ለንሄድ፥ "ዛሬ ምን ያጨቃጭቀን ይሆን?" ብለን እየፈራን አንሄድም። በሃያ አራት ዓመት ውስጥ አንድም ቀን የሚያፋቅር እንጂ የሚያጣላ ስብስባ አላየሁም። በመካከላችን በግልጽ የእግዚአብሔር እጅ እንዳለበት እናያለን።

በውሳኔ አለጣጣችን እርስ በርሳችን መተማመንን ተምረናል። የስምንት ሚሊዮን ዶላር የቤተ ክርስቲያን ሥራ ገና ከጽንስ አሳብ ጀምሮ ተሠርቶ እስከሚያልቅበት ጊዜ ድረስ ያስተላለፍናቸው ውሳኔዎች፥ የቤተ ክርስቲያኒቱን አገልጋዮች፣ መጋቢዎችንና የፕሮግራም ድሬክተሮችን ስንመለምል፥ ልዩ ልዩ አገልግሎት እንዲመሠረቱ ስናደርግ፥ ጊዜና ጉልበት የሚጠይቁ ልዩ ልዩ እያሌ ውሳኔዎችን ስናስተላልፍ በመካከላችን ያለው ፍቅር፥ አንድነትና መተማመን እየጠነከረ መጣ እንጂ አልላላም። በጠቅላላው በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ለሚያጋጥሙን ፈታኝ በሆኑ ጊዜያቶችና ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍ በእግዚአብሔር ላይ ያለን ትምክህትና እምነት፥ እንዲሁም አንዳችን በሌሎቻችን ላይ የሚያስን መተማመን እያደገ መጣ። የሚያስደንቀው ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያጋጥማትን ችግር መፍታት ብቻ ሳይሆን፥ የግል ችግራችንን፥ በየመሥሪያ ቤታችን ያጋጠመንን ፈታኝ ነገር፣ በየቤታችን የምናልፍበትን ሁኔታ ይዘን በመምጣት የልባችንን ሳንፈራ ማፍሰስ በመቻላችን፥ እጅ ለእጅ ተያይዘን አንዱ ለሌላው በጸሎት መቃተቱ፥



በሽማግሌዎችና በመጋቢዎች መካከል ሙሉ የሆነ የልብ መቀራረብና መተማመንን ይለጠን ነበር። ለምሳሌ፥

- መጋቢው አንዳንድ አስቸጋሪ የሆኑ ምዕመናን ሲያጋጥሙት፥ ምን ማድረግ እንዳለበት ሀሳብ ሲጠይቅ፥ እግዚአብሔር ጥበቡን እንዲሰጠው እንጸልይለታለን፤ ትክክል የመሰለንን ምክር እንሰጠዋለን።
- ከሽማግሌዎች መካከል አንዱ አስቸጋሪ የሆነ የሥራ ባልደረባውን እንዴት በትዕግሥት ማለፍ እንደሚችል ምክርና ጸሎት ሲጠይቅ፥ የጸሎትና የምክር ዕርዳታ እንሰጠዋለን።
- ከሽማግሌዎች መካከል ጡረታ የመውጫው ጊዜ ሲደርስ፥በሚሰማው ከባድ ስሜት ምክንያት የአዕምሮ ጭንቀት ውስጥ እንዳይገባ ጸሎትና ምክር ያገኛል።
- ከሽማግሌዎች መካከል ልጁ ከፈቃዱ ውጪ፥ እርሱ የማይደግፈውን ውሳኔ ያደርግ ይሆናል ብሎ በመፍራት በጸሎት እንዲታገዝ ሲጠይቅ፣ አስፈላጊውን እገዛ እናደርግለታለን። ይሄ ሁሉ በመካከላችን ያለውን መተማመንና ቅርበት ያሳያል።

እግዚአብሔርን የሚወዱ ሰዎች እርስ በርሳቸው ሲቀራረቡና ሲተማመኑ ከላይ እንዳየነው የግል ችግራቸውንና ትግላቸውን ለማካፈል አይፈሩም። ሕብረታችንና አንድነታችንን የሚለካው ሁሉም ሰላም በሚሆንበት ጊዜ ብቻ አይደለም። አስቸጋሪ የሆኑ ጊዜያቶችም አጋጥመውናል። "ይህንን ፈታኝ የሆነ ነገር ዋናው መጋቢ ይፍታው፥ እኛ እዚህ ውስጥ እጃችንን አንከትም" ያልንበት ጊዜ የለም። ለቅድስና የማይራመደውን ምዕመን "ልክ አይደለህም" ብሎ ፊት ለፊት መገለጽ ከባድ ቢሆንም፥ ሽማግሌዎች ሁሉ ባሉበት ለብስባ ላይ መቅረብ ያለበትን በማቅረብ፥ ሁለት ወይም ሦስት ሽማግሌዎች በቂ ከሆኑ በእነርሱ ፊት በማቅረብ፥ ምዕመኑን እንደ እግዚአብሔር ቃል ግሳጼን የሰጠንበት ጊዜ አለ። ለታመሙት ዘይት እየቀባን ጸልየናል። የተለያየ ሀዘን ከደረሰባቸው ጋር አብረን አልቅሰናል። ይሄ ሁሉ በመጋቢዎችና በሽማግሌዎች መካከል ያለውን እውነተኛ መቀራረብና የልብ አንድነት ያሳያል።

## 7. ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የመሪዎች የአመራር ችሎታ አስፈላጊ ነው

በኢትዮጵያውያን አማኞች መካከል ጥሩ የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን የሚችሉ አንዳንድ ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ ለማገልገል ፈቃደኞች አይሆኑም። "መሪ ለመሆን መፈለግ ወይም መመኘት ትክክል አይደለም" ብለው ይሆን? ወይም "መሪ ልሁን" ብሎ ራስን ከማቅረብ፣ "መሪ መሆን የሚያስችል ብቃት ወይም ችሎታ

ካለው፣ ሌሎች "መሪ ሁነን" ብለው ሊጠይቁን ይገባል" ብለው በማሰብ ይሆን? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት አማኞች ሁሉም ያላቸው አቋም ይህን ዓይነት አይደለም። በአንድ በኩል መሪ ለመሆን ፈቃደኞች ባለመሆን ገለል ብለው የሚቀመጡ ሲኖሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ችሎታውና ጥሪውም ባይኖራቸው የመሪነትን ቦታ ከመጠን በላይ የሚፈልጉ ናቸው። አንዳንዶቹ የሚፈልጉትን የመሪነት ሥፍራ በትክክለኛው መንገድ ባያገኙ፣ መንፈሳዊነት በሌለው መንገድ፣ የራሳቸውን ብልሃት ወይም ዘዴ በመጠቀም ሥፍራውን ለማግኘት ከፍተኛ ተጋድሎ የሚያደርጉ አሉ። ችሎታውና ጥሪው ያላቸው ወደ መሪነት ደረጃ ለመምጣት በማመንታታቸው ምክንያት፣ ቤተ ክርስቲያን ትክክለኛ መሪ ባልሆኑ ሰዎች እጅ ስትወድቅ ማየት አጅግ በጣም ያሳዝናል። አንዳንዶች እንደምንም ብለው አንድ ጊዜ የመሪነቱን ሥፍራ ተጋድለውም ቢሆን ካገኙ በኋላ፣ በሚሰጡት አገልግሎት አጥጋቢ ውጤት ባይኖራቸውም፣ አንዴ የያዙትን የመሪነት ሥፍራ ላለመልቀቅ ከፍተኛ ተጋድሎ የሚያደርጉ አሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚያድጉበትና የሚታነጹበት ሥፍራ በመሆን ፈንታ፣ "ማኀበራዊ ስብሰባ" የሚካሄድባት ብቻ ሆና ትቀራለች። አማኞችም ከመንፈሳዊ መሪዎቻቸው ጠቃሚ የሆነ መንፈሳዊ ምግብ ባያገኙም፥ ቀባሪ እንዳያጡ ወይም ብቸኛ እንዳይሆኑ ብቻ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ።

"መንፈሳዊ መሪ ለመሆን መፈለግ (መመኘት) በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ዘንድ ትክክል ነው ወይ? የክብር ሥፍራ በመመኘታቸው ምክንያት አንዳንድ ታላላቅ ሰዎች በሕይወታቸው ከፍተኛ ውድቀት ደርሶባቸው የለም እንዴ? እውነተኛ አማኝ መንፈሳዊ መሪ ለመሆን ቢመኝ ራሱን ማተለቁ አይሆንም ወይ?" ብለው የሚጠይቁ ሰዎች አይጠፉም። እርግጥ ነው ክርስቲያን ትክክለኛ ያልሆነ ምኞት ወደ ሕይወቱ እንዳይገባ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። ኤርምያስ ባሮክን፥ *"ታዲያ፥ ለራስህ ታላቅ ጥፋት ታመጣ ለሆና አትፈልገው..."* (ኤር. 45፥5 ሲለው፥ ትክክለኛ ያልሆነ ምኞትን ወደ ሕይወቱ እንዳያስገባ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ጳውሎስ ***"ማንም የቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን ቢፈልግ፣ መልካም ሥራን ይመኛል"*** (1 ጢሞ. 3፥1) በማለት ለጢሞቴዎስ የጻፈለትን መልዕክት እናነባለን። እነዚህ ሁለት ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ አይደሉም። መልካምና ክቡር የሆነ ምኞት እንዳለ ሁሉ፣ እግዚአብሔርን የማያከብር ምኞትም እንዳለ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ጥቅሶች ያሳያሉ። ጳውሎስ ይህን መልዕክት ለጢሞቴዎስ በጻፈበት ዘመን፣ ኤጲስ ቆጶስ መሆን ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍል ነበር። ይኸውም፣ ኤጲስ ቆጶስ የሆነ ሰው በሕይወቱ ስደት፣ መከራ፣ መገፋት የከፋ እንደሆነም ሞት ይደርስበት ነበር። የመጀመሪያውን የሞት ጽዋ የሚቀምሰው ኤጲስ ቆጶሱ ነው። ይህንን እያወቀ ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን የሚመኝ ሰው ቢኖር፣ ሹመቱን የተመኘው ክብርና ዝናን አገኝበታለሁ ብሎ ሳይሆን፣ *"ለመሞት ዝግጁ ነኝ፤ ራሴን መስዋዕት አድርጌ ለመስጠት ተዘጋጅቻለሁ"* ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው። እግዚአብሔርን ለማክበር



እስከ ሆነ ድረስ ትልቅ ነገር መመኘት ኃጢአትነት የለውም። ጳውሎስ ***"ማንም የቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን ቢፈልግ፣ መልካም ሥራን ይመኛል"*** ሲል፣ ቤተ ክርስቲያንን ለራሳቸው ጥቅም፣ እንዲሁም ክብርና ዝናን ለማግኘት የሚፈልጉትን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲሆኑ ማደፋፈሩ አይደለም። እውነተኛነት የሌላቸው መሪዎች መከራ ለመቀበል፣ ራሳቸውን መስዋዕት አድርገው ለመስጠት አቅምም ሆነ ፍላጎት የላቸውም። እግዚአብሔርን የማያከብር፣ መልካምና ጤናማ ያልሆነ ምኞት መመኘት ራስን ለታላቅ ጥፋት መጋበዝ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ቤተ ክርስቲያንን የመምራት ችሎታና የአገልግሎት ልብ ያላቸውን ሁሉ፣ ዳር ቆመው ከመመልከት ይልቅ ወደ አገልግሎት እንዲመጡ በጥብቅ ያሳስባል። ትክክለኛ የሆነ ዓላማና ምክንያት ካለን፣ መንፈሳዊ መሪ ለመሆን ብንመኝ፣ ኃጢአት መሥራታችን እንዳልሆነ ማወቅ አለብን። ክብርና ስም፣ እንዲሁም ለግል ጥቅም ሲሉ መሪ ለመሆን የሚፈልጉ አማኞች መኖራቸው፣ እውነተኛ የሆኑ አገልጋዮች የቤተ ክርስቲያን መሪ እንዳይሆኑ መሸሽ ወይም ራሳቸውን መደበቅ አለባቸው ማለት አይደለም። ዛሬ የዘመኗ ቤተ ክርስቲያን በጥበብና በማስተዋል የተሞሉ፣ ጥሪና ስጦታ እንዲሁም ብቃት ያላቸው እውነተኛ መሪዎች ያጣችበት ትልቁና ዋናው ምክንያት፣ ብዙዎች ራሳቸውን ገለል ያደረጉ በመሆናቸው፣ ወይም ያለአግባብ ተገፍተው ከቤተ ክርስቲያን የራቁ አማኞች በብዛት በመኖራቸው ነው። ኤርሚያስ ባሮክን *"...ለራስህ ታላቅ ነገር ትሻለህን? ...ከሆነ አትፈልገው"* ሲለው፣ ኤርሚያስ ትልቅ ነገር መፈለግን እንደ ኃጢአት በመቁጠር መፍረዱ ሳይሆን፣ ለግል ጥቅም ብሎ ታላቅ ነገርን መመኘት ትክክል አለመሆኑን ለማሳየት ነው። ትልቅ ለመሆን መፈለግ (መመኘት) ኃጢአት አይደለም። ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር የሰጠንን የተፈጥሮ ችሎታ፣ ለእርሱ ክብር እንዲሆን ማዳበር፣ ወይም ትልቅ ለመሆን መፈለግ (መመኘት) ኃጢአት አይደለም። ነገር ግን ፍላጎታችን ወይም ምኞታችን ራሳችንን ለማስቀደም ከሆነ፣ ሥራችን ምንም ያህል መንፈሳዊነት ያለው ቢመስል፣ ያኔ ትልቅ የመሆን ምኞታችን ኃጢአት ይሆናል። ኦስዋልድ ሳንደርስ፥

> *"በእግዚአብሔር ክብር ላይ ያተኮረ፣ ለቤተ ክርስቲያን ደህንነት ከሆነ፥ ምኞት (ፍላጎት) ትልቅ ኃይል ነው[9] አሉ።*

*"አምቢሽን" (ambition)* የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ከላቲን የመጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም "ለሹመት ዘመቻ ማድረግ" ማለት ነው። "አምቢሽን" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል፣ ሰዎች ባሉበት ሕብረተሰብ ውስጥ ጎልቶ ለመታየት፣ ተቀባይነት ለማግኘት፣ ገናናነትን፣ እንዲሁም በሌሎች ላይ የበላይ ለመሆን ያላቸውን ጥማትና ጉጉትን (ምኞትን) ያሳያል። በምኞት የተሞሉ ሰዎች በገንዘብም ሆነ በሥልጣን አማካኝነት በሚያገኙት

[9] Sanders, Oswald J, Spiritual Leadership, Moody Press, IL, Chicago, c1967.

ኃይል በጣም የሰከሩ ናቸው። ይሁን እንጂ፣ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች፣ ከላይ ለጠቀስናቸው ነገሮች ጥማት ያላቸው አይደሉም። ትልቅነት በምን እንደሚገኝ ኢየሱስ በትምህርቱ ጠቅሶታል። *"...ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤ ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፤ የሁሉም ባሪያ ይሁን"* ይላል (የማር. 10፥43-44)። እውነተኛ ታላቅነት፣ እውነተኛ መሪነት የሚገኘው ሌሎችን ለማገልገል ራስን በመስጠት እንጂ ተገልጋዮች እንዲያገለግሉን እነርሱን በመጫን ወይም በመገፋፋት አይደለም። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ሆኖ ማገልገል ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላል። ብዙ ጊዜ በችግርና በመከራ ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል። እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች ትኩረታቸው በእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰዎች በሚሰጡት መልካም አገልግሎት ላይ እንጂ በሚያገኙት ትርፍ፣ ሹመት ወይም ጥቅም ላይ የተመሠረተ አይደለም። እውነተኛ መሪዎች በምድር ላይ ከሚያገኙት ጥቅም ይልቅ፣ የሚከፍሉት መስዋዕት ይበልጣል።

እግዚአብሔር በየዘመናቱ እንደ ልቡ የሚሆኑለትን፣ እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎችን ፈልጎ ማጣቱን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። *"ምድሪቱን እንዳላጠፋት ቅጥሩን የሚጠግን፣ በፈረሰውም በኩል በፊቴ የሚቆምላት ሰው ከመካከላቸው ፈለግሁ፤ ነገር ግን አንድም አላገኘሁም"* ይላል (ሕዝ. 22፥30)። የሕዝቡ መሪ እንዲሆን ያስቀመጠው ንጉሥ ሳኦል፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ የራሱን ፈቃድና ፍላጎት ለመፈጸም በመፈለጉ፣ እግዚአብሔር የወሰደውን እርምጃ ሳሙኤል ሲገልጽለት፣ *"...እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሚሆንለትን ሰው አግኝቶአል፤ አንተ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለመጠበቅህም፣ እርሱን የሕዝቡ መሪ አድርጎ መርጦታል"* አለው( ሳሙ. 13፥14)። እንደ ልቡ የሚሆንለትን፣ ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር መምራት፣ ደቀ መዝሙር ማድረግ የሚችሉትን፣ የእግዚአብሔርን ክብር ሳይሻሙ የተሰጣቸውን የመምራት ኃላፊነት እንደሚገባው የሚጠቀሙበትን ሰዎች፥ እግዚአብሔር ጥንት ብቻ ሳይሆን ዛሬም ቢሆን ይፈልጋል። የራሳቸው ድካምና መተላለፍ ያላቸው ቢሆኑም እንኳን፣ እግዚአብሔር ከነድካማቸው ይጠቀምባቸዋል። ሙሴ፣ ጌዴዮን፣ ዳዊት፣ ሠሎሞንና ሌሎችም የሕዝቡ መሪዎች ሆነው ያገለገሉ እንጂ የራሳቸው ድካምና ወድቀት እንደነበረባቸው የታወቀ ነው።

ጥንት ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ያባትነት ልብ ያላቸው፣ ሰፊው ሕዝብ ካለው የበለጠ ኃይልና እምነት ያላቸው እውነተኛ የሆኑ መሪዎች ያስፈልጋሉ። ብዙ መንፈሳዊ መሪዎች በሚያስፈልጉበት በዚህ ዘመን ለመሪነት ብቃት ያላቸው መንፈሳዊ መሪዎች የታጡበት ምክንያት ለምን ይሆን? ይሁን እንጂ፣ ቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚቆሙ፣ ራሳቸውን "የቤተ ክርስቲያን መሪዎች" ብለው የሾሙ ሰዎችን ግን ያጣችበት ጊዜ የለም። "ሥልጣኑ ለእኔ ይገባኛል" በሚሉ ሰዎች መካከል፣ በመድረኩ ዙሪያ የሚካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት፣ ከምንጊዜውም የበለጠ በአሁኑ ጊዜ ተፋፍሞ ይታያል። ቤተ ክርስቲያን የመሪዎች እጥረት ሳይሆን፣ የመሪዎች ብዛት ያስጨነቃት ትመስላለች። "ቤተ ክርስቲያን የመሪዎች እጥረት አለባት" ስንል፣ በወንጌል ለመክበር የሚፈልጉ፣



የራሳቸውን ፈቃድና ፍላጎት ለማሟላት ከፍተኛ ትግል የሚታገሉትን፣ የመሪነት ጥሪና ችሎታ ሳይኖራቸው "እግዚአብሔር ጠርቶኛል" የሚሉትን ዓይነት ሰዎች ማለታችን አይደለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድና ፍላጎት የሚፈጽሙትን፣ ማንም ሳይገፉቸው በፈቃደኝነት መሪ ለመሆን የሚፈልጉትን ሰዎች ቤተ ክርስቲያን እጇን ዘርግታ እንደምትቀበላቸው ግልጽ ነው። አስቸጋሪ የሆነው ግን፣ እውነተኞችን እውነተኛ ካልሆኑት መካከል መለየት ነው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን "የመሪዎች ያለህ" ብላ ብትጮኽም፣ በሙሉ ኃይልና ሥልጣን የሚመሩ፣ መንፈሳዊ የሆኑ፣ ከፍተኛ መስዋዕት ለመክፈል ፈቃደኞች የሆኑ መሪዎች አጥታለች። ሕዝቡ መነሻውንና መድረሻውን የሚያሳውቀውን መንፈሳዊነት ያላቸውን መሪዎች ይፈልጋል። በመሪነት ሥፍራ የተቀመጡት ሰዎች ራሳቸው ከእግዚአብሔር ጋር የተቀራረበ ግንኙነት ከሌላቸው፣ ምንም ያህል ችሎታ ያላቸው ቢሆኑም ሕዝቡን በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊያሳድጉት እንደማይችሉ ቀደም ሲል ገልጸናል።

ቤተ ክርስቲያን ብርቱ በሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች ከተመራች፣ በሁሉም አቅጣጫ እውነተኛ የሆነ ዕድገት ታሳያለች። ትክክለኛ የሆኑ መሪዎች ከሌሏት ግን፣ በሁከትና ሰላም በማጣት የተሞላች፣ የተጠራችበትን የወንጌል ተልእኮ እንደሚገባው መፈጸም የማትችል ትሆናለች። ዛሬ በኃይልና በሥልጣን እውነተኛውን ወንጌል የሚሰብኩ፣ በሚኖሩት ኑሮ መልካም አርአያ መሆን የሚችሉ መሪዎች ቁጥራቸው በጣም አነስተኛ የሆነበት ዘመን ነው። መንፈሳዊ የሆኑ እውነተኛ መሪዎች ከሌሉ፣ የወንጌልን ብርሃን ለሚቀጥለው ትውልድ እንደሚገባ ማስተላለፍ (ማቀበል) አይቻልም። ችግሩ አቀባይ አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን ተቀባይ ትውልድ መጥፋቱም ጭምር ነው። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች "በቤተ እምነት" ምልመላ፣ በምርጫ የሚገኙ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ራሱ ሲያስነሳቸው ብቻ ነው። የመሪን እጥረት ለማጥፋት፣ መሪ መሆን ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡትን ትምህርት ቤት አስገብቶ ስለ አመራር ትምህርት በመስጠት፣ ፍላጎትን በመቀስቀስ ብቻ መንፈሳዊ መሪዎችን ማምረት አይቻልም። መንፈሳዊ መሪ፣ ከእግዚአብሔር ጥሪ የደረሰው፣ እንዲሁም መሪ ለመሆን የሚያስችል ብቃትም ሆነ ዝግጅት ያለው መሆን አለበት። ሁሉን ማየት የሚችለው እግዚአብሔር፣ የመምራት ችሎታ ያለውን ሰው ሲያገኝ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከሞላው በኋላ ለተለየ አገልግሎት ይጠራዋል (ይለየዋል) (የሐዋ. 9፥17፥22፥21)። ሳሙኤል ብሬንግል፣ "ሳልቬሽን አርሚ" *(Salvation Army)* ውስጥ ብዙ ዓመት ያገለገሉ፥ ራሳቸው የመሪነት ስጦታ የነበራቸው ሰው፥ መንፈሳዊ መሪ መሆን የሚቻልበትን መንገድ ሲዘረዝሩ እንዲህ አሉ፣

> *"በብዙ ጸሎትና ዕንባ እንጂ በሹመት አይገኝም። ኃጢአትን በመናዘዝ፣ በእግዚአብሔር ፊት በትህትና የራስን ልብ በመመርመር፣ ራስን ሙሉ በሙሉ በማስረከብ ጣኦት የሆነውን ማንኛውንም ነገር በድፍረት በማስወገድ፣ ሳያወላውሉ መስቀሉን ሙሉ በሙሉ በመሸከም (በመያዝ)፣ ወደ ተሰቀለው ክርስቶስ በመመል*

*ከት ብቻ የሚገኝ ነው። ትልቅ የሆነውን ነገር ስራስ በመመኘት የሚገኝ አይደ ስም፤እንደ ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ስንል ያስንን መልካም ነገር ሁሉ እንደ ፋንድያ በመቁጠር የሚገኝ ነው። ይሄን ዓይነት ዋጋ መክፈል ከባድ ስለ ሆነ፣ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ካልሆነ፣ያስው ኃይልም ሆነ ሥልጣን በሰማያዊው ጌታ የታወቀና ተቀባይነት ያገኘ ካልሆነ፣ ማንኛውም ሰው ሊያደርገው (ሊደርስበት) የሚችለው አይደለም።*[40]

እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ካልሆነ፥ ከላይ የዘረዘርናቸውን ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍ ሉትን ሁኔታዎች ተቀብሎ መሪ ለመሆን የሚፈልግ ሰው የለም። እግዚአብሔር የሚፈል ገውን ዓይነት ሕይወት ያላቸው ሰዎች ብዙ ባይሆኑም፣ እግዚአብሔር ያወጣውን (የወሰ ነውን) የመሪነት ደረጃ እንደ ሰው ዝቅ ያደርጋል ማለት አይደለም። በመሪነት ስፍራ መቀመጥ ምንም ያህል አስፈሪ ቢሆንም፣ እውነተኛ መሪዎች የሆኑ ከእግዚአብሔር ይህን ዓይነቱ ጥሪ ሲደርሳቸው ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ጥሪውን ይቀበላሉ እንጂ አይታበዩም።

## 8. ለቤተ ክርስትያን ዕድገት የመሪዎች "ሐቀኛነት" (ጽኑ አቋም) (Integrity) አስፈላጊ ነው

ፍሬያማ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመሆን አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንደኛው *"ሐቀኛነት" (ጽኑ አቋም) (integrity)* ያለው ሰው መሆን ነው። *"ሐቀኛነት"* ስንል ምን ማስታችን ነው? "ዌብስተር" የእንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት፣ (integrity) "ሐቀኝነትን" የሚለውን ቃል፣ *የሥነ ምግባር ጥራት፣... ቅንነት... ታማኝነት... እውነተኛነት* በማለት ይገልጸዋል። "ሐቀኛ" (ሐቀኛ አቋም) የሆነ ሰው እንዴት ዓይነት ነው?

- "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው፣ የሚናገረው ነገር ከሚያደርገው ጋር አብሮ የሚሄድ ነው።
- "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው፣ የተናገረውን ቃል የሚጠብቅ ነው።
- "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው፣ የሆነውን ሆኖ ይገኛል እንጂ ያልሆነውን መስሎ ለመታየት አይሞክርም።
- "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው፣ ለግል ጥቅም ሲል እውነትን አይሸቃቅጥም (2 ቆሮ. 2፥17)
- "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው፣ ነውር አልባ ነው (ዘዳ. 18፥13)።

Sanders. Quated in SamuelBrengle, The Soul-Winner's Secret (London: Salvation rmy, 1918), 22.



- "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው፣ የሰጠውን ተስፋ ይጠብቃል፤ ኃላፊነቱን በታማኝነት ይወጣል፤ በገንዘብ አያያዙ ጠንቃቃ ነው፤ በንግግሩ የውሸት ቃል አይቀላቅልም።

በአሁኑ ዘመን *"ሐቀኛ"*የሆኑ፣ ወይም "ሐቀኛ አቋም" ያላቸው ናቸው የሚባሉ ሰዎች ቁጥር እየቀነሰ መሄዱ በብዙዎች ዘንድ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። ግብረ ገብ የጎደለው ተግባር ሲፈጽሙ የሚታዩት፣ ወይም ከእነርሱ የማይጠበቀውን ሕገ ወጥ ተግባር በመፈጸ ማቸው ፍርድ ቤት ተከሰው የሚቀርቡት የዓለም ድርጅት መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያንና መንፈሳዊ አገልግሎትንም የሚመሩ መሪዎች ጭምር በመሆናቸው፣ በአሁኑ ጊዜ ምዕመናን በመሪዎቻቸው ላይ እምነት እያጡ መጥተዋል። "ሐቀኛ አቋም" ያላቸው ሰዎች ተለይተው የሚታወቁት፣ ባመኑበት ነገር ላይ ጽኑ የሆነ አቋም ያላቸው መሆና ቸው ብቻ ሳይሆን በሕይወታቸው የሚደብቁትና የሚፈሩት ነገር የሌላቸው በመሆናቸው ነው። ውስጣቸውና ውጪያቸው ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ፣ በባህሪያቸው ተለዋዋጭ ነት አይታይባቸውም። ሕይወታቸው እንደ ተከፈተ መጽሐፍ ስለሆነ፣ እንባቢያቸውን አያደናግሩም። በሕይወታቸው ከፍተኛውን ሥፍራ የሚሰጡት ነገር፣ እውነተኛውን እነርሱነታቸውን (ሀልውናቸውን) ያንጸባርቃል። በሚወዱትና በሚጠሉት ነገር ማንነታ ቸው ተገልጦ ይታያል። ሕይወታቸው ወዴት እንደሚያዘነብል አቅጣጫውን የሚወስነው በሕይወታቸው ከፍተኛውን ሥፍራ የሚሰጡት ነገር ነው። የሚይዙትና የሚጥሉት ነገር በሕይወታቸው ቅድሚያ የሚሰጡት ነገር፣ እውነተኛውን ባህሪያቸውን (ሀልውናቸውን) ያሳያል።

ሁላችንም እርስ በርሳቸው የሚጋጩ፣ ልናስታርቃቸው አስቸጋሪ የሚሆኑብን የተ ለያዩ ፍላጎቶች አሉን። ምንም ያህል መንፈሳውያን ብንሆን፣ ከእነዚህ የፍላጎት ግጭቶች ነጻ መሆን አንችልም። ከፍላጎቶቻችን መካከል ለየትኞቹ መልስ መስጠት እንዳለብን ውሳኔ ለመስጠት የሚረዳን፣ *"አቋመ-ጽኑነት" ወይም "ሀቀኝነት" (Integrity)* ነው። እኛ ማድረግ በምንፈልገውና እንዲሁም መደረግ ባለበት ነገር (ሁኔታ) መካከል ወይም በሁለት አማራጭ ሁኔታዎች ውስጥ ሁልጊዜ ግጭት አለ። መደረግ ያለበትን ነገር ትተን፣ እኛ የምንፈልገውን ነገር ማድረግ የምንመርጥበት ጊዜ አለ። በእነዚህ ሁለት ምርጫዎች ውስጥ ትክክለኛውን ምርጫ መምረጥ የሚያስችለን "ጽኑ አቋም" (ሀቀኝነት) ያለን ስንሆን ነው። *"ሐቀኝነት"* በሁለቱ መካከል ያለውን ውጥረት ያረግባል። "የሐቀኝ ነት አቋም" ባሕሪ፣ ማንነታችንን የሚያሳይ ከመሆኑ በላይ፣ ምን ዓይነት ውሳኔ ወይም ምርጫ ማድረግ እንዳለብንም ይረዳናል። "ሐቀኛ አቋም" በሁለት ዓይነት ፍላጎቶች መካከል የሚዳኝ ዳኛ ብቻ ሳይሆን በመንገዳችን ላይ በሚያጋጥመን ማንኛውም ዓይነት ነገር ቁርጥ ያለ አቋም ያለን እንድንሆን የሚረዳን ነው። የምንናገረው ነገር ከምናደርገው ነገር ጋር አብሮ የማይሄድ ከሆነ፥ የሚከተሉንን ሰዎች እናደናግራለን። "ሐቀኛ አቋም" ያለን ከሆንን፥ ጠባያችን የማይለዋወጥ ይሆናል። ሁልጊዜ የሆንነውን ሆነን እንገኛለን። ሰው በሚያየን ጊዜም ሆነ ሰው በማያየን ጊዜ እውነተኛው እኛነታችን የሚለዋወጥ አይሆንም። ይኸውም አንዴ አንድ ነገር፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ ነገር ሆነን አንገኝም። ድሃ በነበርንበት ወቅት

የነበረን አቋም፣ ባለጸጋ (ሀብታም) በምንሆንበት ጊዜም አይለወጥም። ሁኔታዎችን እያየን አንለዋወጥም ማለት ነው። የትልቅነት ምልክት ምን እንደሆነ ሶቅራጠስ ሲጽፍ፥ *"የሆንነውን ሆነን መገኘት ነው"* ይላል። ብዙ ጊዜ ከመሆናችን በፊት "አድራጊዎች" እንሆናለን። *መንፈሳዊ መሪ እምነት የሚጣልበት እንዲሆን እውነተኛ (ሀቀኛ) መሆን አለበት።* ጥሩ *ለመዘመር፣ ሙዚቃው ከሰውየው ዝማሬ ጋር አብሮ መሄድ አለበት።* ካልሆነ ግን ጣዕም ያለው ዝማሬ መሆን አይችልም። ልክ እንደዚሁ የምናደርገው ነገር፣ "ነን" ከምንለው ጋር፣ እንዲሁም የምንለው ነገር ከምናደርገው ጋር አብሮ መሄድ አለበት።

*ለምሳሌ መንፈሳዊ መሪ ምዕመናኖቹን ሲያስተምር፥*

| | | |
|---|---|---|
| *"ቤተ ክርስቲያን በሰዓቱ ተገኙ" ቢል፥* | *ራሱ ግን በሰዓቱ ባይገኝ፥* | *ምዕመናኑ ሁሉም በሰዓቱ አይገኙም።* |
| *"አሥራታችሁን በታማኝነት ስጡ" ቢል፥* | *መሪው ግን ራሱ ባይሰጥ፥* | *በከፊል እንጂ ሁሉም አይሰጥም* |
| *"ሁልጊዜ እውነቱን ተናገሩ" ቢል፥* | *መሪው ራሱ ቢዋሽ፥* | *ተከታዮቹ እውነትን አይናገሩም።* |

*መንፈሳዊ መሪ የሚናገረው ነገር ከሚያደርገው ነገር ጋር አብሮ የማይሄድ ከሆነ፣* ምዕመኑ ሁሉም አንድ ዓይነት አቋም ሲኖራቸው አይችልም። "ሐቀኛ አቋም" (ሀቀኝነት)፣ የሆንነውን እንጂ የምናደርገውን ነገር ብቻ የሚያሳይ አይደለም። *ሰዎች በሕይወታቸው ከሚማሩት ትምህርት ውስጥ 89 ከመቶ (89%) በዓይን ያዩትን፣ 10 ከመቶ (10%) በጆሯቸው የሰሙትን ሲሆን፣ 1 ከመቶ (1%) ሌሎች ስሜቶቻቸውን በመደገፍ የሚማሩት እንደሆነ ምሁራን ይገልጻሉ።* ሰዎች *"የሚሰሙትን ይረዱታል፤ የሚያዩትን ግን ያምኑታል"* ይባላል። ብዙ ጊዜ አንዳንድ *መሪዎች* ተከታዮቻቸውን ጥልቀትም ሆነ ዕድሜ በሌለው ነገር ለመቀስቀስ ቢሞክሩም፣ የሚፈልጉትን ዓይነት ውጤት አያገኙም። ሰዎች ከመንፈሳዊ መሪዎቻቸው የሚጠብቁት "መመሪያ ቃል" ሳይሆን፣ ምሳሌ (ሞዴል) እንዲሆኗቸው ነው። መንፈሳዊ መሪ በአቋሙ አስተማማኝ ሲሆን፣ ተከታዮቹ በእርሱ ላይ የበለጠ እምነት ይኖራቸዋል። በእርሱ ላይ እምነት ካላቸው ደግሞ ራሳቸውን ለመስጠት ወደ ኋላ አይሉም። መሪው እምነት የሚጣልበት ካልሆነ ግን፣ ተከታዮቹ በእርሱ እምነት ስለማይኖራቸው ወደ እርሱ በመቅረብ ፈንታ የበለጠ ይሸሹታል። ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ወሳኝ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል አንደኛውና ትልቁ፣ የመንፈሳዊ መሪው "ሐቀኛ አቋም" (ሀቀኝነት) ነው።

## 8.1. "ሐቀኛ አቋም" መተማመንን ያሳድራል

ድዋይት አይዘንሃወር፤

"አንድ ሰው መሪ ለመሆን የግድ ተከታዮች እንዲኖሩት ያስፈልጋል። ተከታዮች እንዲኖሩት ደግሞ እምነት የሚጣልበት መሆን አለበት። ስለዚህ ከመሪ የሚጠበቀው ትልቅ ነገር "የሐቀኛ አቋም" ባሕሪ ነው። መሪው "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው ካልሆነ፣ በኳስ ሜዳም ሆነ ወይም በጦር ሠራዊት ውስጥ፣ ወይም በቢሮ ውስጥ እውነተኛ የሆነ መሳካት፣ እጥጋቢ ውጤት አይኖረውም። አብሮት የሚሠራው ሰው መሪው እውነተኛ አለመሆኑን ወይም አስመሳይ ሆኖ ካገኘው፣ ሐቀኛ አቋም የሌለው መሆኑን ካወቀ፣ እምነት አይኖረውም። ያ መሪ በአመራሩ የጠበቀውን ዓይነት ውጤተ አያገኝም። ሁልጊዜ የሚያስተምረው (የሚናገረው) ነገር ከሚያደርገው ነገር ጋር አብሮ መሄድ አለበት። ስለዚህ መሪ በሕይወቱ ከፍተኛ ሥፍራ ሊሰጠው የሚገባ ነገር ቢኖር፣ "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው መሆን ነው" አሉ።[11]



"የአመራር ሙያ" ምሁራን፤ "ሥልጣን" ማለት አለቆች (መሪዎች) በሥራቸው ላሉት ሠራተኞች አለቃ እንዲሆኑ የሚያስችላቸው ኃይል ሳይሆን፥ አለቆች ባላ ቸው "ሌላውን የመሳብ ኃይል" (influence)፥ ከእነርሱ ሥር ያሉት ሠራተኞች እንዲከተሏቸው የሚያደርግ ኃይል ነው። የበታች ሠራተኞች፣ አለቃቸውን እንደ አለቃ መቀበል የሚችሉት፣ በሚሰጧቸው ትእዛዝ ሳይሆን በሚያሳዩዋቸው ገጸ ባሕሪ ረክተው የተቀበሏቸው ከሆነ ብቻ ነው" ይላሉ።

ከላይ እንደተመለከትነው መንፈሳዊ መሪ ምዕመኑ መሪነቱን አምነው እንዲቀበሉት (እንዲከተሉት)፣ ሐቀኝነትን (አቋመ ጽኑነትን) በሕይወቱ ማለማመድ አለበት። አንዳንድ መሪዎች ሰዎች እንዲከተሏቸው ቀድሞ ከነበራቸው የበለጠ ሥልጣን እንዲሰጣቸው የድርጅቱ ፖሊሲና የመዋቅር ለውጥ እንዲደረግ ይፈልጋሉ። "አልተባበርም" የሚሉ ተከታዮች (ሠራተኞች) ካሉ በእነርሱ ላይ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ይጠይቃሉ። ይሁን እንጂ ምንም ያህል ሥልጣን ቢሰጣቸውም፣ እንደጠየቁት አንዳንድ ለውጦች ቢደረጉም በአመራራቸው ውጤታማ አይሆኑም፤ ተከታዮቻቸውም በመሪነታቸው አምነው አይከተሏቸውም። በአመራራቸው አቅም ያጡት ተከታዮቻቸው ሥልጣናቸውን ባለማክበራቸው ሳይሆን "ሀቀኛ አቋም" የሌላቸው በመሆናቸው እንደሆነ የተረዱት አይመስሉም። በቅርቡ በ400 ሥራ እስኪያጆች ላይ በተደረገው ጥናት 45 ከመቶ (45%) በበላይ አለቆቻቸው ላይ፣ እንዲሁም አንድ ሦስተኛው ደግሞ በቅርብ አለቆቻቸው ላይ እምነት እንደሌላቸው ገልጸዋል። አንድ "የአመራር ሥርዓት" ምሁር የሆኑ ሰው፥

> *"የምመራቸው ሠራተኞች የሚረዱኝ ከሆነ ጆሯቸውን ይሰጡኛል፤ የሚያምኑኝ ከሆነ ግን ተግባራዊ ይሆኑልኛል" አሉ።*

አንድ መሪ ለመምራት አቅም (ጉልበት) የሚያገኘው፣ ሥልጣን ወይም የማዕረግ ዕድገት ሲጨመርለት ሳይሆን፣ ተከታዮቹ በእርሱ ላይ እምነት ሲኖራቸው ብቻ ነው። ተከታዮቹም በእርሱ ላይ እምነት የሚኖራቸውም፣ "አቋመ-ጽኑ" ሆኖ ሲያገኙት ነው። "ሐቀኛ አቋም" መተማመንን ያሳድራል።

[11] Dwight D. Eisenhower, Great Quates from Great Leaders, ed. Peggy Anderson (Lombard: Great Quatations, 1989).

## 8.2. "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው ለመሆን፥ ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላል

"ሐቀኛ አቋም" በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ እንዲሁ ወይም በቀላሉ የሚገኝ አይደለም። ዲሲፕሊን፣ ውስጣዊ የሆነ ብርታትን፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነተኛ ሆኖ መገኘትን፣ እንዲሁም የራስ ጥረትን ይጠይቃል። የሚያሳዝነው በአሁኑ ዘመን፣ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ሆነ፣ ከቤተ ክርስቲያን ውጪ፣ *"የገጸ ባሕሪ" (character)* ድክመት በብዛት የሚታይበት ዘመን መሆኑ ነው። "የሐቀኛነት" ባሕሪ የሚታይባቸው፣ ምሳሌ (ሞዴል) መሆን የሚችሉ ሰዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው። በሰለጠነው ዓለም ብዙ ብርቱዎችና ኃይለኞች ይኑሩ እንጂ መልካም "ገጸ ባሕሪ" ያላቸው ሰዎች ግን በብዛት የሉም። *ሌላውን የሚኮርጁ ብዙዎች ይኑሩ እንጂ የሚኮረጁ ወይም ሞዴል የሚሆኑ መሪዎች የሉም።* በአሁኑ ዘመን *"የሐቀኝነት"* ባሕሪ ደብዛው የጠፋበት ዘመን ነው። *"ሐቀኝነት"* ባህሪን መያዝ ለአንዳንድ የዘመኑ ሰዎች አስቸጋሪ ሆኖ የሚታይበት ምክን ያቱ ምን ይሆን? ቢሊ ግራሃም፣

> *"ሐቀኝነት" የተለያየ የአኗኗር አቋማችንን የሚያያይዝ ነው። ሀብት ቢጠፋ ምንም አንሆንም፤ ጤንነት ብናጣ በመጠኑ እንጎዳለን፤ ገጸ ባሕሪያችን ቢጠፋ ግን ሁሉንም እናጣለን" ሲሉ ተናገሩ።*

ሕይወታችን *"ሐቀኝነት"* ላይ ሲመሠረት፣ ለሌሎችም ሆነ ለራሳችን እውነተኞች ሆነን እንገኛለን።

## 8.3. "ሐቀኛ አቋም"፣ ያለው ሰው አስተማማኝ ነው

ጥሩ መንፈሳዊ መሪ፣ በሕይወቱ እንዲኖረው ከሚጠበቅበት መልካም ባህሪዎች መካከል አንደኛው፣ "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው መሆን ነው። መንፈሳዊ መሪ በድርጊቱም ሆነ በሚኖረው ዕለታዊ ሕይወቱ አስተማማኝነት ከሌለው፣ አምኖ የሚከተለው ተከታይ አያገኝም። መሪውን እንደ መሪ አምኖ ለመቀበል፣ "በሁሉም ነገር ከመሪው ጋር መስማማት አለብን ወይም አንድ ዓይነት አመለካከት እንዲኖረን ያስፈልጋል" ማለት አይደለም። ተከታዩ በመሪው ላይ እምነት ሊኖረው የሚችለው፣ "መሪው የሚናገረው ዝም ብሎ ሳይሆን ከልቡ ነው። እንዲሁም የሚኖረው ኑሮ እውነትነት ያለው ነው" ብሎ አምኖ መቀበል የቻለ እንደሆነ ነው። መሪው የሚናገረው ነገር፣ ከሚያደርገው ጋር የማይጋጭ ወይም የማይቃረን መሆን አለበት። እውነተኛ የሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች እውነተኛነታቸው በሚያደርጉት ነገር ሁሉ ስለሚታይ፣ ለሚያደርጉት ነገር ማስታወቂያ ማውጣት አያስፈልጋቸውም። ቅንነት የሌለው ነገር ለጊዜው የተሰወረ ወይም የተሸፈነ ይሁን እንጂ፣ ምንጊዜም ቢሆን መገለጡ አይቀርም። መሪው በሚመራቸው ሰዎች መካከል ጥሩ እስተያየትና ተቀባይነት እንዲኖረው፣ "የሐቀኝነት" ባሕሪ ያለው ሰው መሆን አለ



በት። በዚህ ዓይነት መንፈሳዊ መሪ ሌላው እንዲከተለው ባለው "ሐቀኛ አቋም" ሌሎችን የመሳብ ችሎታ እንዲኖረው ያስፈልጋል። ታላላቅ መሪዎች ይህን እውነት ያውቃሉ።

*የመሪዎች "ሐቀኛ አቋም" (Integrity)* በምን ይፈተናል? *"ሐቀኛ አቋም"* እንዳለ ንና እንደሌለን ለማወቅ በሁለት ዓይነት ፈተናዎች ውስጥ ማለፍ አለብን። አንደኛ፣ በክፉ ሁኔታዎች፣ ውስጥ ስናልፍ *"ሐቀኛ አቋማችን"* ይፈተናል። ሰው ልዩ ልዩ መከራና አደጋ ሲደርስበት፣ የሚወደው በሞት ሲለየው፣ ከተለያየ አቅጣጭ ተቃውሞም ሆነ ግፊት ሲደርስበት፣ "ሐቀኛ አቋሙን" እንደያዘ መዝለቅ የሚችል መሆኑና አለመሆኑ ተለይቶ ይታወቃል። ሠሎሞን ***"መከራ በሚደርስብህ ጊዜ መጽናት የማትችል ከሆንክ፣ ምንም ብርታት የለህም ማለት ነው"*** ይላል (ምሳሌ 24፥10)። ሁሉ ነገር መልካም ሲሆን፣ ወይም በሰላም ጊዜ "ሐቀኛ አቋም" ያለው ሰው ሆኖ መታየት (መቆም) ይህን ያህል ከባድ አይደለም። ነገር ግን ፈታኝ የሆነ ነገር ሲያጋጥም፣ ጸንቶ መቆም ግን ቀላል አይደለም። "ሐቀኛ አቋም" እንዳለን የምንፈተንበት ሁለተኛ ነገር፣ የተትረፈረፈ ሕይወት ሲኖረን፣ ሁሉም ነገር መልካም ሲሆንልን፣ የሚያመሰግኑንና የሚያደንቁን ሲበዙ፣ ያኔ "ሐቀኛ አቋማችን" እውነተኛነቱ ይመዘናል። ሠለሞን ***"ወርቅና ብር በእሳት ተፈትነው ጥሩነታቸው እንደሚታወቅ፣ የሰውም መልካምነት የሚቀርብለትን ምስጋና በሚቀበልበት ሁኔታ ተፈትኖ ይታወቃል"*** ይላል (ምሳሌ 27፥21)። ጳውሎስ በሕይወቱ ተለማምዶ ያለፈበትን የግል ሕይወቱን ሲገልጽ፣ ***"...በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁ፤ ማጣትን ዐውቃለሁ፤ ማግኘትንም ዐውቃለሁ። ብጠግብም፣ ብራብም፣ ባገኝም ሆነ ባጣ በማንኛውም ሆነ በየትኛውም ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማለትን ምስጢር ተረድቻለሁ"*** ይላል (ፊል. 4፥11-12)። ሰው "ለሐቀኛ አቋሙ" ፈታኝ መሆን የሚችለው፣ ማጣት...መራብ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ መጥገብ...ማግኘት፣ የተትረፈረፈ ሕይወት ውስጥ ማለፍም ጭምር ነው።

## 9. ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የማስተዳደር ችሎታ ያላቸው መሪዎች ያስፈልጋሉ

### 9.1. የማስተዳደር ችሎታ ያለው መሪ የግል ሕይወቱን በሥርዓት ማስተዳደር የሚችል ነው

ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ይህን የመሰለ መንፈሳዊ ባሕሪ በሕይወታቸው እን ዲታይባቸው ይጠብቅ ነበር። በግል ሕይወታቸው ውስጥ ያለውን ችግር መፍትሄ ሳይ ሰጡ፥ ሌሎችን መርዳት እንደማይችሉ ያውቃል። ኢየሱስ የሃይማኖት መሪዎችን የነቀ ፋቸው፥ ወይም "ዕውር መሪዎች" ያላቸው በቅድሚያ የራሳቸውን ሕይወት በትክክል መምራት ባለመቻላቸው ነበር። *"እነርሱ የታወሩና የዕውራን መሪዎች ስለሆኑ ተዉአቸው፤ ዕውር ዕውርን ቢመራ ሁለቱም በጉድጓድ ውስጥ ይወድቃሉ"* (የማቴ. 15፥14) አላቸው።

ሰው በሕይወቱ የሚፈልገውን ለማድረግ ሲነሳ፥ የተሳካ ውጤት ለማግኘት፥ ወይም ግቡን ለመምታት፣ ካሰበው ዓላማ ለመድረስ፣ በቅድሚያ የግል ሕይወቱን ዲሲፕሊን ማድረግ መቻል አለበት። ማንኛውም ሰው "መሪ ልሁን" ብሎ አይነሳም። ነገር ግን በተሰለፈበት ሥራም ሆነ አገልግሎት ላይ በትጋት ሲሠራ፥ የግል ሕይወቱን በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር ሲችል፣ ለመሪነት ይታጫል። አንዳንድ ሰዎች በአገልግሎታቸው ላይ መሪ ሊኖረው የሚገባውን ዓይነት ባህሪና ትጋት ሳያሳዩ፥ ለመሪነት መታጨትን ይፈልጋሉ። ሌላውን ማስተዳደር የሚፈልግ ሰው፥ በቅድሚያ የግል ሕይወቱን እንደሚገባው ማስተዳደር መቻል አለበት። የራሱን ሕይወት መጠበቅ ሲችል፥ ለመሪነት ብቃት እንዳለው ይታወቃል። ስለዚህ "መንፈሳዊ መሪ" የግል ሕይወቱን፥ ይኸውም ዕለታዊ ተግባሩንና እንዲሁም ልማዱን በአግባቡ መያዝ የሚችል መሆን አለበት። "መንፈሳዊ መሪ" ራሱን መቆጣጠር የሚችል የራሱ አለቃ መሆን አለበት። ይህም ማለት ጊዜውን፥ ገንዘቡን፥ ፍላጎቱንና እንዲሁም ያለውን ጉልበት በአግባቡ፣ እንዲሁም ቅደም ተከተሉን እውቆ ማስተዳደር መቻል ማለት ነው።

## 9.2. የማስተዳደር ችሎታ ያለው መሪ "የተረጋጋ" ባሕሪ ያለው ነው

"የተረጋጋ ባሕሪ" ያለው ሰው ጨዋ፥ ለመፍረድ የማይቸኩል፥ የሚያደርገውን ነገር አስቦ የሚያደርግ ሰው ነው። በቀላሉ የሚበሳጭ፥ አትንኩኝ ባይ፥ ድንጉጥ፥ በራሱ እምነት የሌለው ሳይሆን፣ በሚያምንበት ነገር ላይ ጸንቶ የሚቆም ሰው መሆን አለበት። በራሱ የማይተማመን መሪ፥ የሚመራቸውን ሰዎች በራሳቸው እምነት እንዳይኖራቸው የማድረግ ዝንባሌ አለው። ጠንከር ያለ ነገር ሲያጋጥመው ወይም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፍ ቶሎ የሚደናገጥና የሚፈራ መሪ፥ የሚመራቸውም ሰዎች ፈሪና እንዲሁም በራሳቸው እምነት የሌላቸው ይሆናሉ። "የተረጋጋ ባሕሪ" ማንኛውም መንፈሳዊ መሪ ሊኖረው የሚገባ ነው። ይህን ዓይነት ባሕሪ የሌለው መሪ፥ ችግር ሲመጣ፥ ረጋ ብሎ መፍትሄ በመፈለግ ፈንታ፥ በጭንቀት ውስጥ ሆኖ "ምን ልናደርግ ነው?" በማለት ራሱ ተጭንቆ ሌሎችንም ያስጨንቃል። የሚከተሉትም ምዕመናን ደፍረው በቃላት ገልጸው ባይነግሩትም፣ ከውስጣቸው "እኛን ለምን ትጠይቀናለህ፥ መሪው አንተ ስለሆንክ መፍትሄውን ንገረን እንጂ" ማለታቸው አይቀርም። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲያልፍ፥ በእግዚአብሔር በመተማመን ራሱንም ሆነ የሚመራቸውን ሰዎች ማረጋጋት የሚችል መሆን አለበት። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ዳንኤል ነው። ናቡከደነፆር በነገሠ በሁለተኛው ዓመት ሕልም አይቶ ሕልሙ ምን እንደሆነ ለማወቅ መንፈሱ በተጨነቀበት ወቅት፣ በባቢሎን ውስጥ ያሉት ጠቢባን ሕልሙን ማወቅና መፍታት ስላቃታቸው ናቡከደናፆር ተበሳጭቶ "ጠቢባን ሁሉ እንዲገደሉ ዐዋጅ አወጣ፤ ዳንኤልና ጓደኞቹን ፈልገው እንዲገድሉ ሰዎች ተላኩ" (ዳን. 2፥13)። ዳንኤል ሞት በእርሱና በጓደኞቹ ላይ አፍጥጦ በመጣበት ወቅት በመደናገጥና በመርበትበት ፈንታ ወደ ቤቱ ተመልሶ ለጓደኞቹ ለአናንያ፣ ለሚሳኤልና ለአዛርያ ነገሩን ከገለጠላቸው በኋላ፣ *"እርሱና ጓደኞቹ ከቀሩት የባቢሎን ጠቢባን ጋር እንዳይገደሉ፣ የሰማይ አምላክ ምሕረት ያደርግላቸውና ምስጢሩንም ይገልጥላቸው ዘንድ እንዲጸልዩ አሳሰባቸው"* (ዳን. 2፥18)። መንፈሳዊ መሪ በእርሱም ሆነ በሚመራቸው ሕዝቦች ላይ ያልተጠበቀ ክፉ ነገር ሲደርስ፣ ራሱ የተረጋጋ መንፈስ ኖሮት ሕዝቡን ማረጋጋት መቻል አለበት። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥመው፣ በመደናገጥና በመርበትበት ፈንታ በጌታ ታላቅነት በመተማመን ሁኔታዎችን ለመመልከትና መስመር ለማስያዝ ይሞክራል።



## 9.2. የማስተዳደር ችሎታ ያለው መሪ እርቆ የሚያስብና ትሁት ነው

"እርቆ የሚያስብ" ሰው ትሁት፥ የራሱ የሆነ ጤናማ ሚዛን ያለው፥ ችሎታውና ስጦታውን ለይቶ የሚያውቅ ሰው ነው። "ትሁት" ስንል፥ ከሆነው በታች ራሱን "ደካማ" አድርጎ የሚቆጥርና የሚገምት ማለት አይደለም። ራሳችንን ከሆንነው በላይ ማተለቅ ትክክል እንዳልሆነው ሁሉ፥ ከሆንነው በታች ራሳችንን ማሳነስም ትክክል አይደለም። "ትሁት" መሆን ማለት፥ እግዚአብሔር እንደሚያየንና እንደሚያውቀን መሆን ማለት ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ትሁት መሆናቸውን ለማሳወቅ "እኔ የማልረባ ትል ነኝ" ሲሉ ይሰማሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በውድ ዋጋ የተገዛን የክብር ዕቃ መሆናችንን ይናገራል። *"...እናንተ የእግዚአብሔር ናችሁ እንጂ የራሳችሁ አይደላችሁም። ምክንያቱም እርሱ በዋጋ ገዝቶአችኋል፤ ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ"* (1 ቆሮ. 6፥19-20)። "እርቆ የሚያስብ" መሪ እግዚአብሔር በሕይወቱ በሠራው ሥራ ምክንያት ሕይወቱ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው የሚረዳ ነው። ይሁን እንጂ፥ ራሱን ከሆነው በላይ ከፍ አድርጎ እንዳይመለከት ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። አንዳንዶች በሕይወታቸው የሆነው ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ የሆነላቸው መሆኑን በመዘንጋት በችሎታቸውና በስጦታቸው ሲኩሩ ወይም ሲታበዩ ይታያሉ። በመንፈሳዊ መሪ ሕይወት ውስጥ "ራስን የማጉላት" ባህሪ ጎልቶ ሲታይ፣ ምን ያህል ጌታን ያሳዝነው ይሆን? አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በሕይወታቸው፥ ባላቸው አገልግሎት ያገኙትን ከፍተኛ ውጤት ሲናገሩ መስማት በአሁኑ ጊዜ በጣም የተለመደ ነው። የሆነላቸውና የተሳካላቸው በእግዚእብሔር ኃይልና ጸጋ ምክንያት እንደሆነ በመግለጽ ፈንታ፥ ያላቸው ከፍተኛ ትምህርት፥ የተፈጥሮ ስጦታቸው፥ ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታቸው እንዲሁም የአስተዳደር ብቃታቸው እንደሆነ በድፍረት ሲናገሩ መስማት፣ እንኳን እግዚአብሔርን ማንኛውንም ሰው ይሰቀጥጣል። የተረጋጋና እርቆ ማሰብ የሚችል መሪ ራሱን መግዛት ወይም መቆጣጠር የሚችል ሰው ነው። ያለው ችሎታና ስጦታው ከጌታ የመጣ እንደሆነ ያምናል።

## 9.3. የማስተዳደር ችሎታ ያለው መሪ ሀሳቡን በንግግር መግለጽ ይችላል

ጥሩ መሪ አሳቡን ገልጾ በደንብ የማስረዳት ችሎታ ያለው ሰው ነው። ትክክለኛውን ቃል በትክክለኛው ጊዜ መናገር የሚችል ነው። አንዳንድ ሰው ብዙ ቢናገርም ትክክለኛ አሳቡን ግን ገልጾ መናገር አይሆንለትም። ሰዎች ብዙ ጊዜ ከአፋችን የሚወጣውን ቃል ከመስማት የበለጠ፣ መንፈሳችንን የመረዳት ችሎታ አላቸው። አንድ ነገር ስንናገር የተናገርነውን ዝም ብለው ከመስማት ይልቅ፥ የአነጋገራችንን ሁኔታ፥ ያንን ለምን እንደተናገርንና እንዲሁም የተናገርነው ነገር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነና እንዳልሆነ የመመርመር ችሎታ እንዳላቸው እናውቃለን። ሰዎች ለተናገርነው ንግግር የሚሰጡን መልስም ሆነ አስተያየት፥ አሳባችንን በትክክል መግለጽ መቻላችንን ወይም አለመቻላችንን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው። አሳባችንን በትክክል መግለጽ ከቻልን፥ በንግግራችን ውጤት እናያለን። ከመናገራችን በፊት ምን ዓይነት ውጤት እንደምንፈልግ አስቀድመን ማወቅ አለብን። ብዙ መናገር ጥሩ ውጤት ያስገኛል ማለት አይደለም። ብዙ በመናገራቸው ያስተላለፉት መልዕክት ሰሚ የሚያስገኝላቸው የሚመስላቸው ሰዎች አሉ። ጠቢቡ ሠለሞን፥ *"..ብዙ ሕልምና ብዙ ቃል ከንቱ ነው..."* ይላል (መክብብ 5፥7)።

ሰው በንግግር ወይም በሌላ መንገድ አሳቡን የመግለጽ ችሎታ አለው። በፊቱ ገጽታ ወይም በአመለካከቱ ብቻ ብዙ ነገር መግለጽ ይችላል። አሳብን መግለጽ መቻል ትምህርት ቤት ገብተን አንድ ጊዜ ተምረን የምንጨርሰው አይደለም። በሂደት የምንማረው ችሎታ ነው። ራስን መግለጽ አለመቻል፣ ኑሮችንን የበለጠ አስቸጋሪ ያደርገዋል። ጥሩም ሆነ መጥፎ ሰው በየቀኑ፥ በተገኘው መንገድ ሁሉ የግድ አሳቡን መግለጽ መቻል አለበት። ራስን የመግለጽን አስፈላጊነት ያልተረዳ መሪ ራሱን ብቻ ሳይሆን፣ የሚመራውንም ሕዝብ ጉዳት ላይ ይጥላል። ሕብረቱ ወይም ድርጅቱ ባደገ ቁጥር "የመገናኛ ተቋም" (communication) አስፈላጊነቱ፣ የበለጠ ይሆናል። አንዳንድ ሰዎች "የመገናኛ ተቋም" ሂደት የተወሳሰበ እንዲሆን የማድረግ ዝንባሌ አላቸው። ለምሳሌ፣ በወቅቱ በመሠራት ላይ ባለው ፕሮጀክት ውስጥ ድርሻ ያላቸውን ሰዎች፥ ከእነርሱ የሚጠበቅባቸውን የሥራ ኃላፊነት፣ ምን መሥራት እንዳለባቸው፥ ሥራው እንዴት መሠራት እንዳለበትና እንዲሁም መቼ ተሠርቶ ማለቅ እንዳለበት መሪው በግልጽ ሊነገራቸው ይገባል። አሳቡ በግልጽ ሳይነገራቸው በመቅረቱ ምክንያት የሚፈጠረው ችግር ከባድ ሊሆን ይችላል። በተለይ ብዙ ሕዝብ ያለበትን ሕብረት ወይም ድርጅት የሚመራው ሰው፣ ሕዝቡ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በደንብ መወጣት እንዲችል፣ አሳቡን በትክክልና በጥራት የመግለጽ ችሎታ ሊኖረው ይገባል። የሕብረቱ ወይም የድርጅቱ ዋና መሪ የሆነው ሰው አስተዋይ ከሆነ፥ የተወሰነው ውሳኔም ሆነ፥ ሊሠራ የታቀደው ነገር በጊዜውና በትክክል ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ መግለጽ አለበት። ካልሆነ ግን በጥራትና በግልጽ አሳቡን ማስተላለፍ ለሚችሉ፥ እርሱ ለሚያምንባቸው ሰዎች ውክልናውን (delegate) መስጠት አለበት።



*"ግንኙነት" (ኮሚውኒኬሽን)* የተጀመረው ከእግዚአብሔር ነው። ዓለምም ሆነ ሰው ከመፈጠራቸው በፊት እግዚአብሔር አብ ከልጁ ከኢየሱስ ጋር፥ እንዲሁም ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፥ ግንኙነት ነበራቸው። ሰው "ግንኙነትን" የተማረው ከእግዚአብሔር ነው፤ ምክንያቱም በመጀመሪያ እግዚአብሔር ከሰው ጋር የተገናኘ በመሆኑ ነው። መጀመሪያ እግዚአብሔር ራሱን ለመግለጽ የሞከረው በእጆቹ ሥራዎች ነው። *"ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤ የሰማይ ጠፈሮችም፤ የእግዚአብሔርን ሥራ ያውጃሉ... ንግግር ወይም ቃል የላቸውም፤ ድምጻቸውም አይሰማም፤ ነገር ግን መልእክታቸው ወደ ዓለም ሁሉ ይሰራጫል፤ እስከ ምድር ዳርቻም ይደርሳል..."* (መዝ. 19፥1-3)። በዘመናት እግዚአብሔር ከሰው ጋር በተለያየ መንገድ ይገናኝ ነበር። በመጨረሻም በልጁ በኢየሱስ በኩል ይናገር ነበር። *"እግዚአብሔር በቀድሞ ዘመናት በተለያየ መንገድና በነቢያት አማካይነት ለአባቶቻችን ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር"* (ዕብ. 1፥1) ይላል። በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር ለሰው የሚናገርበት ዋናው መንገድ በቃሉ አማካኝነት ነው። እግዚአብሔር ሲናገር፥

ሁልጊዜ የሚናገረው እውነት ነው። ውሸት ተናግሮ አያውቅም።

የሚናገረውም በኃይልና በሥልጣን ነው።

በተለያየ መንገድ ይናገራል።

ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ምንም ሳያስቀር ይናገራል።

የሚናገረውም በፍቅርና በርህራሄ ተሞልቶ ነው።

ስለዚህ እንዴት መናገር (መገናኘት) እንዳለብን
ከእግዚአብሔር መማር አለብን።

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት ሌላው መንገድ ጸሎት ነው። መንፈሳዊ መሪ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ካልቻለ፥ የእግዚአብሔር አሳብ ምን እንደሆነ በቂ መረዳት ከሌለው በሕይወቱም ሆነ በአመራሩ ውስጥ ብዙ ችግሮች ያጋጥሙታል። መንፈሳዊ መሪ ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ካልተገናኘ፥ ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረውም ግንኙነት ፍሬያማ አይሆንም። ሙሴ የብዙ ሕዝብ መሪ በመሆኑ፤ ብዙ ሥራዎች ነበሩበት። ይሁን እንጂ፤ ሙሴ ከሚሠራቸው የሥራ ዝርዝሮች ውስጥ "ጸሎት" የመጀመሪያውና ትልቁን ክፍል የያዘ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት፥ ከሰው ጋር ከመገናኘት ይበልጣል። መንፈሳዊ መሪ፥ ጥሩ መሪ መሆን የሚችለው ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር ሲችል ነው። መሪ ከሚመራቸው ሰዎች ጋር ተራርቆ መምራት አይችልም። ግንኙነቱ ከማሕበሩ ወይም ከጠቅላላ ሕብረቱ ጋር ብቻ ሳይሆን፥ ከግለሰቡም ጋር መሆን አለበት።

## 9.4. የማስተዳደር ችሎታ ያለው መሪ ተደማጭነት ያለው ነው

ማንኛውም ሰው ከሌላው ሰው ጋር በንግግር የሚያደርገው "ግንኙነት" የተሟላ እንዲሆን፣ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆን አድማጭም ሲኖር ነው። በምንም ዓይነት ሁኔታና ቋንቋ ብንናገር፣ አንዳንድ ሰዎች የሚያዳምጡ አይደሉም። "ውይይት" በሁለት ሰዎች መካከል እንጂ በአንድ ሰው ብቻ የሚካሄድ አይደለም። ተናጋሪ አሳቡን ስመግለጽ፣ የሚያዳምጠው ሰው (አዳማጭ) የግድ መኖር አለበት። በሰዎች መካከል ጥሩ ውይይት ወይም ግንኙነት ሊፈጠር የማይችልበት አንደኛውና ትልቁ ምክንያት ሰዎች በማዳመጥ ፈንታ ሁልጊዜ መናገር ስለሚፈልጉ ነው። መሪዎችን ተከታዮቻቸው የማያዳምጧቸው ለምን ይሆን?

1ኛ/ ***ብዙ ስለሚናገር ይሆናል*** – *የብዙ ሰዎች ችግር ብዙ መናገር ነው። ብዙ ከተናገሩ፣ አሳባቸውን የሚረዱላቸው የሚመስላቸው አሉ። ጠቢቡ ሠለሞን "...**የምትናገረው ቃልህ የተመጠነ ይሁን...**" (መክብብ 5፥2) በማለት ምክር ይሰጣል። እንዲሁም "...**ከልፍለፋህም ብዛት የተነሣ የሞኝነትን ቃል እስከ መናገር ትደርሳለህ..**" ይላል (መክብብ 5፥3)። ሰዎች ንግግር ሲበዛባቸው፣ የሰሙትን ሁሉ ማስታወስ የማይችሉ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ የሰሙትንም በቀላሉ ይረሱታል። ብዙ መናገር የሚያመጣው ሌላው ችግር ሰዎች ንግግር ሲበዛባቸው ስለሚሰለቻቸው አዕምሯቸው መተኛት ይጀምራል። ጥሩ መሪ አድማጭ እንዲኖረው፣ መቼ መናገር እንዳለበት ብቻ ሳይሆን፣ መቼ ንግግሩን ማቆም እንዳለበትም ጭምር ነው።*

2ኛ/ ***አሳባቸውን በደንብ መግለጽ ስለማይችሉ ይሆናል*** – *ሰዎች ግራ የሚጋቡት፣ የሚጠበቅባቸውን ማድረግ የማይችሉት፣ በመሪነት ደረጃ የተቀመጠው ሰው አሳቡን እንደሚገባው ገልጾ መመሪያ መስጠት ካለመቻሉ የተነሣ ነው። ይህን ዓይነቱ ሁኔታ ብዙዎቹን ያበሳጫል። አንዳንዶች ደግሞ የተነገራቸው ነገር በደንብ ካልገባቸው "ችግሩ ያለው እኛ መረዳት ስላቃተን ነው" በማለት በራሳቸው የሚፈርዱ አሉ። ጥሩ መሪ ንግግሩን ከመዝጋቱ በፊት፣ የሰጠው መመሪያ በደንብ ገብቷቸው እንደሆን ሕዝቡን በመጠየቅ ለመረዳት መሞከር አለበት።*

3ኛ/ ***ሌላው በሚገባው ዓይነትና ቋንቋ ስለማይናገሩ ይሆናል*** – *በረቀቀና በሚጣፍጥ ቋንቋ መናገር መጥፎ ባይሆንም፣ አድማጮች የማይረዱት ከሆነ ዋጋ የለውም። አንዳንድ ተናጋሪዎች ምን ያህል እንደተማሩና እንደሚያውቁ እንዲሁም ረቂቅ የሆኑ ተናጋሪዎች መስለው ለመታየት ሲሉ ብቻ፣ ንግግራቸውን ሰዎች እንዳይረዱት የሚያደርጉ አሉ። ጥሩ መሪ ለማስተላለፍ የሚፈልገውን አሳብ የሚከተሉት ሰዎች ሊረዱት በሚችሉት ሁኔታና ቋንቋ ማቅረብ አለበት። ሰዎች በሚረዱት ቋንቋና ሁኔታ አለማቅረቡ፣ የሚያዳምጡት ሰዎች አሳቡን የማይረዱት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ራሱን አተልቆ ለማሳየት የሚሞክር ሰው መሆኑን ስለሚገነዘቡ፣ በማድነቅ ፈንታ ይታዘቡታል።*



4ኛ/ ***ከመጠን በላይ አጋንነው ስለሚናገሩ ይሆናል*** – *አንዳንድ ሰዎች አጋነው የሚያወሩበት ሁሉም የራሳቸው የሆነ የተለያየ ምክንያት አላቸው። አንደኛው ምክንያት ከሆኑት በላይ ራሳቸውን አተልቀው ለማሳየት ይሆናል። ወይም ሰዎች ሲያዳምጧቸው የሚናገሩት ንግግር በጣም አስፈላጊ ነው ብለው እንዲያስቡ ለማድረግ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ከዚህ በፊት በሕይወታቸው የሠሩትን ስህተት ለመሸፈን የሚያደርጉት ጥረት ይሆናል። አጋኖ ማውራት ብዙ ጊዜ ከውሸት በስተቀር ሌላ ነገር እንዳልሆነ፣ ወይም ሰዎችን ለማሳሳት እውነት ያልሆነ ነገር መደባለቅ መሆኑን የተቀበሉት በጣም ጥቂት ናቸው። ይህን ዓይነቱ ሁኔታ፣ መሪው ከሚመራቸው ሕዝቦች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዳይኖረው ከፍተኛ እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል የታወቀ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከመጠን በላይ በተጋነነ ወሬ ምክንያት የተጎዱ ብዙዎች ናቸው።*

ሰዎች መሪዎቻቸውን የማያዳምጡበትን ምክንያት በመጠኑም ቢሆን ከላይ ተመልክተናል። እንዲያዳምጧቸውስ ምን ዓይነት አቋም እንዲኖራቸው ያስፈልጋል? በተከታዮቻቸው ዘንድ ተደማጭነት እንዲኖራቸው መሪዎች፣

1ኛ) *ሁልጊዜ እውነቱን የሚናገሩ መሆን አለባቸው* – አንዳንድ ጊዜ የሚያውቁትን ነገር ሁሉ በአንድ ጊዜ መናገር አስፈላጊ የማይሆንበት ጊዜ አለ። ይሁን እንጂ፣ ምን ጊዜም ቢሆን ውሸት መናገር የለባቸውም። እልፎ አልፎ "ስለዚህ ነገር መናገር ወይም ሁኔታውን መግለጽ በአሁኑ ጊዜ አልፈልግም" ማለት ይችላሉ። መሪዎች ከሚመሩት ሕዝብ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚበላሸው፣ "ሀቀኝነት" ወይም እውነተኛነት ሲጠፋ ነው። ሠለሞን ***"እውነትን የሚናገር ምስክር ሕይወትን ያድናል፤ ሐሰት የሚናገር ግን ከዳተኛ ነው"*** ይላል (ምሳሌ 14፥25)። እንዲሁም ምሳሌ 12፥19 ላይ ***"እውነት የሚናገሩ ከንፈሮች ለዘላለም ጸንተው ይኖራሉ፤ ሐሰተኛ አንደበት ግን ለቅጽበት ያህል ብቻ ነው"*** ይላል። ስለዚህ፣ እውነት አለመናገር የሚያደርሰውን ችግር ተገንዝበው መንፈሳዊ መሪዎች ሁልጊዜ እውነትን የሚናገሩ መሆን አለባቸው።

2ኛ) *የሌሎችን ምስጢር የሚጠብቁ መሆን አለባቸው* – አንዳንድ ሰዎች ምክር (ዕርዳታ) በመፈለግ የግል ሚስጥራቸውን ለመንፈሳዊ መሪዎቻቸው ገልጠው ያካፍላሉ። የሚነግሯቸውም ምስጢራቸውን ለሌሎች ገልጠው እንዳያናገሩ በማስጠንቀቅ ነው። ምስጢራቸውን የማይጠብቁላቸው ከሆነ፣ ለመሪዎቻቸው ላይ እምነት የሚያጡ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ሐሜተኞች በመቁጠር ይታዘቧቸዋል። ***"ሐሜተኛ ምስጢር አይጠብቅም፤ ታማኝ ሰው***

*ግን ምስጢር ይጠብቃል"* ይላል (ምሳሌ 11፥13)። እንዲሁም ምሳሌ 17፥9 ላይ *"በደልን የሚሸፍን ፍቅርን ያዳብራል፤ ነገርን የሚደጋግም ግን የልብ ወዳጆችን ይለያያል"* ይላል። መንፈሳዊ መሪ የሚመራቸውን ሰዎች ምስጢር የሚጠብቅ ከሆነ፥ የሚናገረውን ነገር ለማዳመጥ አይከብዳቸውም። ዕርዳታ ፈላጊዎች "ማንም እንዳይሰማው" ብለው የሚያቀርቡትን ሀሳብ መሪው ማስተናገድ ያለበት በምን ዓይነት ሁኔታ መሆን አለበት? የሚነገራቸውን ነገር ምስጢር አድርገው ለመያዝ ካልፈለጉ፣ "ለማንም አልናገርም" ብለው ተስፋ መግባት የለባቸውም። የተሻለ የሚሆነው፥ *"ለሌላ ለው መንገር የሌለበት መሆኑን ለመወሰን አስቀድሜ ታሪኩን መስማት አለብኝ"* ማለት መቻል አለባቸው። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ መንገሩ አስፈላጊና ጠቃሚ የሚሆንበት ጊዜ ስላ አለ ነው። ወይም *"ላለመናገር የተቻለኝን ያህል እሞክራለሁ"* ማለት የሚሻልበት ጊዜ አለ።

*3ኛ)* ***<u>ለሌሎች ልባቸው የተከፈተ መሆን አለበት</u>***– መንፈሳዊ መሪዎች ከሰዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖራቸው ከፈለጉ፥ *"ይህን ብነግረው ለለ እኔ ምን ያስብ ይሆን? ምን ይለኝ ይሆን?"* በማለት ያለ ፍርሃት የልባቸውን እንዲያጫውቷቸው ልባቸውን ክፍት አድርገው ማቅረብ አለባቸው። ብዙዎች ከፍርሃት የተነሳ ያለባቸውን ችግርም ሆነ ፈተና ለመንፈሳዊ መሪዎች መግለጽ ይከብዳቸዋል። ለጥሩ ግንኙነት፥ "ጥሩ አዳማጭ" መሆን አስፈላጊ ነው። መሪው የሚያዳምጣቸው ካልመሰላቸው፥ የልባቸውን አሳብ ገልጠው መናገር አይሆንላቸውም። በዚህ ዓይነት መሪው ከሚመራቸው ሰዎች ጋር መገናኘት ካልቻለ፥ የመሪነቱ ኃይል የቀነሰ ይሆናል። ሌላው ሰው አሳብ ሲያቀርብላቸው አሳባቸውን ሰምቶ በመቀበል ፈንታ የሚነቅፉ ከሆነ፥ መሪው ትዕቢተኛ፥ በራሱ ላይ ያተኮረ ሕይወት ያለው ነው በማለት ይሸሿቸዋል።

*4ኛ)* ***<u>ሌሎችን መቀበል የሚችሉ መሆን አለባቸው</u>*** – ሕዝቡ በመሪዎቻቸው ላይ እምነት የሚኖራቸው፥ ልክ እንዳሉ፥ ይኸውም ድካምም ቢኖርባቸው ከነድካማቸው የሚቀበሏቸው መሆኑን ሲያረጋግጡ ነው። በንቀት መንፈስ ማነጋገር መሪው ልክ እንዳሉ እንዳልተቀበላቸው ያሳያል። ችግራቸውን ተረድተው የሚያግዙላቸውን መሪዎች እንጂ፥ የሚፈርዱባቸውን መንፈሳዊ መሪዎች የሚፈልግ ማንም የለም። ሁኔታው ሳይገባቸው፥ ታሪኩን እንደሚገባው ሳይረዱ አስፈላጊ ባልሆነበት ጊዜ ጥበብ የጎደለው አስተያየትና ፍርድ የሚሰጡ አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች እንዳሉ የታወቀ ነው። አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች በምዕመናኑ መካከል አድሎ የሚያሳዩ አሉ። ይህን ሲያደርጉ፥ አድሎ የተደረገበት ሰው፥ መሪው ያልተቀበለው መሆኑን ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔርም ያልተቀበለው ሲመስለው እንደሚችል መረዳት ይጠቅማል።



*መንፈሳዊ መሪዎች ለተወሰኑ ለዎች፥ በተለይ ቅርባችን ነው ለሚሉት ብቻ* አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሲያደርጉ፥ ሌሎችን ግን መቀበል አቅቷቸው ሲገፉ ይታያል። እንዲህ ዓይነቱ ባሕሪያቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጠይቃቸው መሆኑን መዘንጋት የለባቸውም።

## 10. ለቤተ ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ተጠያቂነት (Accountability) ያላቸው መሪዎች ያስፈልጋሉ

በየትኛውም የሥራ ዘርፍ የተሰሰፈ ሰው ከበላይ ሆኖ የሚቆጣጠረው አለቃ አለው። ሲያጠፋ የሚገስጸው፣ ሲያሳምር "ጎሽ!" የሚለው አለቃ ይኖረዋል። አንዳንድ ሰው *"ማንም እንዲቆጣጠረኝ አልፈልግም፤ የራሴ አለቃ፣ የራሴ ገዢ መሆን ነው የምፈልገው"* በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሲሉ ይሰማሉ። ይሁን እንጂ፣ በትክክለኛው ከኃላፊነት ወይም ከተጠያቂነት ነጻ አይሆኑም።

ለማንም ተጠያቂነት የሌለው ሰው፣ ልቅ ሕይወት፣ እንደ ልቡ የመኖር ዝንባሌ ያለው ሰው ነው። ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወትም ለመምራት ለሌላው ሰው ተጠያቂነት እንዲኖረን ማድረግ አስፈላጊ ነው። ብዙ ታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች *"ከእኔ በላይ ማንም የለም"፤ አለቃ የለብኝም"* የሚሉ በሕይወታቸው መጥፎ አወዳደቅ እንደወደቁ እናውቃለን።

ማንኛውም ሰው በሕይወቱ ተጠያቂነት እንዲኖረው ያስፈልጋል፥

- የመንፈሳዊ አገልግሎት ድርጅት መሪ ለድርጅቱ የቦርድ አባሎች ተጠያቂ መሆን አለበት።
- የቤተ ክርስቲያን መጋቢ በቤተ ክርስቲያኒቱ የቦርድ አባሎች ወይም የሽማግሌዎች ቦርድ ተጠያቂ መሆን አለበት። ብቻውን ፈላጭ ቆራጭ መሆን የለበትም።
- የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ለተቀሩት የሽማግሌዎች የቦርድ አባላትና ለምዕመናን ተጠያቂነት ሊኖረው ያስፈልጋል።
- ምዕመናን ለሽማግሌዎች ቦርድ ወይም ለቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ራሱን መስጠትና ማስገዛት ይኖርበታል።

ይህ ከላይ የገለጽነው በአንድ ዓይነት መዋቅር ውስጥ ስንሆን ለአሠራራችን የሚረዳን ወይም የሚጠቅመን ነው። ከመዋቅሩስ ውጪ፣ በግል ሕይወታችን ራሳችን ፈቅደን ከሌላው ሰው ጋር ማድረግ ወይም ተጠያቂ መሆን ያስፈልገን ይሆን? የእግዚአብሔር ቃል በተለየየ ሥፍራ እርስ በርሳችን መጠበቅ፥ መደጋገፍ እንደሚያስፈልገን ያስተምረናል። ተጠያቂ መሆን ያለበት መንፈሳዊ መሪው ብቻ ሳይሆን፥ ምዕመናንም ራሳቸውን ለመንፈሳዊ መሪዎች ተጠያቂ ማድረግ አለባቸው። ይህም እግዚአብሔር

የሚያዘው መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለምዕመናን የግል ሕይወታቸውም ጠቃሚ በመሆኑ ነው። ብዙዎች ለእግዚአብሔር ተጠያቂዎች መሆናቸውን ያለምንም ጥያቄ አምነው ይቀበላሉ። "አባታችን ነው፤ ፍጹም አምላክ ነው፤ በሕይወታችን የፈቀደውን ለማድረግ ሙሉ መብት አለው፤ ያለአንዳች አድልዎ መፍረድ ይችላል" ይላሉ። ለምድራዊ ሰው ግን ራሳቸውን ተጠያቂ ለማድረግ ፈቃደኞች አይደሉም። አንዳንድ ሰዎች፣ "ለእግዚአብሔር እንጂ ለማንም አልገዛም" ሲሉ ይሰማሉ። እንዲህ የሚሉት ቀደም ሲል በሕይወታቸው "መንፈሳዊ መሪ ነኝ" በሚሉ ሰዎች የተጎዱ በመሆናቸው ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ለመንፈሳዊ መሪዎች ራሳችንን ተጠያቂዎች ማድረግ እንዳለብን ቃሉ ያስተምረናል።

## ምዕራፍ ፫

# ጥሪን መጠበቅና የማሳደግ ኃላፊነት

*"...ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር..."*(ሮሜ 12፥8)

ቤተ ክርስቲያን ስለምትከተለው የአመራር ሥልትና እንዲሁም መሪዎቿ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዴት እንደሚፈጽሙ በቂ የሆነ መረዳት ለማግኘት፣ በአንዳንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የሚፈጠሩትን አንዳንድ ችግሮች በቅድሚያ ማወቅ ይጠቅማል። በምዕራቡ ዓለም፣ ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ሁኔታ ለማወቅ ብዙ ጥናቶችና ምርምሮች ተደርገዋል። ምርምሩን ካደረጉት ምሁራን መካከል አንደኛው *"ቶድ ሃንተር"* የተባሉ የአንድ ቤተ እምነት መሪ ሲሆኑ፣ በጥናታቸውካገኙት ውጤት ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ በታች ጠቅሰናል፥

- በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያናቸው የሰጣቸው ራዕይ ምን እንደሆነ በትክክል መግለጽ የሚችሉት ከመቶ መጋቢዎቹ ውስጥ አሥሩ ብቻ ናቸው።

- በአሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆነው ከሚያገለግሉት ውስጥ፣ "የመሪነት ስጦታ አለኝ" የሚሉት፥ ከመቶ አምስቱ (5%) መጋቢዎች ብቻ